በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን

ጽርሐ ተዋሕዶ

የተሰኘ ልዩ ዕትም መጽሔት



ዘመናዊና ዓለም አቀፋዊ ሁለገብ የስብሰባ ማዕከል

ይህ “ጽርሐ ተዋሕዶ” የተሰኘ ልዩ ዕትም መጽሔት፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት የተገነባውን ዘመናዊና ዓለም አቀፋዊ ሁለገብ የስብሰባ ማዕከል በማስመልከት በሕዝብ ግንኙነት መምሪያ የተዘጋጀ ነው።

ማውጫ

የመጽሔቱ መልእክት 2
የዐቢይ ኮሚቴው መልዕክት 4
የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ አባታዊ መልእክት 6
የብፁዕ ጠቅላዩ ሥራ አስኪያጅ መልእክት 8
የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ መልእክት 10
የመንፈሳዊ ዘርፍ ዋና ምክትል ሥራ አስኪያጅ መልእክት 12
የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዘርፍ ዋና ምክትል ሥራ አስኪያጅ መልእክት 14
መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላዩ ቤተ ክህነት ባለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት 16
የቤተ ክርስቲያናችንን ታሪክና ክብር የሚመጥን ዓለም አቀፍ የሰብሰባ ማእከል 32
በጠቅላዩ ቤተ ክህነት ተሠርተው የተጠናቀቁ እና ጅምር የልማት ሥራዎች 51
የዲጂታል ቴክኖሎጂና ሚዲያ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብዙኃን መገናኛ. 57
በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ በ2018 ዓ.ም. የተከናወኑ ተግባራት 65
የአዳራሽ ትዝታ 69

ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ሠዩማን አስከንድር ገ/ክርስቶስ

ኮምፒዩተር ጽሑፍና ዝግጅት
ሳዕከ ሰላም ነቢየ ኤልያስ

ግራፊክስ ዲዛይን
ተመስገን ቶማስ

ትርጉም
ወ/ሪት ዮርዳኖስ አዲሴ
መምህር አካለወልድ ተሰማ (ዶ/ር)
ረዳት ፕሮፌሰር ቀሲስ ግርማ ባቱ
መምህር ዳንኤል ሰዩፈ ሚካኤል

ፎቶግራፍ
መልአከ ሰላም አባ ኪሮስ ወልደአብ

ኅትመት
ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት

የመጽሔቱ መልእክት

"የትውልድ ቅብብሎሽ ሥራ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት"

ጥንታዊት÷ ታሪካዊት÷ ብሔራዊትና ዓለም አቀፋዊት የሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎቷን ለማሳለጥ÷ አስተዳደራዊ መዋቅሯን ለማዘመን÷ ልማቷን ለማፋጠንና የገቢ አቅሟን ለማሳደግ ያደረገቻቸው የተሳኩ ጥረቶች ውጤታማ መሆን የቻሉት÷ ሥራዎቹን በቅብብሎሽና በትብብር ማከናወን በመቻሏ እንደሆነ ከጥንት ጀምሮ የተሠሩና በትውልድ ቅብብሎሽ ውጤታማ የሆኑ ጥንታውያን ገዳማት÷ አብያተ ክርስቲያናትና ዛሬ የቤተ ክርስቲያን የገቢ ምንጭ በመሆን በማገልገል ላይ ያሉ ሕንጻዎችና ቤቶች ቋሚ ምስክሮች ናቸው።

ቀደምት አባቶቻችን ቋሚ ሥራዎችን ለመሥራት አስበው÷ አቅደውና ጀምረው ሳይጨርሷቸው በኅልፈተ ሥጋ ሲለዩ÷ ሌሎች በውጥኑ ወቅት የነበሩ÷ በጅምሩ ዋዜማ የተቀላቀሉ አባቶች የአባቶቻቸውን አደራ በመቀበል በሚገባ በመፈጸምና ለውጤት በማብቃት የአባቶቻቸውን ስም በደግ ሲያስነሡ÷ ትውልድ በተሠሩ የልማት ሥራዎች እንዲጠቀምና ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግል ሲያደርጉ÷ ትውልዱም በፋንታው ለቀጣዩ ትውልድ የሚሆን ልማት ሲያስብ÷ ሲያቅድ÷ ግንባታ ሲያደርግና ዐረፍተ ዘመን ሲገታው የእርሱ ልጆች አደራውን ተቀብለው ሲያስፈጽሙ ዛሬ ላይ ደርሰናል።

ዛሬ የምንመርቀው ይህ እጅግ ዘመናዊ ዓለም አቀፋዊ ሁለገብ የሰብሰባ ማእከልም በዚህ የቅብብሎሽ ሂደት ውስጥ የተከናወነ የቤተ ክርስቲያናችን አባቶች አርቆ አሳቢነት ውጤት የሆነ÷ ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለሀገር ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጥ ፕሮጀክት ነው።

ወንጌልን በስፋትና በምልአት መሰበክ እንዲቻል የቤተ ክርስቲያኒቱን ክብርና ደረጃ በጠበቀ መልኩ እጅግ ዘመናዊ ሕንጻ መገንባት እንዳለበት በማመን ዕቅዱን የተለሙት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ናቸው። ቅዱስነታቸው ዛሬ ይህ ዘመናዊ ሕንጻ በተገነባበት ነባሩ አዳራሽ ውስጥ ሆነው ዘመናዊ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ መገንባት እንደሚያስፈልግ በተደጋጋሚ ጊዜ የገለጹ ሲሆን፤ በቅዱስ ሲኖዶስ አስወስነው የመሠረት ድንጋይ አኑረው ነበር።

ይሁንና ቅዱስነታቸውን ዐረፍተ ዘመን ቢገታቸውም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወአጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ዘመነ ሢመት በብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅነት÷ በብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሓፊነት ዘመን የግንባታ ፈቃድ ወጥቶ÷ የአፈር ምርመራ ተደርጎና የዲዛይን ሥራ ተከናውኖ እንዳለቀ የሁለቱ ብፁዓን አባቶች የአገልግሎት ጊዜ በመጠናቀቁ ወደ ቁፋሮና ግንባታ ሥራ መግባት ሳይቻል ቀርቷል።

በመቀጠልም ወደ አመራርነት የመጡት ብፁዕ አቡነ ያሬድም አስቀድሞ የተጀመረውን የግንባታ ፈቃድ መነሻ በማድረግ ወደ ሙሉ የሕንጻ ግንባታ ሥራ የተሸጋገሩት በዘመነ ሢመታቸው መጀመሪያ ላይ ተከሥቶ መላ ዓለምን ሲያስጨንቅ የነበረው የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በተገታ ማግሥት ነበር። ብፁዕነታቸው ለዚህ ዘመናዊና ግዙፍ ሕንጻ ግንባታ ልዩ ትኩረት በመስጠት ነባሩን አዳራሽ በፍጥነት በማስፈረስና ጊዜያዊ አዳራሽ በመገንባት ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ የምታከናውነው አጠቃላይ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሳይስተጓጎል አዲሱ ዘመናዊ ግዙፍ ሕንጻ ግንባታ እንዲካሄድ በሳል አመራር በመስጠት ሥራውን አስጀምረው በማስቀጠል አኩሪ ውጤት አስመዝግበው የአገልግሎት ጊዜያቸው ተጠናቋል።

ከብፁዕነታቸው ዘመነ ሢመት በኋላ ወደ

መልእክት

አመራርነት የመጡት ብፁዕ አቡነ አብርሃምም ተጀምሮ በጥሩ አፈጻጸም ደረጃ ላይ ሆኖ የተረከቡትን ይህንን ግዙፍ ሕንጻ ግንባታ በማስቀጠል የተወሰነ የዲዛይን ማሻሻያ በማድረግ በሕንጻው ላይ አምስት መቶ ካሬ ሜትር የሚሸፍን ከአንድ መቶ በላይ ብፁዓን አባቶችን ሊያስተናግድ የሚችል የቅዱስ ሲኖዶስ መሰብሰቢያ አዳራሽ እንዲያካተትበት በማድረግ ግንባታውን አስቀጥለው የበኩላቸውን አሻራ በማኖር ዘመነ ሢመታቸው ተጠናቀቀ።

ብፁዕ አቡነ አብርሃምን ተክተው በጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነት የመጡት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ከቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሓፊ ከብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ጋር በመሆን ከእርሳቸው አስቀድመው የነበሩ ብፁዓን አባቶች ያከናወኗቸውን ሥራዎች መነሻ በማድረግ ግንባታውን ከሚያከናውኑት የሕንጻ ግንባታ ተቋራጮች፥ ከአማካሪ ድርጅቱና ከቤተ ክርስቲያኒቱ መሐንዲሶች ጋር በመመካከር የግንባታ ሥራው በተቻለ ፍጥነት እንዲቀጥል ልዩ ትኩረት በመስጠታቸው እነሆ ይህ ዘመናዊና ግዙፍ ዓለም አቀፍ ሕንጻ ሥራው ተጠናቆ ለምርቃት ሊበቃ ችሏል።

ይህ ዘመናዊና ግዙፍ ሕንጻ በከፍተኛ ፍጥነት፥ በጥራትና በውበት ተጠናቆ ዛሬ ለምርቃት መብቃት የቻለው ከፍ ሲል በመጠኑ እንደተገለጸው ብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ በየጊዜው ግንባታውን በመከታተል ከተቋራጩና ከአማካሪ ድርጅቱ ጋር በመወያየት አቅጣጫ ማስቀመጥ በመቻላቸው እንደሆነ እርግጥ ቢሆንም፤ በግንባታ ሥራው ላይ ይታይ የነበረው መቀዛቀዝና የሥራ መጓተት በመሠረቱ የተፈታውና ግንባታው በሚያስገርም ፍጥነት መከናወን የጀመረው ግን በብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ከፍተኛ ጥረትና ያላሰለሰ ክትትል እንደሆነ ማንም የማይክደው ሐቅ ነው።

ዛሬ ለምርቃት የበቃው ይህ ዓለም አቀፋዊ ጥራትና ውበት የተላበሰ ሕንጻ በሚገባ ተሠርቶ እንዲጠናቀቅ ያደረጉት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ፦ በሕንጻው ዙሪያ በቂ የመኪና ማቆሚያ ሥፍራ እንዲኖር፥ ቅጽረ ግቢው ቤተ ክርስቲያናችንን በሚገልጽ ሥነ ጥበብ እንዲያጌጥ፥ ቅጽሩም በቤተ ክርስቲያን አርማ አጊጦ እንዲቀጸር፥ ምድረ ግቢው ሳቢና ውበትን የተላበሰ እንዲሆን በማድረግ፥ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት የቤተ ክርስቲያንን ክብርና ደረጃ እንዲመጥን በማስቻል በዘመነ ሢመታቸው የላቀ ውጤት በማስመዝገባቸው በታሪክ ሲዘከሩ እንዲኖሩ የሚያስችላቸውን ሥራ ሠርተዋል።

ይህ ግዙፍ ሕንጻ፦ ከ2800 በላይ ተሰብሳቢዎችን የማስተናገድ አቅም ያለው አዳራሽ፥ ሌሎች ዘጠኝ አነስተኛ የስብሰባና የሥልጠና አዳራሾች፥ ከአንድ መቶ በላይ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳትን የሚይዝ የቅዱስ ሲኖዶስ መሰብሰቢያ አዳራሽ፥ ሙዚየምና ዲጂታል ቤተ መጻሕፍት፥ ቢሮዎች፥ ዘመናዊ ሬስቶራንትና በርካታ የመጸዳጃ ክፍሎች አካቶ ይዟል።

ይህ ታላቅ ዓለም አቀፍ የስብሰባ ማእከል በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ አርቆ አሳቢ አእምሮ ተጠንስሶ፥ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ዘመነ ሢመት ተጀምሮ የተጠናቀቀ፤ በብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነት ዘመነ ሢመት፥ በብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሓፊነት ዘመን የግንባታ ፈቃድ ወጥቶለት፥ በብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነት ዘመነ ሢመት፥ በብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሓፊነት ዘመን ለምርቃት የበቃ የቤተ ክርስቲያን የቅብብሎሽ ሥራ ውጤት ማሳያ ፕሮጀክት ነው።

የዚህ ዘመናዊ አዳራሽ ግንባታ በዘመነ ሢመትዎ ተጀምሮ ለምርቃት የበቃው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት እንኳን ደስ አልዎ እንላለን። ሕንጻው ለምርቃት እንዲደርስ ከውጥኑ እስከ ፍጻሜው ድረስ የአመራርነት አሻራችሁን በማሳረፍ ለዚህ ያበቃችሁት ብፁዓን የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጆችም እንኳን ደስ ያላችሁ እንላለን።

የተጀመሩ ሌሎች ፕሮጀክቶችም እንደዚሁ ተጠናቀው ለምርቃት እንዲበቁ የብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ፥ የሸገርና የምዕራብ ሸዋ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሓፊ የራያ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የተናበበ ውጤታማ ሥራን በማድነቅና በማመስገን፤ የሕንጻ ምርቃት መርሐ ግብሩን በማስመልከት ያዘጋጀነውን መጽሔት እንድታነቡና መረጃዎችን እንድታገኙ ስንጋብዝ፤ በብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የተጀመሩ አዳዲስ ፕሮጀክቶች አስቀድሞ የነበሩ የልማት ሥራዎች በቅብብሎሽ ሥራ ውጤታማ እንደሆኑ ሁሉ እነዚህም በቅብብሎሽ ሥራ ውጤታማ እንደሚሆኑ እርግጠኞች በመሆን ነው።

መልካም ንባብ!

ለቀ አየማን እስክንድር ገብረ ክርስቶስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሕዝብ ግንኙነት መምሪያ ዋና ኃላፊና
የቤ/ሕ/አ/ል/ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ

የወቢይ ኮሚቴው መልእክት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ረጅም ዘመናትን በተሻገረው የታሪክ ጉዞዋ ውስጥ የህገርና የሃይማኖት ምሰሶ ሆና ከመቆየቷም በላይ፥ በልማት ረገድም ግንባር ቀደም አርአያ ሆና ትኖራለች። በዚህም መሠረት በ2019 ዓ.ም መጀመሪያ በታሪክ ማኅደር ውስጥ በወርቃማ ፊደላት ከምታስመዘግባቸውና በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዐት ከምታስመርቃቸው ግዙፍና ስልታዊ የልማት ፕሮጀክቶች መካከል "ጽርሐ ተዋሕዶ" ዓለም አቀፍ የስብከተ ወንጌልና የስብሰባ ማእከል አንዱና ዋነኛው ነው።

ይህ ታላቅ ማእከል ቤተ ክርስቲያናችን ያለችበትን ዓለም አቀፋዊ ደረጃና አቅም በሚገባ የሚያንጸባርቅ፥ ዘመናዊ የቴክኖሎጂና የሥነ-ሕንጻ ጥበብን ከአገልግሎት ጋር አዋሕዶ የያዘ ተቋማዊ ሀብት ነው። ይህንን ደረጃውን የጠበቀና በዓለም አቀፍ መድረክ የቤተ ክርስቲያናችንን ክብርና ገጽታ የሚያጎላ ታላቅ የስብከተ ወንጌልና የስብሰባ ማእከል የምረቃ በዓል ደማቅ፥ ታሪካዊና መንፈሳዊ ግርማ ሞገሱን በጠበቀ መልኩ ይከናወን ዘንድ የተቋቋመው የምረቃ በዓል ወቢይ ኮሚቴ የተጣለበትን ታላቅ አደራና ታሪካዊ ኀላፊነት በከፍተኛ የባለቤትነት ስሜት በመቀበል ወደ ሥራ በመግባት ሲንቀሳቀስ ቆይቷል።

መርሐ ግብሩ አስቀድሞ በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳና ግብ መሠረት ስኬታማ ሆኖ እንዲጠናቀቅና የእያንዳንዱ ዘርፍ እንቅስቃሴ ተቀናጅቶ እንዲሄድ ለማድረግ፥ የወቢይ ኮሚቴው አመራሮችና አባላት አጠቃላይ ሂደቱን በበላይነት ከመምራት ባሻገር አስፈላጊ የሆኑ ንኡሳን ኮሚቴዎችን በማዋቀር ሰፊ አደረጃጀት ፈጥረዋል። በዚህም መሠረት የእንግዶችን አቀባበል የሚያስተባብር የመስተንግዶ ኮሚቴ፥ የዝግጅቱን መንፈሳዊና ታሪካዊ መልእክቶች ለሕዝብ የሚያደርስ የሥነ ጽሑፍ፥ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ኮሚቴ፥ እንዲሁም የሥነ ሥርዐቱን ፍሰትና የክብረ ወሰን ደንቦችን የሚጠብቅ የፕሮቶኮልና የሥነ-ሥርዐት ኮሚቴ ተዋቅረው ወደ ሙሉ ሥራ ገብተዋል። እነዚህ ንኡሳን ኮሚቴዎች የተሰጣቸውን የሥራ ድርሻና ኀላፊነት በከፍተኛ ትጋት፥ በሙሉ ቅንጅትና ሙያዊ ብቃት በመወጣታቸው፥ የዝግጅቱ እቅድ ከወረቀት አልፎ መሬት እንዲወርድና የምረቃ መርሐ ግብሩ በታላቅ ስኬት እንዲከናወን ለማድረግ አስችለዋል።

ቤተ ክርስቲያናችን በተለይም በብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ፥ የደቡብ ምዕራብ ሸዋና የሸገር አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፥ በብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሓፊና የራያ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ወደ ተቋማዊ አመራርነት ከመጡ ወዲህ አዳዲስ የልማት፥ የአስተዳደርና የተቋማዊ ማሻሻያ አቅጣጫዎችን በመከተል ላይ ትገኛለች።

ብፁዓን አባቶቻችን ክብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወአጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት አባታዊ መመሪያና ቡራኬ በመቀበል፥ የተቋሙን ሁለገብ አድገት የሚያፋጥኑ፥ ገቢውን የሚያሳድጉና መዋቅራዊ አቅሙን የሚያጠናክሩ ጉዳዮችን በቋሚ ሲኖዶስ በማስወሰንና በተግባር በመተርጐም ረገድ አርአያነት ያለው ታላቅ ተግባር ሲያከናውኑ ቆይተዋል።

ዛሬ በጠቅላይ ቤተ ክህነታችን ቅጽር ግቢ ውስጥ ለምረቃ የበቃው ይህ ዓለም አቀፋዊ የስብከተ ወንጌልና የስብሰባ ማእከልና በተለምዶ "አሮጌው ቄራ" እየተባለ በሚጠራው አካባቢ የተገነባው ሁለገብ ሕንጻ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ ለዚህ መዓርግ መብቃቱ የአባቶቻችንን አርቆ አስተዋይ አመራር፥ ቁርጠኝነት፥ ታማኝነትና ስኬታማነት በግልጽ የሚያረጋግጥ ነው።

በመሆኑም ወቢይ ኮሚቴው ቤተ ክርስቲያናችን ይህን የመሰለ ዓለም አቀፋዊ ይዘትና ደረጃ ያለው የስብሰባ አዳራሽ ገንብታ ለምርቃት ማብቃቷን ተከትሎ፥ የዚህ ታሪካዊ ክስተትና የማይጠፋ አሻራ አካል ለመሆን በመቻሉ የተሰማውን ጥልቅ ደስታ ይገልጻል።

ኮሚቴው ለብፁዕ ወቅዱስ አባታችንና ለሁለቱ ብፁዓን አባቶቻችን ያለውን የላቀ አድናቆትና ክብር እየገለጸ "እንኳን ደስ አላችሁ፤ እንኳን ደስ አለን!" ለማለት ይወዳል። አሁንም ይሁን ወደፊት በቤተ ክርስቲያናችን የሚሰጡ ማንኛቸውንም ተመሳሳይ ታላላቅ ኀላፊነቶችና አገልግሎቶች በከፍተኛ ታማኝነትና ትጋት ለመወጣት ሁል ጊዜም ዝግጁ መሆኑንም ያረጋግጣል።

በመጨረሻም፥ የቤተ ክርስቲያናችን ክብር፥ ልዕልናና ግርማ ሞገስ በጉልህ የተገለጠበት ይህ "ጽርሐ ተዋሕዶ" ዓለም አቀፍ የስብከተ ወንጌልና የስብሰባ አዳራሽ ባማረና በተዋበ መልኩ ተሠርቶ እንዲጠናቀቅና የምረቃ መርሐ ግብሩ በታላቅ ድምቀት እንዲከናወን በገንዘባቸው፥ በሐሳባቸው፥ በቀኖቀኖስ ድጋፋቸው፥ በሙያዊ ዕውቀታቸውና በጉልበታቸው ያልተቆጠበ አስተዋፅኦ ላደረጋችሁ ምእመናን፥ ባለሙያዎችና አጋር አካላት ሁሉ ወቢይ ኮሚቴው በቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ስም ላቅ ያለ ምስጋናውንና አክብሮቱን ያቀርባል።

እንኳን ደስ አላችሁ፤ እንኳን ደስ አለን!



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአኩስም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

መልእክተ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ



በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ አሜን።

«ወዘሰ ጸንዐ ወቆመ ምግባረ ውእቱኬ ዘይነሥእ ዕሴቶ ፥ ሥራው ጸንቶ የተገኘለት ሰው ዋጋውን የሚቀበል እርሱ ነው።»

(1ኛ ቆሮንቶስ 3፥14)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በጻፈው መልእክቱ በሐዋርያዊ ተልእኮ ውስጥ በትምህርተ ሃይማኖት የመትከል፥ በሥርዓት የመምራት፥ በፍቅር የመንከባከብ ልዩ ልዩ ጸጋ ያላቸው ሥዩማን ሲኖሩ፤ የሥራው ባለቤት ግን እግዚአብሔር መሆኑን በሕንጻ ግንባታ እየመሰለ ሲያስተምር፤ በነቢያት፥ በሐዋርያትና በሊቃውንት ትምህርት በተገለጠው የክርስቶስ መሠረትነት ላይ ውሉደ ክህነት አገልግሎታቸውን በታላቅ ጥንቃቄ ማከናወን እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባል።

የተጀመረ ሥራ ከፍጻሜ ሲደርስ ከውጥኑ አንሥቶ የመሳተፍ ዕድል የገጠማቸው ሰዎች በልቡናቸው ጥልቅ ስሜት ሊፈጠር እንደሚችል እሙን ነው። እኛም ዛሬ ባርከን አገልግሎት የምናስጀምረው የቅዱስ ሲኖዶስ፥ የስብከተ ወንጌልና ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤያትን ዘመኑን በዋጀ መልኩ ለማካሄድ የሚያስችሉ አዳራሾች የተካተቱበት ግዙፍ ሕንጻ ዋጋው የሚመዘነው በተሠራበት ቁሳቁስ ብቻ ሳይሆን በተገነባበት ዓላማ ጭምር ነውና፤ የቦታ አጠቃቀምንና ማራኪ ሥነ ሕንጻን በማዋሐድ ተገንብቶ የቤተ ክርስቲያናችን ሐዋርያዊ አገልግሎት በሚፈለገው ልክ የሚጠናከርበትና ለቀጣዩ ትውልድም የምናቆየው ዘመን ተሻጋሪ ሀብት እንደሆነ በመረዳት ከፍ ያለ መንፈሳዊ ደስታ ይሰማናል።

የተወደዳችሁ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻችን!

የዚህ ሕንጻ ግንባታ ሐሳብ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፮ኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ መዋዕለ ሕይወት ተነሥቶ የነበረ ቢሆንም፤ ፈቃደ አምላክ ተጨምሮበት ዕቅዱን የማደራጀትና የግንባታ ተግባሩ በዘመነ ክህነታችን ተጀምሮ መጠናቀቁ የታሪካችን አንድ ክፍል ሆኖ እንዲታወስ ስለሚያደርገው ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ምስጋናችንን እናቀርባለን።

ዓመታትን በወሰደው የሥራ ሂደትም ብዙዎች በዕውቀታቸው፥ በጉልበታቸው፥ በሓላፊነታቸውና በትጋታቸው የየራሳቸውን አሻራ በማሳረፋቸው የዛሬው ምሉእ ውጤት የተገኘው በእነዚህ ባለ ድርሻዎች ጥረት ሲሆን፤ በተለይም የግንባታው ንድፍ ይፋ ከተደረገበት ጊዜ አንሥቶ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ እየተመደቡ በጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነትና በቅዱስ ሲኖዶስ ጸሓፊነት ያገለገሉ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት የዚህ ወርቃማ ታሪክ አካል ከመሆናቸውም ባሻገር፤ በልዩ ጥራት ተጠናቆ ለምርቃት ይደርስ ዘንድ አሁን በሥራ ላይ የሚገኙት ብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅና ብፁዕ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ፥ እንዲሁም በየደረጃው የሚገኙ የቤተ ክርስቲያኒቱ የሥራ ሓላፊዎች የነበራቸው ሚና የጎላ በመሆኑ፤ ሁሉንም የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻችንን እንኳን ለዚህ ዕለት አደረሳችሁ! እንኳንም የድካማችሁን ፍሬ ለማየት አበቃችሁ! ለማለት እንወዳለን።

የተወደዳችሁ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻችን!

ዛሬ ይህንን ሕንጻ በምንመርቅበት ቅጽበት በመላው ዓለምና በሀገራችን መዓዝናት በረሀብ፥ በጦርነት፥ በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ሕይወታቸውን የሚያጡ፤ ከኖሩበት ቀዬም የሚፈናቀሉ ብዙዎች ናቸውና፤ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በዚህ ዘመን ከምንጊዜውም በላይ በእውነት፥ በፍቅር፥ በመተማመንና በመንፈሳዊ ሕብረት ላይ ተመሥርቶ፤ የተጨነቁትን የሰው ልጆች ተስፋቸው ስለሚለመልምበት ሁኔታ ማሰብ እንደሚገባ በዚሁ አጋጣሚ እናስታውሳለን።

በመጨረሻም በአዲሱ ጽርሐ ተዋሕዶ የሚደረጉ ጉባኤያት ሃይማኖትን ለማጽናት፥ ለቤተ ክርስቲያን አንድነት፥ ለሕዝባችን ደኅንነትና ለሀገር ሰላም አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ፥ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ከነሙሉ ክብሩ ለትውልድ የሚሸጋገርባቸው ሊሆኑ ይገባል እያልን አባታዊ የአደራ መልእክታችንን በእግዚአብሔር ስም እናስተላልፋለን።

እግዚአብሔር አምላክ

ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን

ይባርክ!

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፤

አሜን።

አባ ማትያስ ቀዳማዊ

ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

ሊቀ ጳጳስ ዘአኩስም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

መስከረም ፴ ቀን ፭፻፲፱ ዓ.ም.

አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ

“መይኤይስ ትርሢቱ ለዝንቱ ቤት ደኃሪ እምቀዳሚ ÷ የዚህ የኋለኛው ቤት ክብር ከፊተኛው ይልቅ ይበልጣል” (ሐጌ 2÷9)።



የብፁዕ ጠቅላይ ዋና ሥራ አስኪያጅ መልእክት

በቅድሚያ ከብዙ ጥረትና ድካም በኋላ ይህን ታሪካዊ ስኬት ለማየት ያበቃን እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ለእርሱ ይሁን።

በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ውስጥ ታላቅ የመንፈስ መነቃቃትንና ተቋማዊ ዕድገትን የሚያበሥር አዲስ ምዕራፍ በሚከፈትበት ለዚህ ታላቅ ዕለትና ለአዲሱ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ሁለገብ አዳራሽ ምረቃ በዓል እንኳን በሰላም አደረሳችሁ።

ዛሬ የምናስመርቀውን ይህን ግዙፍ ማዕከል ከቁሳዊ ስኬት በላይ ከፍ አድርገን ብንመለከተው÷ የሃይማኖታችን ጽናት፣ የሕብረታችን ፍሬ፣ የጸሎታችን መልስና የእግዚአብሔር ታማኝነት ሕያው ምስክር ነው። ነቢዩ ሐጌ÷ «የዚህ የኋለኛው ቤት ክብር ከፊተኛው ይልቅ ይበልጣል÷ ይላል እግዚአብሔር የሠራዊት አምላክ፤ በዚህም ስፍራ ሰላምን እሰጣለሁ» (ሐጌ 2÷9) ብሎ እንደተናገረው፤ ይህ አዳራሽ ከቀደሙት ይልቅ የቤተ ክርስቲያናችንን የአገልግሎት አቅም ወደ ታላቅ ደረጃና ክብር የሚያሸጋግር፣ የወንጌል ሰላምና አውነት ለትውልድ የሚታወጅበት አዲስና ደረጃውን የጠበቀ መድረክ ነው።

ቤተ ክርስቲያናችን በረጅም ዘመናት ታሪኳ ውስጥ ታላላቅ በዓላትና መንፈሳዊ ኩነቶችዋ በጊዜው በነበሩ አነስተኛና ዝቅተኛ

መልእክት

ደረጃ በነበራቸው መሰብሰቢያዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል። የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት መምሪያዎች የሚያዘጋጇቸው መርሐ ግብራትም ሌሎች ተቋማትን ደጅ መጥናትና ለከፍተኛ ወጪ መዳረግ የተለመደ ነበር። ከዚህም በላይ ቤተ ክርስቲያናችን ባሏት ትምህርታዊ ሀብታትና በስመ ጥር ሊቃውንት ጸጋ ላይ ተመሥርታ ታላላቅ ጉባዔያትን ለማድረግ እንዳትችል በቦታ ውሱንነት ተገድባ ቆይታለች። ዛሬ የምናስመርቀው ይህ ሕንጻ እነዚህን ሁኔታዎች የመቀየር ታላቅ አቅም አለው። በእነዚህና በሌሎችም ተያያዥ ምክንያቶች የሕንጻው መጠናቀቅና ለምረቃ መብቃት እንደ ታሪክ ቀያሪ ክስተት በቆጠር ተገቢ ነው።

ሥራዎችን በተገቢው መንገድ ዐቅዶና ትግበራውን ተከታትሎ ለፍጻሜ ማብቃት ትልቅ ስኬት ነው። ይሁን እንጂ ነገሮች በታሰቡበት ልክ የማይሄዱበትና ያልታሰቡ ጉዳዮች የሚከሰቱበት አጋጣሚም ብዙ ነው። ይህ ሕንጻ ለመጠናቀቅ ታቅዶለት የነበረው የመጀመሪያ የጊዜ ሰሌዳ አልፎ፣ ለረጅም ጊዜ መስተጓጎል ገጥሞት እንደነበረ ግልጽ ነው። በመሆኑም የተጀመሩ ሥራዎችን ተከታትሎ ማስፈጸም በሚለው አንደኛው የተግባራዊ እንቅስቃሴያችን አካል ሊሆን በመቻሉ÷ የተገኙ ለውጦች ለዚህ ሊያበቁት ችለዋል። የዚህ ሕንጻ ግንባታ መጠናቀቅና ይህን በመሰለ መልኩ ፕሮጀክቱን ተከታትሎ ማስፈጸም መቻል ቤተ ክርስቲያናችን የያዘቻቸውን ቀጣይ የልማት ዕቅዶች መፈጸም ስለመቻልዋ የሚፈጥሩት እርግጠኝነት በቀላሉ አይታይም። አሁንም ቀጣይ ታላላቅ ፕሮጀክቶች ይህን ቁርጠኝነት እየጠየቁን ስላሉ ይህኛው ስኬታችን ታላቅ የሥነ ልቡና ብርታት ይፈጥርልናል።

ይህንን ታላቅ ሕንጻ ለማጠናቀቅ ያቀድነው ዕቅድ እውን የሆነው በቅድሚያ በእግዚአብሔር መልካም ፈቃድና ረድኤት ነው። ነቢዩ ኢሳይያስ÷ «እለሰ ይሴፈውዎ ወይትዔገሥዎ ለእግዚአብሔር ይሔድሱ ኀይሎሙ ወይበሥሉ ክነፊሆሙ፣ ከመ ንስር ይረውጹ፣ ወኢይደክሙ የሐውሩ ወኢይርኅቡ ÷ እግዚአብሔርን የሚታመኑ ግን ኀይላቸውን ያድሳሉ፤ እንደ ንሥር በክንፍ ይወጣሉ፤ ይሮጣሉ አይታክቱም፤ ይሄዳሉ አይደክሙም» (ኢሳ. 40÷31) እንዳለው፣ እኛም በሂደቱ ያጋጠሙንን ፈተናዎች በሙሉ በእግዚአብሔር ታምነንና ተስፋችንን በእርሱ ላይ አድርገን አልፈናል።

ይህ ሁለገብ አዳራሽ ሲጀመር የነበረውን ፈታኝ ሁኔታ፣ ያለፈበትን ረጅም መንገድና እስከዚች ሰዓት ድረስ የተከፈለውን ሁለንተናዊ ዋጋ ስናስብ፣ የእግዚአብሔር እጅ በሕይወታችንና በቤተ ክርስቲያናችን ላይ እንዴት አድርጎ ሲሠራ እንደነበር በግልጽ እንረዳለን። በግንባታው ሂደት ውስጥ ያጋጠሙን የፋይናንስ፣ የቴክኒክና የልዩ ልዩ ፈተና ማዕበላት ቀላል አልነበሩም። ነገር ግን የያዝነው ዓላማ የወንጌልን እውነት ከማስፋፋትና ቤተ ክርስቲያንን በሁለንተናዊ መልኩ ከማጠናከር ጋር የተያያዘ አደራ በመሆኑ በጽናት ቀጥለናል።

ታላቁ አባት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለ ስደቱ በተናገረበት ድርሳኑ÷ «ብዙዎች ቤተ ክርስቲያንን ሊያሸንፏት ሞከሩ፣ እርሷ ግን ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ አለች። የቤተ ክርስቲያን ታላቅነቷ ሲነሡባት ስታሸንፍ፣ ስሟን ሲያጠፋ እንደ ፀሐይ ስታበራ፣ ማዕበል ሲመታት ሳትሰጥም የምትገኝ መርከብ በመሆኗ የሚገለጽ ነው» እንዳለው ሁሉ፣ እኛም በመንፈስ ቅዱስ መሪነትና በአባቶቻችን ጸሎት ፈተናዎችን ሁሉ አልፈን ዛሬ ለዚህ ታላቅ ክብርና የምረቃ በዓል በቅተናል።

ዛሬ የምናስመርቀው ይህ ግዙፍ ማዕከል ለቤተ ክርስቲያናችን አገልግሎት ዘመናዊና ሁለገብ የሆነ ታላቅ ተቋማዊ ዐቅም የሚፈጥር ነው። ይህ ስፍራ የቅዱስ ሲኖዶስና የዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ማካሄጃ፣ የታላላቅ ዓለም አቀፍ ጉባኤያት መድረክ፣ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያናችንን ታላቅነት የሚያንጸባርቁ መንፈሳዊ በዓላት በልዩ ሁኔታ የሚከበሩበት አዳራሽ ነው። ጌታችን በወንጌል÷ «በጨለማ የምነግራችሁን በብርሃን ተናገሩ፤ በጆሮአችሁም የምትሰሙትን በሰገነት ላይ ስበኩ» (ማቴ. 10÷27) በማለት የሰጠንን ታላቅ አደራ በብቃት ለመወጣት፣ እንደዚህ ያሉ ዘመናዊና ሰፋፊ ሁለገብ አዳራሾች አስፈላጊነታቸው የጎላ ነው። ይህ አዲስ አዳራሽ የወንጌል ትምህርት በስፋት የሚሰጥበት፣ የትውልዱ መንፈሳዊ ጥያቄዎች በሊቃውንት ትምህርት የሚመለሱበት ታላቅ የማእከልነት ሚና ይጫወታል።

ይህ ሕንጻ በርካታ ውጣውረዶችን አልፎ ለዚህ እንዲበቃ ከፍተኛ ጥረት ያደረጋችሁ ሁሉ፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ÷ «እንግዲህ ወንድሞቼ ሆይ፣ ድካማችሁ በእግዚአብሔር ዘንድ ከንቱ እንዳይሆን አውቃችኋልና የምትደላደሉ፣ የማትናወጡም፣ የጌታም ሥራ ሁል ጊዜ የሚበዛላችሁ ሁኑ» (1ቆሮ. 15÷58) በማለት ያስተማረው ቃል ዛሬ በእናንተ ትጋት ፍሬ አፍርቶ ይታያል። በዚህ ታላቅ የምረቃ ዕለት፣ ይህ ሕንጻ እውን እንዲሆን የተከፈለውን ዋጋ ስናስብ፣ በየደረጃው አስተዋፅኦ ያደረጋችሁትን ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ስም ልናመሰግናችሁ እንወዳለን። ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ «በእግዚአብሔር ላይ ያለን እምነትና ተስፋ ፈጽሞ አያሳፍርም» እንዳለው፣ እኛም በፈተናዎች መካከል ተስፋ ሳንቆርጥ የያዝነውን በጎ ሥራ ፈጽመን ለመመረቅ በመብቃታችን አምላካችንን እናመሰግናለን።

በመጨረሻም፣ ይህን አዲስና ሁለገብ አዳራሽ እየመረቅን ባለንበት ጊዜ የቅድስና፣ የታማኝነትና የትጋት መንፈሳችን አዲስ እንዲሆን አደራ ለማለት እወዳለሁ። ከወትሮው በላቀ ሁኔታ የሥራ ተነሣሽነታችን እንዲጨምር፣ ኅብረታችን እንዲጸናና ለጋራ ዓላማ እንድንሰለፍም ጥሪዬን አስተላልፋለሁ። «ለእግዚአብሔር የምታደርጉትን ሁሉ በትጋትና በቅንነት አድርጉት» (ቈላ. 3÷23) የሚለው የሐዋርያው ማሳሰቢያ የዘወትር መመሪያችን ሊሆን ይገባል።

ይህ ሕንጻ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መገለጫ ግርማ፣ ለወንጌል ብርሃን መፍለቂያ ማእከል፣ ለአምላካችንም ክብር ምስጋና ማቅረቢያ እንዲሆንልን እመኛለሁ። የቅዱሳን አባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያናችንን ይጠብቅ፣ ቀሪ ሥራዎቻችንን ሁሉ ይባርክ። ሀገራችንን በሰላም÷ በፍቅርና በአንድነት ያጽናልን።

መልካም የምረቃ በዓል!

አባ ሳዊሮስ

የመንበረ ፓትያርክ ጠቅላዩ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ
የደቡብ ምዕራብ ሸዋና የሸገር ከተማ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

ወይሔይስ ትርሲቱ ለዝንቱ ቤት ዘደኃሪ እምዘቀዳሚ ÷ ከፊተኛው ይልቅ የዚህ የሁለተኛው ቤት ክብር ይበልጣል"

ሐጌ 2÷9



የብፁዕ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሓፊ መልእክት

ከሁሉ አስቀድመን የክብር ሁሉ ባለቤትና የዘመናት ጌታ ያለፈውን ዓመት በክብር ሸኝተን ዐዲሱን ዓመት በማይልፍ ሰማያዊ ሀብቱ፣ በማይወሰን ምኅረቱ እንድንቀበል፤ የጀመርነውን የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽርሐ ተዋሕዶ ሁለገብ ሕንፃ አጠናቀን እርሱን በማመስገን እንድንመርቅ ላበቃን ልውል እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይሁን እያልን ሁላችንንም እንኳን በሰላም አደረሰን እንላለን።

ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት "እመ እግዚአብሔር ኢሐነጸ ቤተ ከንቶ ይጸምው እለ የሐንጹ - እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ÷ ሠራተኞቹ በከንቱ ይደክማሉ።" እንዲል የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ከልሐቅ እስከ ደቂቅ የሚሰበሰቡበት፣ የሚማሩበት፣ በኅብረት የሚያገለግሉበት፣ የቤተ ክርስቲያናችን ክብር የሚገለጥበት፣ የወንጌል ቃል የሚታወጅበት፣ ያለፈውን በጋራ ሰምተን የወደፊቱን የምናቅድበት፣ ዓለም አቀፍ ጉባኤያትን የምናከናውንበትና ሁለገብ አገልግሎትን የምንሰጥበት የዚህ ታላቅ ሕንፃ ግንባታ እግዚአብሔር ባያግዘን በእኛ አቅም የሚቻልና የሚፈጸም አልነበረም። ስለሆነም ወሀቤ ጸጋ ለሆነው አምላካችን ከፍ ያለ ምስጋናችንን እናቀርባለን። (መዝሙር 127÷1)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ "እርስ በርሳችን ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እንድንነቃቃ እንተያይ፤ መሰብሰባችንንም እንደ አንዳንዶች ልማድ አንተው።" ብሎ እንደጻፈ ይህ አዳራሽ እርስ በርሳችን የምንበረታታበት፣ እምነታችንን የምናጠናክርበት፣ ፍቅርንና ኅብረትን የምንገነባበት፣ ስንቸገር ለመፍትሔ የምንሰባሰብበት፣ አበይተ ቤተ ክርስቲያን ጥበባቸውንና ልምዳቸውን ለቀጣዩ ትውልድ የሚያካፍሉበት፣ ውሉደ አበው ወጣቶች የሚማሩበት ሆኖ በመጠናቀቁ ሁላችንም

ደስ ብሎናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “ሁለት ወይም ሦስት ሁናችሁ በስሜ በምትሰበሰቡበት እኔ በመካከላቸው እኖራለሁ” ብሎ ቃል ኪዳንን ስለሰጠን ጽርሐ ተዋሕዶ በአንድ አማናዊ ልብ በመሰብሰብ ውይይቶቻችን በአክብሮት፣ ውሳኔዎቻችን በጥበብ፣ ልዩነቶችን በፍቅርና ተልእኮአችንን በታማኝነትና በመፈጸም መንፈሳዊና ማኅበራዊ ፍሬ የምናቀርብበት ረድኤተ እግዚአብሔር የሚገኝበት ወሳኝ ስፍራ ነው። (ማቴ 18÷20፣ ዕብ 10÷24)

በርግጥ አንድ ሕንፃ ትርጉም የሚኖረው በግድግዳው፣ በጣሪያው ወይም በውበቱ ብቻ ሳይሆን በሚሰጠው አገልግሎት፣ በሚቀርቡ ዕሴቶችና በሚፈጸሙ መልካም ሥራዎች ነው። ነቢዩ ሐጌ 2÷9 ላይ፦ “የዚህ የኋለኛው ቤት ክብር ከፊተኛው ቤት ክብር ይበልጣል” ሲል ነባሩንና የቀደመውን የወደደና የባረከ አምላክ፤ ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛውን ወድጃለሁ በማለት ቃል ኪዳኑ እንዳተቋረጠና ከእኛም እንዳልተለየ አረጋግጦልናል። በቀደመው ሕንፃ ውስጥ ለብዙ ዐሥርት ዓመታት አያሌ አገልግሎቶችን ከሰበካ ጉባኤ ጀምሮ ስብከተ ወንጌልን፣ የወጣቶች ተሳትፎ፣ የአበውን ዝክርና ክብር፣ የዘመናት ዐውደ ርእይና በርካታ የቤተ ክርስቲያንን ተልዕኮ ያለማቋረጥ ፈጽመንበት ነበር። አሁን ደግሞ በዚያ ላይ ተመሥርተን እግጅ ውብና ሰፊ፣ ጠንካራና ሁሉን አሳታፊ አዲስ ሕንፃ ተሠርቶ ለምረቃ በቅቷል።

ዛሬ የምንመርቀው ሕንፃ ከባለፈው ሕንፃ በሁለንተናው ይበልጣል፡ ፡ በትልቅነቱ፣ በሚይዘው የሰው አቅም፣ በሚሰጠው የአገልግሎት ስፋት፣ በማራኪነቱና በውበቱ በሁሉ የላቀ ነው። ይኸንን ሁሉም አይቶ የሚመሰክረው ሐቅ ነው። ከቀድሞው በብዙ እጥፍ የበለጠ እንዲሆንም በአዲሱ አዳራሽ የሚቀርበው አገልግሎት ትልቅ ሊሆኑ የሚገባ ሲሆን እነርሱም ፍቅርና እምነት፣ መተባበርና ኅብረት፣ ጥበብና ትጋት፣ አንድነትና የተቃና አገልግሎት የመሳሰሉት ናቸው። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ “እናንተም እንደ ሕያዋን ድንጋዮች መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ።” ብሎ የሰጠን መመሪያ ለዛሬው የምረቃ በዓል ትልቅ ትርጉም አለው። ጽርሐ ተዋሕዶ ብዙ ሰዎችን በአካልና በአእምሮ እንዲያሰባስብ ተገንብቷል፤ እንደዚሁም ሁሉ የእኛ ማንነት በማይጠፋውና በማያረጀው በክርስቶስ የተገነባ ሕያው ማኅበረሰብ መሆን አለብን። ጽርሐ ተዋሕዶ አሁን ስናየው እጅግ የሚያምር፣ በብዙ ድካምና ጥበብ የተሠራ ምድራዊ ሲሆን በሚያረጀው ሕንፃ ውስጥ የማይፈርስውንና የማያረጀውን በሁለንተናችን የከበረ እና የደመቀ ማንነት፣ ያማረ አንድነትን የምንሠራበት በመሆኑ ሰማያዊ ክብርን እንድንገነባ ያግዘናል። (1ኛ ጴጥሮስ 2÷5)

እንደሚታወቀው እግዚአብሔር የሚመሰገንበትና የሚከብርበት ሕንፃ ከምድራዊ ጥሬ ዕቃዎች ብቻ ሳይሆን በሰዎች እምነትና ቅድስና፣ ፍቅርና ንጽሕና፣ ጥበብና መንፈሳዊነት ይገባል። እንደ ሕንፃው ሁሉ እኛ እርስ በርሳችን ጠንካራ አንድነት፣ ኅብረትና መከባበር ያስፈልገናል። ስለዚህ ዛሬ ይህን አዳራሽ ስናስመርቅ “እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ፣ ይህን ሕንፃ እንደገነባን ልባችንንም ገንባ፤ የዚህ ታላቅ ሕንፃ ግድግዳውን እንዳቆምን ተስፋቸችንንና አንድነታችንንም በጽኑ መሠረት ላይ አጽንተህ አቁምልን፤ በአስደናቂ አፈጻጸም ጣሪያውን እንደከደን ምሕረትህን በላያችን ፍቅርህን በውስጣችን አኑርልን፤ በዚህ ሕንፃ ውስጥ የሚሰበከው ስብከት፣ የሚቀርበው ስብሐት፣ የምናደርገው ምክክርና የምንፈጽመው ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ መርሐ ግብር ሁሉ ያማረና የሰመረ አድርግልን” እያልን በአንድነት ልንጸልይ ይገባናል።

ጽርሐ ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ዘመኑን በሚመጥን፣ ትውልድን በሚዋጅ፣ ዓለም አቀፍ ደረጃዋን በሚጠብቅ ለታላቋ ቤተ ክርስቲያን ቀጣይ ቁመና መሠረት የሚጥል፣ ለወደፊቱ ሐዋርያዊ ተልእኮ ወሳኝ ምዕራፍ የሚከፍት ለቀጣዩ ትውልድ የሚወረስ ቅርስ ነው። ቅርስነቱ የሕንፃ ሀብት ብቻ ሳይሆን የመንፈሳዊ አገልግሎትና ጠንካራ የአምነት ምስክር፣ ለቤተ ክርስቲያን ዋጋ ለመክፈል ያለንን ቁርጠኝነት ማሳያ ምስክር ነው። ስለሆነም ሕንፃውን ስንመርቅ አደራ የምንቀበልበትም አደራ የምናወርስበት እለት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ “በአዳራሽ ውስጥ መሰብሰብ ቀላል ነው፤ በፍቅር አንድ ሆኖ መኖር ግን እውነተኛው ምስክርነት ነው።” እንዳለው እውነተኛ ምስክርነት የምናቀርብበት እንዲሆን ቃል የምንገባበትና ለቀጣዩ ትውልድ መልካም የሆነ የትጋት ምሳሌና ጅምርን የመጨረስ አርአያንና አደራን የምንተውበት የምረቃ ቀን ነው።

ከፊተኛው አዳራሽ ይልቅ ሁለተኛው አዳራሽ እንደሚበልጥ ሁሉ ካለፈው ይልቅ የወደፊቱ ተልእኮአችን የበለጠ የሰመረ፣ ከዘመኑ ጥበብ እጅግ የከበረ፣ የላቀና የታፈረ ያድርግልን እያልን ግንባታው እንዲጠናቀቅ ከቅዱስ ሲኖዶስና ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ጀምሮ የሚመለከታቸው ባለሙያዎችና የሥራ ኃፊዎች ሁሉ ተገቢውን ጥረት በማድረጋቸው ልናመሰግናቸው ይገባናል። እንደሚታወቀው የሕንፃው ሥራ የታቀደውና የመሠረት ድንጋይ የተቀመጠው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ (ዶ/ር) አምስተኛው ፓትርያርክ ዘመን ነበር፡ ፡ የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ሆኖ እኔና ብፁዕ ወንድሜ አቡነ ሳዊሮስ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጠቅላይ ዋና ሥራ አስኪያጅ የደቡብ ምዕራብ ሸዋና የሸገር ከተማ ሊቀ ጳጳስ በአንድነት አስጀምረን፣ በመካከል ብፁዕ አቡነ ያሬድ ሊቀ ጳጳስና ብፁዕ አቡነ አብርሃም ሊቀ ጳጳስ በጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነት የሥራ ዘመናቸው የበኩላቸውን ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተው አሁንም በታሪክ አጋጣሚ እኛው አንዳስጀመርነው ለማስመረቅ በመብቃታችን አምላካችንን እናመሰግነዋለን።

በተለይም ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ተጀምሮ የነበረውን አዳራሽ ከመፈጸም በተጨማሪ በአጭር ጊዜ ውስጥ በመንበረ ፓትርያርክ ግቢ ያከናወኗቸው ትውልድ ተሸጋሪ የግንባታና የማስዋብ ሥራዎች፣ አደረጃጀቱን ለመንፈሳዊ፣ ለማኅበራዊና ለአስተዳደር ሥራ ብቁና ደረጃውን የጠበቀ በማድረግ፣ ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ጋር በቅርበት በመወያየት ያለአግባብ ተወስዶ የነበረውን የመንበረ ፓትርያርክ ጠ/ቤ/ክ/ ግቢ ይዞታ በአስተዳደራዊ ጥበብ በማስመለስ፣ ክፍት በሆኑ የቤተ ክርስቲያን ይዞታዎች ላይ ታላላቅ የሕንፃ ግንባታዎችን በማስጀመር፣ ተጀምረው የነበሩት በፍጥነት እንዲጠናቀቁ በማስቻል፣ በጠቅላይ ጽ/ቤቱ ከአድዓኦ የጸዳ መልካም አስተዳደርና ዘመናዊ አሠራር እንደሰፍን ቀን ከሌሊት ያለእረፍት የሚያደርጉት ጥረት አርአያነት ያለው በትውልድ የማይረሳ ታሪካዊና ሐዋርያዊ ተግባር በመሆኑ ከፍ ያለ የተለየ ክብርና ዕውቅና ሊሰጠው ይገባል። እግዚአብሔር አምላካችን ሥራችንን ለበረከት ያድርግን አገልግሎታችን ይቀበልልን፣ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን እና ሀገራችን ኢትዮጵያን ይጠብቅልን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

አባ ዲዮስቆሮስ

የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊና የሪያ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ



የመንፈሳዊ ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ መልእክት

በስመ እግዚአብሔር ሥሉስ ዘኢይትበዓድ በክዋኔ!

“ይትፌሣሕ እግዚአብሔር በተግባሩ፤ እግዚአብሔር በሥራው ይደሰታል።”
(መዝ.103÷31)

በሰማይም ሆነ በምድር ያለው፥ የሚታየውም ሆነ የማይታየው ፍጥረተ ዓለም ሁሉ በአጠቃላይ የሥራ ውጤት ነው። ታላቁ መጽሐፍ በስድስቱ ዕለታት የተፈጠሩ ፍጥረታትን በገለጸበት ስፍራ ሁሉ፥ የሥራው ባለቤት የሆነ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ውበት መደሰቱን ሲገልጽ፦ ‹‹መልካም እንደሆነ አየ›› በማለት ይገልጸዋል። (ዘፍ.1÷4)

መልእክት

ዛሬ በዓለማችን የሚታዩ ድንቃድንቅ ነገሮች በሙሉ የሥራ ውጤቶች ናቸው፤ ሰውም ደስተኛ የሚሆነው ሠርቶ በሚያገኘው ውጤት ነው፤ ገበሬ አርሶ በሚያፍሰው ምርት፥ ነጋዴ ነግዶ በሚያገኘው ትርፍ፥ ተማሪ ተምሮና አጥንቶ በሚያገኘው ማርክ ይደሰታል። የቤተ ክርስቲያን ላእካንም ወንጌልን አስተምረው በሚያሳምኑትና በሚያድኑት ምእመን መንፈሳቸው ትደሰታለች። «ወአነሂ እትፌሣሕ በእንቲአኪ፤ እስመ ረከብኩ እምውስተ ደቂቅኪ እለ የሓውሩ በትእዛዘየ፤ እኄም ካንቺ የተነሣ እደሰታለሁ፤ ከልጆችሽ ወገን በትእዛዜ የሚሄዱ አግኝቻለሁና» የሚለው ቃሉም ይህንን ያረጋግጣል፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ ከሥራ ሁሉ የበለጠ ሥራ ነው። ምክንያቱም ሥራን መሥራት ትልቁ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነውና። (ዘፍ. 2÷15)

በዛሬው ዕለት የተመረቀው ግዙፉ የቤተ ክርስቲያናችን የሁለገብ አገልግሎት መስጫ አዳራሽ የቤተ ክርስቲያናችን የሥራ ውጤት ነው፤ ሕንጻው ሰባ ሚሊዮን የሚሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን አሻራ ያረፈበት ነው፤ ንብረትነቱም በዚያው መጠን የሁሉም ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ሀብት ነው፤ በመሆኑም ቤተ ክርስቲያናችን ባሏት ታሪካውያንና ግዙፋን ቅርሶች ላይ ይህን ለልጅ ልጅ የሚተላለፍ ተጨማሪ ቅርስ ሠርታ በዛሬው ዕለት በማስመረቋ እንኳን ደስ አለን፤ ደስ አላችሁ! እንላለን፤

ቤተ ክርስቲያናችን በአሁኑ ጊዜ ከዚህ ሕንጻ በተጨማሪ በተለያዩ ሳይቶች እጅግ ግዙፍ የሆኑ ሌሎች ሕንጻዎችን እያስገነባች ትገኛለች፤ ሕንጻዎቹ በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድና ዕውቅና፥ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአኵስም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ቡራኬና የበላይ አመራር ሰጪነት፥ በብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ስራ አስኪያጅ፥ የደቡብ ምዕራብ ሸዋና ሸገር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፥ የምስካየ ኅዙናን መድኀኔ ዓለም ገዳም የበላይ ኃላፊ የዕለት ተዕለት ክትትልና የቅርብ አመራር ሰጪነት ሥራቸው በፍጥነትና በጥራት እየተከናወነ ይገኛሉ። ሌሎችም ዲዛይናቸው በሥራ ሂደት ላይ ያሉና በቅርብ ጊዜ የሚጀመሩ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች እንደቀጠሉ ናቸው።

ቤተ ክርስቲያናችን በአሁኑ ጊዜ በየአከባቢው ብዙ የልማት ሥራዎችን እየሠራች እንደሆነ ግልጽ ነው፤ ይሁንና የቤተ ክርስቲያናችን ልማታዊ ሥራዎች ሁሉ መከናወን ያለባቸው ከአጥቢያ አንሥቶ እስከ መንበረ ፓትርያርክ ባለው መዋቅር በተናበበና ስኬትን ሊያመጣ በሚችል ስልት መሆን ይገባዋል። ቤተ ክርስቲያናችን እንደ ቀድሞው የሀገር ሚሶ ሀብት ባይኖራትም ባሏት የአፀደ ቤተ ክርስቲያን ይዞታዎች በዕቅድና በተጠና አሠራር፥ እንደዚሁም የከተሞችን ውበት በጠበቀና ቦታ ቁጣቢ በሆነ መልኩ ልታለማ ይገባል። በአንጻሩም ግልጸኝነት በሌለበትና ጉጂ በሆነ መልኩ ለሦስተኛ ወገን ተጠቃሚ እየተላለፉ የሚሠራ አባካኝ አሠራር ማስቆም ይገባል። በየደረጃው የሚገኙ የመዋቅር ተጠሪዎችም የቤተ ክርስቲያን ይዞታ እንዳይባክን፥ ይልቁኑም በአስተማማኝ ሁኔታ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም እንዲውልና ተጨማሪ ሀብትን በመፍጠር ገቢን እንዲያሳድጉ ማድረግ ይገባል።

እንደሚታወቀው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሰፊ ነው፤ ይኸውም በማኅበራዊ፥ በኢኮኖሚያዊና በመንፈሳዊ አገልግሎት ሕዝበ ክርስቲያኑን ማገልገል ነው፤ ይህንን ተልእኮ በብቃት ለመወጣት አስተማማኝ የሆነ የሀብት ምንጭ ያስፈልጋል፤ ዘላቂ ሀብት በልማታዊ ሥራ ካልሆነ በቀር በሌላ ሊገኝ አይችልም፤ ስለሆነም ለሐዋርያዊ ተልእኮና ለገቢ ልማት አብዝተን መሥራትና መትጋት ይገባናል። ነገር ግን ሥራዎችን መሥራት ብቻ ሳይሆን በአግባቡ የሥራችን ተጠቃሚዎች መሆንም ሌላው ሊታሰብበት የሚገባ ነው። ከዚህ አንጻር በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ግዙፍ የሆነ ይህ ሕንጻ በግዘፉ ልክ ግዙፍ የሆነ የሐዋርያዊ ተልእኮ ሥራ ሊሠራበት ይገባል።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ፥ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፥ ዕውቅ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በመላ ዓለም ለሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ተከታዮች ትምህርተ ሃይማኖትን በቀጥታ ሥርጭት የሚያስተላልፉበት የስብከተ ወንጌል ዋና ማእከል ሆኖ ማገልገል ይኖርበታል። ከትምህርተ ወንጌል የበለጠ የቤተ ክርስቲያን ሥራ የለምና።

በተረፈ ይህን ግዙፍ ሕንጻ ተጠናቅቆ ለምረቃ በመብቃቱ አምላካችን እግዚአብሔርን በእጅጉ እናመሰግናለን። ለመላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንም በድጋሚ እንኳን ደስ አላችሁ እንላለን!

ወከእግዚአብሔር አኰቴት

ዘወሀብነ ንማዕ በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ

ንቡረ እድ ኤልያስ አብርሃ

በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላዩ ቤተክህነት
የመንፈሳዊ ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ



የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ መልእክት

«አምኅበ እግዚአብሔር ኮነት ዛቲ፣ ወነካር ይእቲ ለአእይንቲነ ÷ ይህች ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች÷ ለእይናችንም ድንቅ ናት»

(መዝ. 117÷23:24)

ከሁሉ አስቀድሜ፡ ለዚህ ታላቅ ሕንጻ ምረቃ በዓፀ እንኳን አደረሰን፣ እንኳን ደስ አለን ለማለት እመጻለሁ፡፡

ከብዙ ልፋትና ድካም በኋላ የተገኘ ስኬትን በተለያየ እይታና መንገድ ማድነቅ የተለመደ ነው፡፡ ሕንጻው በግዘፈቱ፣ በኪነ ሕንጻውና በሚሰጠው አገልግሎት ይደነቃል፡፡ ከዚህ በላይ ደግሞ የሥራ ውጤቱንና ስኬቱን ሁሉ ለእግዚአብሔር ለሚሰጥ የሃይማኖት ሰው የሥራ ፍሬ ሁሉ የሰው ጥረት ብቻ ያስገኛቸው እንዳልሆኑ በማመን ነገረ እግዚአብሔርን ማድነቅ አለ፡፡ ይህም ሕንጻ በዋናነት ከቅድስት ቤተ ክርስቲያኑ በረድኤትና በቸርነት የማይለየው ቅዱስ እግዚአብሔር እንዲፈጸም ያደረገው ነው፡፡

ልበ አምላክ ዳዊት በመዝሙሩ፦ «ይህች ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች፥ ለዐይናችንም ድንቅ ናት፡፡ እግዚአብሔር ያደረጋት ቀን ይህች ናት፤ በእርሷ ደስ ይበለን፥ ሐሴትም እናድርግ» (መዝ. 117፥23፡24) ብሎ እንደተናገረው፣ ዛሬ በዐይናችን የምናየውና የምናስመርቀው ይህ ግዙፍ ሕንጻ በሰው ምኞትና ጥረት ብቻ የተከናወነ ሳይሆን የእግዚአብሔር ልዩ ድንቅ አሠራርና የቸርነቱ ፍሬ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በዚህ ዙሪያ የሚንቀሳቀስ የውስጥም ሆነ የውጭ ተመልካች የግንባታውን እንቅስቃሴና የአፈጻጸም ሂደት በጉጉት ሲከታተል ቆይቷል፡፡ ቅን ሐሳብ ያለው ወገን ሁሉ የቤተ ክርስቲያኑን ክብር የሚጠብቅና ነገ የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት የተዘጋጀ ሕንጻን በዚህ መልኩ ተጠናቆ ለማየት በመብቃቱ ደስ ይለዋል፡፡ እግዚአብሔርንም ያመሰግናል፡፡

በተቋማዊ አመራርና በሕይወት ጉዞ ውስጥ «ጀምሮ ማጠናቀቅ» የነፃነት፣ የዕናትና የታማኝነት ትልቁ መለኪያ ነው፡፡ ማቀድና መጀመር የብዙዎች ልማድ ቢሆንም፣ ተስፋ ባለመቁረጥ፣ ማዕበሉንና ፈተናውን በመቋቋም፣ የጀመሩትን ሥራ እስከ ፍጻሜው ማድረስ ግን ልዩ የስኬት ማኅተም ነው፡፡ በመሆኑም ከሥራው ፍሬ ጋር በዚህ የተወለደው አዲሱ ሥነ ልቡና «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው፤ ትናንት አስጀምሮ ዛሬ እዚህ ላይ ያደረሰን አምላክ፣ ነገም ሌላ ታላቅ ታሪክና ሥራ ዐቅደን ለመጨረስ ያስችለናል!» የሚል መንፈሳዊ ብርታትና ተቋማዊ ጥንካሬን ይፈጥራል፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን ከዚህም የገዘፉ ሌሎች ፕሮጀክቶችን ሰፋ ባለ ዕቅድ ጀምራለች፤ ስለዚህ ዛሬ “ጀምሮ ማጠናቀቅ ይቻላል” የሚል እምነትና ተስፋ እየተተከለ ነው፡፡ መዝሙረኛውሥ ይህች ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች፥ ለዐይናችንም ድንቅ ናት በማለት ለዛሬው እንደተናገረው፥ ነገም ከእግዚአብሔር ዘንድ ይሆናል ያስኘናል፡፡

ለእግዚአብሔር ክብር የሚሠሩ ሥራዎች ሁሉ የወደፊቱን ትውልድ እምነት የሚያጸኑ ሕያዋን ድልድዮች ናቸው፡ ፡ ዛሬ ያጠናቀቅነው ይህ ሕንጻ ነገ ለምናቅዳቸው ታላላቅ ዕቅዶች መነሻና ማረጋገጫ ነው፡፡ ባለፉት ረጅም ዘመናት ስንገለገልባቸው የነበሩ ሕንጻዎች ጊዜውንና የአገልግሎቱን መስፋት የሚመጥኑ ስላልሆኑ በዚህ ተተክተዋል፡፡ ከዚህ የምንማረው ነገር ቢኖር፣ ነገም አገልግሎታችን የበለጠ እየሰፋ፣ ፍላጎቶች እየጨመሩ እንደሚሄዱ ነውና፤ ከዕቅድ ደረጃ ጀምሮ የሩቅ ተመልካችና የተፈጻሚ ሕልሞች ባለቤት መሆን ይጠበቅብናል፡፡ በተጠናቀቀ ሕንጻ ምረቃ በዓል ላይ ሆነን እንኳ ቢሆን ከዚህ የበለጠውን ታላቁን ስኬት ማለም ይኖርብናል፡፡

እንኳን ደስ ያለን፡ ሐሴትንም ጀምሮች አጠናቀን ለመመረቅ ያብቃን!

ረዳት ፕሮፌሰር ቀሲስ ግርማ ባቱ
በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላዩ ቤተ ክህነት
የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ

መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ባለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት

በቂቀ ሥዩማን አስክንድ ገ/ክርስቶስ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መፈሳዊ አገልግሎቷን ለማሳለጥና ለማስፋፋት ይቻላት ዘንድ ዘመናዊ የአስተዳደር ሥርዐት በመዘርጋት ወደ ሥራ ከገባች በርካታ ዐሥርተ ዓመታትን አስቆጥራለች። በደርግ ሥርዐት መብቷ ተጥሶ ከመንግሥት በሚመደብላት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ሥራዋን እንታከናውን ተገዳ ነበር። በሥርዐቱ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ የሚመደብባት ዋንኛ ምክንያት የሃይማኖት ነፃነት የማይታወቅበት ዘመን በመሆኑ ሲሆን፤ የበጀት ምደባ እንድታገኝ መደረጉ ደግሞ በገቢ ምንጭነት ስትጠቀምባቸው የነበሩ ቤቶቿና ሕንጻዎቿ በደርግ መንግሥት ተወርሰውባት ስለነበር ነው።

ከደርግ ውድቀት ማግሥት ጀምሮም ቤቶቿና ሕንጻዎቿ የተመለሱላት ሲሆን፤ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጆችዋንም ከብፁዓን የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት መካከል በምልአተ ጉባኤ በሚደረግ ምርጫ በመመደብ ራሷን በራሷ ማስተዳደር ከጀመረች በርካታ ዓመታት ተቆጥረዋል። ታዲያ እነዚህ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት በሚመሩት የአስተዳደር ሥርዐት ውስጥ ለቤተ ክርስቲያናችን መስፋፋትና መጠናከር የሚጠቅሙ እጅግ ብዙ ሥራዎች የተሠሩ ከመሆኑም በላይ በተመዘገቡት ውጤቶችም በርካታ ጥቅሞቿ ተከብረዋል፤ ልማቶቿ ተስፋፍተዋል።

የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ በእነዚህ ዓመታት የተመዘገቡ ውጤቶችን ለመግለጽ ባለመሆኑ ለጊዜው ከፍ ብሎ የተጀመረውን ርእሰ ጉዳይ ገታ በማድረግ፤ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ በመሆን በቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ከተሾሙ ጊዜ ጀምሮ ላለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት የተመዘገቡ የሥራ ውጤቶችን በመጠኑ በመዳሰስና መረጃዎችን በመግለጽ ለታሪክና ለትውልድ ተመዝግቦ እንዲቀመጥ ለማድረግ ነው።

ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ወደ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነት በመጡበት ወቅት በርካቶች፥ አንዳንድ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳትንም ጨምሮ፥ ከፍተኛ ሥጋትና ይህን ኀላፊነት ይወጡት ይሆን? የሚል ጥያቄ አድሮባቸው የነበረ ከመሆኑም በላይ፥ ዘመነ ሢመታቸው የጭቅጭቅ፥ የሰዶ ማሳደድ፥ የመበቃቀልና የፈተና ጊዜ እንደሚሆን በመስጋት ተስፋ በመቁረጥ ሁኔታ ውስጥ ገብተው እንደነበረ ይታወሳል።

ይሁን እንጂ የተገመተው ቀርቶ እጅግ አስገራሚ የአመራር ጥበብና ብቃት፥ ትዕግሥትና ቆራጥነት የታየበት፥ ሁሉም የግምቱን መዛባት ለመሸሸግ ያልቻለበት ውጤት መመዝገብ የጀመረው ገና ወደ አመራርነት በመጡ በሁለትና ሦስት ወራት ውስጥ ነበር። ብዙ የማይናገሩት፥ ብዙ የሚሰሙትና ባጭር ቃል ጠንካራ መልእክት የማስተላለፍ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ፥ እንደተፈራው ያሉ አባት አለመሆናቸውን በአስተዳደራዊውና በመንፈሳዊው ዘርፍ የሚቆጠሩ፥ የሚታይና የሚዳሰስ ውጤት በማስመዝገብ አረጋግጠዋል። የቤተ ክርስቲያናችን ኩራትና ዘመናዊ የአስተዳደር ሥርዐት የሚገለጽበትን ሕንጻ ግንባታ አጠናቀው ለምርቃት ማብቃታቸውን መነሻ በማድረግ ባለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት የተከናወኑ የሥራ ሂደቶችንና ውጤቶችን በመዳሰስ እነሆ እንደሚከተለው እንዘክራቸዋለን።

ይህን ጽሑፍ ስናዘጋጅም እውነቱን ብቻ በመዳሰስ ያልተዛባ መረጃ በመስጠት የብፁዕነታቸውን ትክክለኛ የሥራ ውጤት በወፍ በረር ከመግለጽ ባሻገር፥ ለከንቱ ውዳሴ በተጋነነና በቤተ ክህነት ባህል መሞጋገስን መርህ ባደረገ መልክ የተጻፈ እንዳልሆነ አንባብያን መራት ላይ ከሚታየው ውጤት ጋር አገናዝበው እውነታውን እንደሚረዱ እንተማመናለን።

የጠቅላይ ቤተ ክህነት ቅጽረ ግቢ

የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ቅጽረ ግቢ ዘርፈ ብዙ መገለጫዎች የነበሩት ሲሆን፤ ያለፉትን ዐሥራ ስድስት ወራት መለስ ብሎ በማስታወስ አሁን የሚገኝበትን ሁኔታ ለተመለከተው ማንም ሰው ጠንክሮ ከሠራ የማይለውጠው ነገር እንደማይኖር በተጨባጭ ያረጋግጥልናል። ቅጽረ ግቢው ከዐሥራ ስድስት ወራት በፊት እጅግ የተጐሳቆለ፥ ቆርቆር በቆርቆሩ በሆኑ ቤቶች፥ በአሮጌ መኪናዎች፥ በፍርስራሽ ቁሳቁሶች፥ በአፈርና በቆሻሻ ክምሮች፥ ማስተካከያና እንክብካቤ በጎደላቸው ዕፀዋቶች የተሞላ፥ የቤተ ክርስቲያናችንን ክብርና ልዕልና የማይገልጽ ከደረጃ በታች የሆነ ግቢ እንደነበር የሚካድ አይደለም።









ብዙዕነታቸው የቅጽረ ግቢው ቁመና መቀየር እንዳለበት በማመን በቅድሚያ ለበርካታ ዓመታት አገልግለው የቆሙ መኪናዎች ቀድሞ ከቀረጥ ነፃ የገቡ በመሆናቸው በጨረታ ለመሸጥ ስለማይቻል ከግቢው ውጭ ሌላ ቦታ እንዲሆኑ አመራር ከሰጡ በኋላ፥ በግቢው ውስጥ ካሉ ዕፀዋት መካከል መቀየትና መወገድ የሚገባቸውን በመለየት የለውጥ እንቅስቃሴያቸውን ቀጠሉ። በማስከተልም በተወገዱ ዕፀዋት ምትክ በተገቢ ቦታዎች ላይ ሀገር በቀል ዕፀዋትንና ሣር በመትከል፥ ማራኪ የውኃ ፏፏቴ በማሠራት ቅጽረ ግቢው ከውስጥም ሆነ ከውጭ ሲመለከቱት ግልጽ፥ እጅግ ማራኪና ውበትን የተላበሰ እንዲሆን አድርገዋል።

ዛሬ የምንመለከተው የጠቅላይ ቤተ ክህነት ቅጽር ግቢ በአለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት ከምናውቀው ቅጽረ ግቢ ጋር በዐይነ ኅሊና ለማወዳደር ብንሞክር የሰማይና የምድር ያህል ልዩነት የታየበት፥ የቤተ ክርስቲያኒቱ ደረጃ የተንጸባረቀበት፥ የምንኮራበትና የምንመካበት ተቋም ወደመሆን የተሸጋገረው ከዐሥራ ስድስት ወራት በፊት ወደ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነት መንበር ሲመጡ በጥርጣሬና በስጋት ባየናቸው በብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ አመራር ሰጪነትና ቅርብ ክትትል መሆኑንን ስናስብ ምን ይሰማን ይሆን?

ሁኔታው እግዚአብሔር አምላክ በማን ላይ አድሮ ምን እንደሚሠራ የተገለጸበት፥ የብፁዕነታቸው አቅም የታየበት፥ ከቅዱስ ፓትርያርካችን መመሪያ በመቀበል፥ ከብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሓፊ ጋር በመናበብና አንድነትን ፍጹም በማጽናት የተመዘገበ እፁብ ድንቅ የሚታይና የሚዳሰስ ውጤት ነውና፥ በብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ታሪክ ውስጥ አንድ ተብሎ በውጤታማነት ተመዝግቧል። ይህ እውነታም ለትውልድ ትምህርትን፥ በጥላቻ ታውሮ በግምት ሰውን በመፈረጅ ስም ማጥፋት ሥራቸው የሆኑ ወገኖችን ውርደትና ኪሳራ ላይ ከመጣሉም በላይ፥ እንዴት በዚህ ዘመንና በእሳቸው መሪነት ይህን የመሰለ ውጤት ይመዘገባል? ለሚሉ አንዳንዶች ሀፍረትን አከናንቦ ታሪክ እውነቱን ሲዘክረው ሊኖር በወርቃማ ቀለም መዝግቦታል።

መጻሕፍትና ኮሮጌ መጋዘኖች

በዘመናዊ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ሥርዐት ውስጥ አቅዶ፥ ገበያ አጥንቶ፥ ትርፍና ኪሳራን አስልቶ፥ ሥርጭትና ተጨማሪ ጥቅመትን ቀምሮ፥ የገበያ ፍላጎትንና አቅርቦትን አመጣጥኖ መጻሕፍትን ለማተምና ለማሠራጨት ባለመታደላችን ምክንያት፥ ለቊጥር የሚታክቱ መጻሕፍት በዓይነት በዓይነት በማሳተም በበርካታ መጋዘኖች እንዲከማቹ ተደርጎ ቆይቷል። በከተማና በገጠር የመጻሕፍትን ፍላጎት ሳናረካ ሌሎች አካላት በቤተ ክርስቲያኒቱ ማእከላዊ አስተዳደር ብቻ መታተም የሚገባቸውን መጻሕፍት ጭምር እያተሙ እንዲያሠራጩ ዕድል ፈጥረን፥ በበርካታ ሚሊዮኖች ወጪ የታተሙ መጻሕፍትን በመጋዘኖች ከመከመር ባሻገር፥ የተወሰኑ መጻሕፍት መጋዘን ውስጥ ተቀምጠው ከገበያ በመጥፋታቸው በአንዳንድ ክልልሎች የሚሰጡ መንፈሳዊ አገልግሎቶች በፎቶ ኮፒ መጻሕፍት የሚጠቀሙበት ሁኔታ በመፍጠር አሳዛኝ ታሪክ አስመዝግበናል።

እነዚህ በከፍተኛ ወጪ የታተሙ መጻሕፍት ገበያ ላይ ሳይውሉ በላይ በላዩ ተጨማሪ መጻሕፍትን በማሳተም፥ የመጻሕፍት ማከማቻ መጋዘኖችን በማስፋፋትና የመጻሕፍት ሥርጭቶችን በመቀነስ አሳዛኝ ታሪክ የተመዘገበበት ሁኔታ እንዲያበቃ በጽኑ እምነት የተንቀሳቀሱት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ፥ መጻሕፍቱ በዓይነት እንዲለዩ፥ ጥቅም ላይ መዋል የማይችሉና በሊቃውንት ጉባኤ ተመርምረው በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ እንዲወገዱ የተወሰነባቸው አንዳንድ የሃይማኖት ችግር ያለባቸው ጸሓፍት ያሳተሟቸውና በመጋዘን እንዲከማቹ የተደረጉ መጻሕፍት በውሳኔው መሠረት እንዲወገዱ በማድረግ፥ ከመጻሕፍት ክምችት ጋር በተያያዘ የተፈጠረው አላስፈላጊ ክምችት በሕግና በሥርዐት መፍትሔ እንዲያገኝ ተደርጓል።

ምንም ዓይነት ተመልካች ሳያገኝ ለበርካታ ዓመታት ቤተ ክርስቲያን በከፍተኛ ወጪ ያሳተመቻቸው መጻሕፍት በዓይነት፥ በቊጥር፥ በብዛት፥ በገበያ ተፈላጊነትና በሥርጭት አዋጭነት ተለይተው ወደ ገበያ ውስጥ መግባት እንዲችሉ ለማድረግ የሚያስችል ኮሚቴ በማቋቋምና ለመጻሕፍቱ ደህንነት አስተማማኝ ወደሆነ ስፍራ በማዘዋወር ሂደት ውስጥም መላውን የጠቅላይ ቤተ ክህነት ሠራተኛን በማንቀሳቀስና በማሳተፍ፥ የሥራ ክቡርነትና አሠሪ ከተገኘ ተናቦና ተደማምጦ መሥራት እንደሚቻል ያመላከተ የአመራር ጥበብን በማሳየት በሁሉም ሠራተኛ ትጋት መጻሕፍቱን ከጉስቁላ መጋዘኖች ወደ ተሻለ ቦታ የማዛወሩ ሥራ በውጤታማነት የተከናወነውም በብፁዕነታቸው አመራር ሰጪነት ባለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት መጀመሪያ ሲሆን፤ የብፁዕነታቸው ሌላኛው ስኬታማ ሥራ በመሆን ተመዝግቧል።







ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከፍ ሲል በመጠኑ የተገለጸውን የመጻሕፍት ክምችት በመያዝ ለበርካታ ዓመታት ያገለገሉት ጐስቋላ መጋዘኖችን በማንሣትና አካባቢውን በሚገባ በማጽዳት ቅጽረ ግቢው እንዲያምር፥ የተገነባው ዘመናዊ አዳራሽም በቂ የመኪና ማቆሚያ ስፍራ እንዲያገኝ በማድረግ አስቀድሞ በሕንጻው ግንባታ ወቅት ለመኪና ማቆሚያ መዋል እንደሚገባው በጥናት የተገለጸውን ስፍራ በአስቸኳይ በማንሣት የሕንጻውን ደረጃ በማስጠበቅ በአጭር ጊዜ ስኬታማ ሥራ የሠሩትም ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ በመሆናቸው ታሪክ በውጤታማ ሥራ አስኪያጅነት ከሚጠቅሳቸው ሥራዎች አንዱ ይህን ቦታ ማጽዳትና ለታለመለት ዓላማ ማዋል መሆኑን ልብ ይሏል።

በሌላ በኩልም ከመጋዘኖቹ ጀርባ የሚገኙ እጅግ የተጐሳቆሉ በቆርቆሮና በጭቃ የተሠሩ መኖሪያ ቤቶች ለእሳት አደጋ የተጋለጡና ለእይታ የማይመቹ ቤቶችን በማንሣት ጠቅላይ ጽ/ቤቱን ከአደጋ መታደግ፥ ቅጽረ ግቢውን በሚገባ ማስዋብና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ እንደሚገባ ጽኑዕ እምነት ያላቸው ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ፥ ከአራዳ ክፍለ ከተማ፥ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር የተጐሳቆለውንና ለአደጋ የተጋለጠውን ሥፍራ ማንሣት እንደሚገባ መተማመን ላይ መደረሱን ተከትሎ፥ ከዐሥራ ሁለት በላይ አባወራዎችን በማንሣትና ጊዜያዊ መጠለያ የሚያገኙበትን ዕድል በመፍጠር ቦታውን የማጽዳት፥ የማሳመርና የቤተ ክርስቲያንን ክብር በሚመጥን ደረጃ የማስተካከሉን ሥራ ተያይዘውታል።

በአጠቃላይ ከመጻሕፍት ክምችት፥ ከአሮጌ መጋዘኖች መነሣት፥ ለአደጋ ከተጋለጡ ቤቶች መፍረስና ጠቅላይ ቤተ ክህነቱ ውብና ማራኪ እይታን የተላበሰ፥ የቤተ ክርስቲያንን ክብርና ደረጃ ባስጠበቀ መልኩ የማደራጀትና የማስዋብ ሥራው እጅግ የተሳካና ውጤታማ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፤ ሥራው ሲከናወን ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ መከናወኑ፥ አብዛኛው ሥራ በስፖንሰር መሸፈኑ፥ ይልቁንም ከፈረሱ መጋዘኖች ሽያጭ ቤተ ክርስቲያን ገቢ የምታገኝበት ሁኔታ መፈጠሩ ሌላው ግኝት ነው። በተሠራው ሥራ ቤተ ክህነቱ ከአረጀ አስፋልት ወደ ጥሩ የአስፋልት ንጣፍ፥ ሳቢነት ከሌለው አቋም ወደ ማራኪና ንጹሕ ቅጽረ ግቢ ተለውጦ በፏፏቴና ቤተ ክርስቲያንን በሚገልጹ ምልክቶች እንዲያሸበርቅ፥ ቤተ ክርስቲያን በግቢዋ በሚገኙ ውብ ሕንጻዎቿና በማራኪ ዙሪያ ገብ አጥሯ የምትገለጽ፥ ቅጽረ ግቢዋን የተመለከተ ሁሉ በኩራት አንገቱን ቀና አድርጎ የሚሄድባት ሁኔታ የተፈጠረው በብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ዘመነ ሢመት ባለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት ውስጥ መሆኑን ቤተ ክርስቲያን በታሪክ ማኅደሯ ከትባ ለትውልደ ትውልድ ልታስተላልፈው አንድ ብላ በውጤታማነት መዝግባዋለች።







መልካም አስተዳደር በቤተ ክህነት

የመልካም አስተዳደር መገለጫዎች እጅግ ብዙና ዓይነታቸውም ልዩ ልዩ መሆኑ ግልጽ ነው። መልካም አስተዳደርን በተቋም ደረጃ እውን ለማድረግ ከምንጠቀምባቸው ስልቶች መካከል ሥራን ተቋማዊ በሆነ መንገድ መምራትና አሳታፊነትን በማጠናከር፥ ክፍተቶችን በሥልጠና በመሙላት፥ ሥራዎችን አከፋፍሎ በመስጠትና የመጡትን ውጤቶች በመገምገም የቀጣይ ሥራዎችን አቅጣጫ በማስቀመጥ መምራት ሲቻል እንደሆነ ግልጽ ነው።

ባለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት ብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ የተከተሉት ስልት አሳታፊነትንና ሥራዎችን ከፋፍሎ የመስጠት እንዲሁም ውጤቶችን በቅርበት የመከታተል ሂደት በተለያዩ ዘርፎች በርካታ ውጤቶች እንዲመዘገቡ ያደረገ ሲሆን፤ ያጋጠሙ ችግሮችን በመፍታትና ልዩ ልዩ ውሳኔዎችን በአስተዳደር ጉባኤና በቋሚ ሲኖዶስ አፋጣኝ ምላሽ የሚያገኙበትን አሠራር የመከተል የአመራር ጥበብ ሥራዎችን የጋራ በማድረግ ደረጃ ትልቅ አስተዋፅኦን አበርክቷል።

ከዚህ አንጻር ብፁዕነታቸው በአቤቱታ ከተለያዩ አህጉረ ስብከት የሚመጡ ጉዳዮችን ለማጣራትና ውሳኔ ለመስጠት የሄዱበት ርቀት፥ ያሳዩት ትዕግሥትና ችግሮች በጥናት ላይ ተመሥርተው እንዲፈቱ የሰጧቸው አመራሮች፥ መምሪያና ድርጅቶች በራሳቸው አቅም ሥራዎችን ሠርተው በውጤት እንዲገለጹ ያደረጉበት መንገድ፥ ልዩ ልዩ ሥልጠናዎች እንዲካሄዱና የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም እንዲጐለብት ያደረጉበት አካሄድና የተመዘገበው ውጤት፥ በአጠቃላይ አንድ የዘመናዊ አስተዳደር ሥርዐት የሚጓዝበትን መንገድ በማመላከትና በቆራጥነት በመምራት ያስመዘገቡት የመልካም አስተዳደር ውጤት፦ በሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ፥ በኢ/አ/ተ/ቤ/ክርስቲያን መገናኛ ብዙኃን ድርጅት፥ በሕዝብ ግንኙነት መምሪያ፥ በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ፥ በቅርስ ጥበቃና ቤተ መጻሕፍት ወመዛክር መምሪያ፥ በትምህርትና ማሠልጠኛ መምሪያ፥ በካህናት አስተዳደር መምሪያ፥ በቤቶችና ሕንጻዎች አስተዳደርና ልማት ድርጅት በግልጽ የተመዘገቡት ውጤቶች፥ የብፁዕነታቸውን የመሪነት አቅም ያሳዩ በመልካም አስተዳደር ሥርዐት ዝርጋታ ውስጥ ተጨባጭ ውጤቶች የተመዘገቡበት እንደሆነ ባለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት የተገለጸ ሐቅ ነው።

የቤቶችና ሕንጻዎች አስተዳደርና ልማት ድርጅት

የቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ የገቢ ምንጭ በመሆን የሚታወቀው የቤቶችና ሕንጻዎች አስተዳደርና ልማት ድርጅት የሚሰጠው አገልግሎት ደንበኛ ተኮር፥ ቀልጣፋና በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ከማድረግ ጐን ለጐን በሚሰጠው አገልግሎት መቀላጠፍና ፍትሐዊነት ቤተ ክርስቲያንን እንዲያስመሰግን፥ በመልካም ሥራ አፈጻጸም ውጤታማነት ቤተ ክርስቲያንን የሚሰብክ ተቋም መሆን እንዲችል ከፍተኛ ጥረትና ቀጥተኛ አመራር በመስጠት፥ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ በድርጅቱ ተቋማዊ አገልግሎት ውስጥ ሥር ነቀል ለውጥ እንዲመዘገብ አድርገዋል።

ብፁዕነታቸው የድርጅቱን አሠራር ለማዘመንና ደንበኛ ተኮር ሥራ እንዲሠራ በሰጡት ቀጥተኛ አመራርና ባደረጉት የዕለት ተዕለት ክትትል ድርጅቱ ከጊዜ ወደጊዜ የተሻለ አፈጻጸም በማስመዝገብ አሠራሩን ይልቁንም የቤት ኪራይ ክፍያ ሥርዐቱን ዲጂታል ማድረግ የቻለ በመሆኑ፥ በዘርፉ ይስተዋል የነበረውን የሙስናና የአሠራር ችግር ከመሠረቱ በመቅረፍ የተሻለ ተቋም የሚሆንበት ዕድል እንዲፈጠር አድርገዋል።

የቤቶችና ሕንጻዎች አስተዳደርና ልማት ድርጅት ብፁዕነታቸው በልዩ ትኩረት ከሚመሯቸው ተቋማት አንዱ በመሆኑ፥ ደንበኞች በየሚኖሩበት ሕንጻ በሚመርጧቸው የነዋሪዎች ኮሚቴ አማካኝነት ችግሮቻቸው የሚደመጡበትና አፋጣኝ ምላሽ የሚያገኙበት ሥርዐት ተፈጥሯል። በኋላ ቀር አሠራር ይከፈል የነበረው የቤት ኪራይ በዲጂታል የክፍያ ሥርዐት እንዲተካ በማድረግ ጊዜ ቆጣቢና ቀልጣፋ የገቢ አሰባሰብ ሥርዐት እንዲገነባና ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል። ለአገልግሎት የማይመቸውና የተጐሳቆለው ቢሮም በዘመናዊና ለአገልግሎት ምቹ በሆነ ቢሮ ተቀይሮ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል። በተጨማሪም ታማኝ ኪራይ ከፋዮች የሚሸለሙበት ሥርዐት ተዘርግቶ እውቅና እንዲያገኙ ተደርጓል።

ኪራያቸውን በወቅቱና በአግባቡ የሚከፍሉ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት የእውቅናና የምስጋና መርሐ ግብር ተዘጋጅቶ ቅዱስነታቸው በተገኙበት ተሸላሚዎች እንዲሆኑ ተደርጓል። ውጤታማ ሠራተኞችና አመራሮች የማበረታቻ ሽልማት እንዲያገኙና ሥራቸውን የበለጠ በውጤታማነት የሚያከናውኑበት፥ የአገልጋይነት መንፈስ የሚዳብርበት ሥርዐት የተዘረጋ ሲሆን፤ ከሠራተኞችና ከነዋሪዎች ጋር ተደጋጋሚ ውይይቶች የሚደረጉበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ከሦስት ወራት በላይ የሚወስደው ውል የማደስ ሥራም በሃያ ደቂቃ የሚጠናቀቅበት አሠራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ተደርጓል። ሥራዎች ሁሉ የሚገለጹበት ማኅበራዊ ሚድያ ተከፍቶ ተጨባጭ ውጤት በመመዝገብ ላይ ይገኛል። ነዋሪዎች መረጃ የሚያገኙበትና መረጃ የሚያቀብሉበት የቴሌግራም ግሩፕ ተፈጥሮ መረጃዎች የሚሰበሰቡበት፥ የሚደራጁበት፥ የሚተነተኑበትና መፍትሔ የሚያገኙበት አሠራር ተዘርግቶ ተግባራዊ

በመሆን ላይ ይገኛል። በዕለት ተዕለት አገልግሎት ውስጥ የሚስተዋሉ ችግሮችን በወቅቱ በመፍታት ተገልጋዮች በተቋሙ አሠራር የሚመኩበትና የሚደሰቱበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ደንበኞች በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ሐሳብ የሚሰጡበት የሐሳብ መስጫ መዝገብ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ ውሏል።

በአጠቃላይ ድርጅቱ ሥር ነቀል ለውጥ በማድረግ በየዓመቱ የቅዱስ ሲኖዶስ አጀንዳ ከመሆን ወጥቶ ተመስጋኝና ተሰፋ የሚጣልበት ተቋም ወደመሆን የተሸጋገረው በብፁዕነታቸው ቀጥተኛ ትእዛዝ፥ የቅርብ ክትትልና ቆራጥ አመራር ሰጪነት በመሆኑ፥ ብፁዕነታቸው ተጨባጭ ለውጥ ያስመዘገቡበት ያለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት የሥራ ፍሬያቸው ማሳያ በመሆን በደማቅ የወርቅ ቀለም ተጽፎ ለትውልድ የሚተላለፍ ይሆናል።

መንፈሳዊ አገልግሎት

ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ባለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት ከፍ ሲል በመጠኑ የዳሰስናቸውንና ከዚህ ርእሰ ጉዳይ በኋላ የምንዳስሳቸውን ውጤታማና ስኬታማ የሥራ ውጤቶች ከማስመዝገብ ጐን ለጐኑ፥ በእርግጠኝነት ከዚህ ቀደም በታሪክ ባልተመዘገበ መልኩ ከጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነት የሥራ ድርሻቸው በተጨማሪ፥ በሁሉም መንፈሳዊ አገልግሎቶች በንቃት በመሳተፍ በደቡብ ምዕራብ ሸዋም ሆነ በሸገር ከተማ አህጉረ ስብከታቸው በሰንበትም ሆነ በበዓላት ወቅት በመገኘት ቀድሰው በማቍረብ፥ ከዚያ መልስም ሳይታክቱና ሳይደክሙ ቢሮ በመገኘት የአስተዳደር ሥራቸውን በሚገባ በማከናወን በርካታ ውጤቶችን ያስመዘገቡ አባት ስለመሆናቸው በእርግጠኝነት መመስከር ይቻላል።

ብፁዕነታቸው በመንፈሳዊው የአገልግሎት ዘርፍ በትጋት የሚሠሩ ብቻ ሳይሆኑ በአህጉረ ስብከታቸው፥ በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳምና በተለያዩ በማእከል ደረጃ በሚከበሩ በዓላት ላይ በመገኘት መልእክቶችን በማስተላለፍና ምእመናንን አስተምረው በመባረክ ረገድ ያደረጉትና እያደረጉት ያለው አባታዊ ተሳትፎ የጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነት ሥራቸውን የበለጠ የተዋጣ ያደረገላቸው እንደሆነ ባለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት የታዘብነው ሀቅ ሲሆን፤ ከእርሳቸው በቀደሙ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጆች ያልተስተዋለ የመንፈሳዊ አገልግሎት ትጋትና ውጤት በታሪካቸው ሲወሳ ሊኖር ተመዝግቧል።

ይህ መንፈሳዊ አገልግሎትን ከአስተዳደራዊ አገልግሎት ጋር በማጣመር አንዱ በሌላኛው አገልግሎት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሳያሳድር ይልቁንም ማራኪና አንጸባራቂ ውጤት በማስመዝገብ አዲስ ምዕራፍ የከፈተው የብፁዕነታቸው አገልግሎት፥ ሳይደክሙና ሳይታክቱ ቤተ ክርስቲያንን በሁለንተናዊ አገልግሎት ዘርፍ ለማገልገልና ውጤታማ ለማድረግ ያላቸውን ትጋት ያሳየ፥ ምርጥ መሪነታቸውን ያረጋገጠ፥ በትጋትና በቆራጥነት ቤተ ክርስቲያንን ለማሻገር ያለሰለሰ ጊዜያቸውን፥ ዕውቀታቸውንና ችሎታቸውን አስተባብረው ለሥራ ዝግጁ መሆናቸውን ያሳዩበት፥ ብዙዎች ስለ ብፁዕነታቸው ያላቸውን የተሳሳተ ግምት የቀየረ፥ ብፁዕነታቸውን በልካቸው እንድንገልጻቸውና ሌሎችም በሚገባ እንዲያውቋቸው ያስገደደ ስኬታማ የአገልግሎት ትጋታቸው ይገለጽ ዘንድ እነሆ የአለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት የሥራ ጊዜያቸውን በምንዘክርበት በዚህ ጽሑፋችን ታሪክ መዘግቦ ለትውልድ ሊያስተላልፈው ግድ ሆነ።

ፊማት በኮሮጌው ቁራ

በተለምዶ አሮጌው ቁራ በመባል በሚታወቀው ቦታ ላይ ቤተ ክርስቲያን በዘመናዊ ሕንጻ ግንባታ ታሪካዊ ራሷን በራሷ ማስተዳደር ከጀመረች ወዲህ ከትንሣኤ ሕንጻ ቀጥሎ ሁለት ሕንጻዎችን በመገንባት የገቢ አቅሟን ለማሳደግ ያስችላት ዘንድ በብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነት፥ በብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሓፊነት ዘመነ ሢመት 1000 እና 480 ካሬ ሜትር ስፋት ባላቸው ቦታዎች ላይ ሁለት ሁለገብ ሕንጻዎችን ለመገንባት አስፈላጊው ጥናት ተደርጎ፥ ዲዛይን ተሠርቶና ግንባታ ተጀምሮ በመፋጠን ላይ እያለ የሁለቱ ብፁዓን አባቶች ዘመነ ሢመት በመጠናቀቁ ምክንያት የግንባታዎቹን ሥራ በሚፈለገው ፍጥነት መቀጠል ሳይቻል የቀረ ሲሆን፤ በሀገሪቱ የተከሠተው የግንባታ ቁሳቁስ ዋጋ ንረትም ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ወጪ ለማውጣት የተገደደችበት ሁኔታን ፈጥሯል።

ይሁንና እነዚህ ሁለት ግዙፍ ሁለገብ ሕንጻዎች በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ሥራቸው ባለበት ቆሞና አንዳንዱም በጥቂቱ እየተሠሩ ከእነርሱ በኋላ የተጀመሩ ሕንጻዎች ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት በጀመሩበት ዘመንም ቢሆን፥ የሰው ያለህ እያሉ ዛሬ ላይ ሲደርሱ፥ አስቀድመው የጀመሯቸው ብፁዓን አባቶች ቦታ ተቀያይረው ተመልሰው ወደ አመራርነት ሲመጡ ሕንጻዎቹ በፊት ከነበሩበት የግንባታ አፈጻጸም ደረጃ እምብዛም ሳይራመዱ፥ ውስጣዊ አደረጃጀታቸው ተበጣጥሶና ሥራው ተጓቶ በጣም በሚያስገርም ሁኔታ ቤተ ክርስቲያንን ለከፍተኛ ወጪ ዳርገው፥ ጥቂቶችን አበልጽገው ዳግም ተገናኙ።

ይህ ሁኔታ እጅጉን ያሳዘናቸው ብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ወጪ ቆጣቢና ጊዜን ታሳቢ ባደረገ አግባብ ግንባታዎቹ በአስቸኳይ ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት እንዲጀምሩ ማድረግ በመቻላቸው፥ በ480 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የተገነባው ሕንጻ ተጠናቆ የተመረቀ ሲሆን፤



በ1000 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የተገነባው ሕንጻም የማጠናቀቂያ ሥራው በሚገባ ተከናውኖ እነሆ በዛሬው ዕለት ለምርቃት በቅቷል።

በአሮጌው ቁራ ለምርቃት የበቁት ሕንጻዎች በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ግንባታቸው ዘግይቶ ቤተ ክርስቲያንን ለከፍተኛ ወጪ በመዳረግ፥ ለግንባታ ሥራው ከሚያስፈልገው በላይ የግንባታ ቁሳቁስ ወጪ በማስከተልና የጥቂቶችን ኪስ በመሙላት ረገድ በቤተ ክርስቲያን የግንባታ ሥራ ውስጥ በመጥፎ ታሪክ የተመዘገቡ ሕንጻዎች ቢሆኑም፤ ዘመን ቆጥሮ፥ ግፍን ሰፍሮ እግዚአብሔር አምላክ አስቀድሞ ግንባታቸውን የጀመሯቸው አባቶች እንዲያጠናቅቋቸው በማድረጉ ምስጋና የሚገባው ሲሆን፤ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ያላቸውን በሳል የመሪነት አቅም ተጠቅመው በአጭር ወራት ሥራቸው ተጠናቆ ለምርቃት እንዲበቁ ያደረጉት የተሳካ ጥረት፥ ግንባታዎቹን በማጓተትና የግል ጥቅምን በማሳደድ ቤተ ክርስቲያን ላይ ደባ የሠሩትን ያሸማቀቀ፥ የብፁዕነታቸውን የሥራ ሰውነት በተግባር ያረጋገጠ ፕሮጀክት በመሆን ያለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት ስኬታቸው መገለጫ ሆኖ በታሪክ ተመዝግቧል።

የቁብቢ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ገዳም

በመላው ዓለም በታላቅነቱ፥ በታሪካዊነቱና በስዕለት ሰሚነቱ የሚታወቀው የቁልቢ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ላለፉት ሰባ ዓመታት ይህ ነው የሚባል እድሳት ሳይደረግለት በመቆየቱ ለከፍተኛ ጉዳት ተዳርጎ የነበረ ሲሆን፤ ቅጽር ግቢውም ለአገልግሎት የማይመች፥ በአውደ ምሕረቱ ፊት ለፊት የሚገኘው የምእመናን መውጫና መግቢያ ተሰነጣጥቆ የጉዳቱ መጠን ጎልቶ ይታይ ነበር።

ይህ ለቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ገቢ በማስገኘት ለአብነት ት/ቤቶች ማስፋፊያ፥ ለመንፈሳዊ ኮሌጆች ማጠናከሪያ፥ ለገዳማት መርጃና ማስፋፊያ ከፍተኛ በጀትን በመሸፈን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መጠናከር ታላቅ ሚና የሚጫወተው የቁልቢ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ገዳም፥ ከቤተ ክርስቲያን አልፎ ለቁልቢ ከተማ ንጹሕ የመጠጥ ውኃን፥ ለከተማው ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤትና መገልገያ መኪና በመለገስ ለከተማው ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከተውና በማበርከት ላይ



የሚገኘው ታላቁ ገዳማችን፥ «ሸክላ ሠሪ በገል ይበላል» እንዲሉ፥ መቅድሱ ዝናብ እያስገባ፥ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ ተጐድቶና በጥገና ስም በአላስፈላጊ ቁሳቁሶች ተለጣጥፎ ዘመናት ቢያስቆጥርም፤ ገዳሙ እድሳት እንዲደረግለት ከዐሥር ዓመታት በላይ የወተወቱ የገዳሙ ሥራ ኃላፊዎች የሚሰማቸው አጥተው መቆየታቸው እርግጥ ነው።

ይሁንና ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ሆነው በተሾሙ ማግሥት ጥያቄውን ተቀብለው ገዳሙ የሚገኝበትን ወቅታዊ ሁኔታ ተዘዋውረው ከተመለከቱ በኋላ፥ በአጭር ጊዜ የእድሳት ሥራው እንዲከናወን የሰጡትን ትእዛዝ ተከትሎ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ በከፍተኛ ጥንቃቄና ጥበብ ታድሶ ከሰባ ዓመታት በኋላ በፊት የነበረውን ግርማ ሞገስና ውበት ተላብሶ ባለፈው ሐምሌ 17 ቀን 2018 ዓ.ም. ታቦተ ሕጉ ከመቃኞ ወደ ታደሰው ቤተ ክርስቲያን ተመልሶ ምርቃቱ ተከናውኗል።

ይህን ለበርካታ ዓመታት ምላሽ ያላገኘና በዘመናት ብዛት አንዳንድ ችግሮቹን ለመቅረፍ በማሰብ በተደረገለት ጊዜያዊ ችግሮችን የመፍታት ሥራ የበለጠ እየተጐዳ የቆየውን ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን፥ መሠረታዊ እድሳት በማድረግ ውበትና ጥራቱን የማላበስ ሥራ በብፁዕነታቸው በሳልና ቆራጥ አመራር የተከናወነ ሲሆን፤ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ በቀጣይነት መከናወን የሚገባቸው ቀሪ ሥራዎች በፍጥነት እንዲቀጥሉ አመራር ተሰጥቷል።

ከገዳሙ አስተዳደር ጋር ተያይዞ የተስተዋለውን ችግር መፍትሔ ለመስጠትም ገዳሙን የሚመጥኑ፥ የተረጋጉና በሁለንተናዊ ብቃታቸው የተመሰከረላቸው አስተዳዳሪ በመመደብ የገዳሙ ችግር እንዲቀረፍ፥ ቀጣይና ቀሪ ሥራዎችም በአግባቡ እንዲከናወኑ በማድረግ ብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ የቀደምት አባቶቻቸውን ታሪክ በመድገም ባለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት በደማቅ ቀለም ከጻፏቸው ታሪኮች የቁልቢ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ገዳም የእድሳት ሥራ አንዱ በመሆን በታሪካቸው ተመዝግቧል።

የዘመናዊ አዳራሽ ግንባታ

ዛሬ ለምርቃት የበቃው ዘመናዊ አዳራሻችን በብፁዕ አቡነ ያሬድ ዘመነ ሢመት ተጀምሮ በብፁዕ አቡነ አብርሃም ዘመነ ሢመት የቀጠለ ፕሮጀክት ሲሆን፤ በብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ዘመነ ሢመት በከፍተኛ ትኩረትና ቅልጥፍና ተገንብቶ እነሆ ለምርቃት በቅቷል። ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ዛሬ የተመረቀው አዳራሽ በጥራትና በፍጥነት ተሠርቶ በወቅቱ ካልተጠናቀቀ ቤተ ክርስቲያንን ለከፍተኛ ወጪ እንደሚዳርጋት በመረዳት፥ በልዩና በከፍተኛ ትኩረት የግንባታ ሥራው እንዲከናወን በሰጡት በሳልና ቆራጥ አመራር በአጭር ጊዜ ውስጥ የግንባታው የማጠቃለያ ሥራዎች በሚገባ መከናወን በመቻሉ እነሆ ለምርቃት በቅቷል።



ብፁዕነታቸው የአዳራሹን ሥራ በቅብብሎሽ የአሠራር መርህ ከቀደሙ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጆች በመረከብ በከፍተኛ ፍጥነትና ትጋት እንዲከናወን በማድረግ ያስመዘገቡት ውጤት የሚደነቅና የሚበረታታ ነው። አሮጌ ቁራ አካባቢ የተሠሩት ሕንጻዎችም በዚህ ፍጥነት ተሠርተው ቢሆን ኖሮ ቤተ ክርስቲያንን ለወጪና ለኪሳራ ይዳርጉ እንዳልነበር በማሳየት ደረጃ ምሳሌ ሊሆን የሚችል ሥራ የሠሩ ሲሆን፤ ወደፊትም የግንባታ ሥራዎች በቅብብሎሽና በትጋት መከናወን እንዳለባቸው ትምህርት የሰጡ፥ ተግባራዊ የመሪነት ጥበብን ያሳዩ፥ ተቋማዊ መርሕን ተከትለው የሚሠሩ መሆናቸውን ያረጋገጡ አባት ያደርጋቸዋል።

በአጠቃላይ ብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ዛሬ ለምርቃት የበቃውን ዘመናዊ ሕንጻ ለማጠናቀቅና ለማስመርቅ ካደረጉት ከፍተኛ ጥረት ባሻገር የአዳራሹን ውበት ለማስጠበቅ የሚያስችል የፏፏቴና የአስፋልት ሥራ፥ የአረንጓዴና ጽዱ ቅጽረ ግቢ የዕፀዋትና የአበባ አትክልት ተከላ ሥራዎች ከመኪና ማቆሚያ ቦታና ከቅጽረ ግቢ አጥር ሥራ ጋር ተናበው መሠራታቸው ለአዳራሹ ተጨማሪ ውበትን ያጐናጸፈው መሆኑ የሚታይ ሐቅ ነው። እናም ብፁዕነታቸው በዚህ ግዙፍና ዓለም አቀፍ አዳራሽ ግንባታ ውስጥ ያኖሩት አሻራ የመሪነት አቅማቸውንና የልማት ሰውነታቸውን የሚመሰክር በመሆን ለትውልድ ይተላለፍ ዘንድ ከአለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት ስኬታማ ሥራዎቻቸው አንዱ በመሆን በቤተ ክርስቲያናችን መዝገብ ሰፍሯል።

የሦስቱ ሁለገብ ሕንጻዎች ግንባታ

ቤተ ክርስቲያናችን በቀጣዩ ትውልድ ምንም ዓይነት የኢኮኖሚ ችግር ሳይገጥማት የስብከተ ወንጌል አገልግሎቷን ለማሳለጥና ለአዲሱ ትውልድም አገልግሎታን በጥራት ለማስቀጠል ኢኮኖሚያዊ አቅሟ ሊዳብርና ሊጠናከር ይገባል። ይህንን ሁኔታ ቀጣይ ለማድረግም የልማት ሥራዎቿን ማስፋፋት የግድ ይላታል። ይህንን መሠረታዊ ሁኔታ በሚገባ የተረዱት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ በተለያዩ ቦታዎች ተበጣጥሰው የነበሩ የቤተ ክርስቲያን ይዞታዎችን ሰብስበ አድርጎ በአንድ ቦታ በማጠቃለል ታላላቅ የግንባታ ሥራዎችን

እንድትሠራ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ተቋቁሞ የነበረው የኮሪደር ልማት ኮሚቴ ባቀረበው ሐሳብና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በፈጠረው ምቹ ሁኔታ አማካኝነት በከተማችን በሦስት ቦታዎች ላይ የግንባታ ሥራዎችን ማከናወን እንደሚገባት በመገንዘብ በአራት ኪሎና በፒያሳ አካባቢ አዳዲስ የግንባታ ሥራዎችን አስጀምራለች።

እነዚህ በአራት ኪሎና በፒያሳ አካባቢ የሚገነቡት የቤተ ክርስቲያናችን ሁለገብ ሕንጻዎች ሲሆኑ፤ በተለይም በአራት ኪሎ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ፊት ለፊት የሚገነባውና «ቤተ አበው» በሚል ስያሜ በ6000 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የተንጣለለው ሕንጻ እጅግ ግዙፍና በርካታ ቢሊዮን ብር ወጪን የሚጠይቅ ነው። የግንባታ ሥራው በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ሜጋ ፕሮጀክት ሲሆን፤ እጅግ ዘመናዊ መኖሪያ ቤቶች፥ የመኪና ማቆሚያ፥ ሱቆችና ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰጡ ግብአቶችን የያዘ ፕሮጀክት ነው።

ብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ በቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ውሳኔ የሚገነቡትን እነዚህን ሕንጻዎች በልዩ ሁኔታ የሚከታተሏቸውና የሚገመግሟቸው ሲሆኑ፤ በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ ይጠናቀቃሉ ተብሎ ይጠበቃል። ሁሉም ሕንጻዎች በሚጠናቀቁበት ጊዜም በከተማችን የሚስተዋለውን የመኖሪያ ቤት ችግር በመቅረፍ ረገድ ትልቅ አስተዋፅኦ ከማድረጋቸውም በላይ ለቤተ ክርስቲያናችን ተጨማሪ የገቢ ምንጭ በመሆን መንፈሳዊ አገልግሎቷን እንድታሳልጥ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋሉ።

እነዚህ በብፁዕነታቸው ዘመነ ሢመት የተጀመሩ የግንባታ ሥራዎች በአግባቡና በተያዘላቸው ጊዜ መጠናቀቅ እንዲችሉ በዘርፉ የተሠማራችሁ ባለሙያዎች፥ ሥራውን በማከናውን ላይ የምትገኙ የሕንጻ ተቋራጮችና አማካሪ ድርጅቶች በኃላፊነት መንፈስና ሥራው የቤተ ክርስቲያን መሆኑን በመረዳት ፍጹም በሆነ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ለሥራው ትኩረትና ጊዜን በመስጠት፥ ከዚህ ቀደም በፕሮጀክቶች መጓተት ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ዋጋ እንድትከፍል የተደረገበትን ሂደት በማረም እውነትም የቤተ ክርስቲያን ልጆች መሆናችሁን ማስመስከር ይኖርባችኋል።

እነዚህን ፕሮጀክቶች ለማከናውን የሥራ ዕድል የተፈጠረላችሁ የሕንጻ ተቋራጮችም ዕድሉ የተሰጣችሁ የቤተ ክርስቲያን ልጅነታችሁን ታሳቢ በማድረግ መሆኑን በመገንዘብና ነገ በታሪክና በእግዚአብሔር ፊት መቆም እንደሚኖር በማወቅ የቤተ ክርስቲያን ሀብት ትርጉም ባለው መልኩ ተጨማሪ ሀብት በመፍጠር ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መጠናከር እንዲውል የሚደረገውን ጥረት ተረድታችሁ፥ ከብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጃችን ጎን በመቆም ሥራው በተቀላጠፈና ጥራቱን በጠበቀ መልኩ እንዲከናወን እንድታደርጉ አደራ የተጣለባችሁ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እንወዳለን።







አማካሪ ድርጅቶችም ሥራው የቤተ ክርስቲያን እንጂ ተራ የግንባታ ሥራ አለመሆኑን በመገንዘብ እያንዳንዱን ሂደት በሚገባ በመፈተሽ ሙያዊ ብቃታችሁን ተጠቅማችሁ የቤተ ክርስቲያን ጥቅም መከበር እንዲችል ዝርዝር ሥራዎችና አፈጻጸሞችን በሚገባ በመፈተሽ እንዳለፉት ግንባታዎች ሥራዎች እንዳይጓተቱ፥ የጥራት ጉድለት እንዳይታይባቸው በማድረግ መንፈሳዊ ግዴታችሁን ጭምር በመወጣት የዚህ ታሪካዊ ግንባታ አካል መሆናችሁ የሚያኮራችሁና የሚስደስታችሁ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅባችኋል። የቤተ ክርስቲያናችን መሐንዲሶችም ሥራው ደመወዝ የምታገኙበት ጉዳይ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በዘመናችሁ የምትወቀሱበትና የምትመሰገኑበት፥ መንፈሳዊ ግዴታችሁን ጭምር የምትወጡበት ፕሮጀክት መሆኑን አውቃችሁ ሥራችሁን በኃላፊነት መንፈስ እንድታከናወኑ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አደራዋን እንደጣለችባችሁ መረዳት ይኖርባችኋል።

በአጠቃላይ እነዚህ ግዙፋን የቤተ ክርስቲያናችን ፕሮጀክቶች በብዕዕነታቸው ዘመነ ሚሞት የተጀመሩና በመልካም አፈጻጸም ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ ብዕዕነታቸው በቀሪ ዘመነ ሚሞታቸው ለበለጠ ውጤት እንደሚያበቋቸው በመተማመን፥ እነዚህ ሦስት ሕንጻዎች የብዕዕነታቸው ስኬታማ አመራር ማሳያዎች ተደርገው ባለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት ስኬቶች ጋር በታሪክ ተመዝግበዋል።

የአራት ኪሎ መጥምቃውያን ቤተ ክርስቲያን

በቀደመው ዘመን የቤተ ክርስቲያናችን ሀብትና ንብረት በመሆን የሚታወቀው «የአራት ኪሎ መጥምቃውያን ቤተ ክርስቲያን» የሚገለገልበት ቤት በደርግ ዘመን ቤቱን ሊጠብቁ የነበሩ መነኮሴ ተገድለው የተወረሰ አንጡራ የቤተ ክርስቲያናችን ሀብት መሆኑ ይታወቃል። ይሁን እንጂ ይህ የቤተ ክርስቲያን ሀብት በቤተ ክርስቲያናችን ቅጽረ ግቢ የሚገኝ እንደመሆኑ፥ ለቤተ ክርስቲያን እንዲመለስ ለማድረግ በርካታ ጥረቶች ቢደረጉም በውስጥና በውጭ ችግሮች ምክንያት ቤቱ ሳይመለስ ቆይቷል።

ይህ ብዙዎችን ያስቆጨ፥ ብዕዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስን ተስፋ ያስቆረጠ የይዞታ ይመለስልን ጥያቄ ለዘመናት ሲንከባለል ቆይቶ፥ በብዕዕ አቡነ ሳዊሮስ ዘመነ ሚመት ዕልባት ማግኘት ችሏል። ይህ በበርካታ ውጣ ውረድና በውስጥና በውጭ ችግሮች ተተብትቦ የቆየው የይዞታ ይመለስልን ጥያቄ በብዕዕነታቸው በሳልና ቆራጥ አመራር ሊመለስ የቻለው፦ በቂ ማስረጃ በመያዝና በማደራጀት፥ ምክንያታዊ የማስረዳት ሂደትና ከከተማ አስተዳደሩ ጋር ውይይት በማድረግ ሲሆን፤ የከተማ አስተዳደሩም ችግሩን ለመፍታት ቅንነትና ቁርጠኝነት በማሳየቱ ምክንያት ነው።

ይህ ይዞታ ለቤተ ክርስቲያን እንዲመለስ በሕግና በአስተዳደር ዘርፍ ለበርካታ ዓመታት የተደረገው ጥረት ፍሬ ማፍራት ያልቻለው ጉዳዩ ዕልባት ሊያገኝ ሲል በጥቅም ትስስር ቤተ ክርስቲያን የምትሸነፍበት ሥራ እየተሠራ እንደሆነ የማያውቅ የቤተ ክርስቲያን አመራር የለም። ቤተ ክርስቲያን ደመወዝ የምትከፍላቸው የሥራ ኃላፊዎች ከመጥምቃውያን ሰዎች ጋር ግምባር በመፍጠር የቤተ ክርስቲያን ጥቅም እንዳይከበርና ይዞታዋ እንዳይመለስ በብርቱ ሠርተዋል።

ብዕዕ አቡነ ሳዊሮስ ወደ ጠቅላይ ቤተ ክህነት በአመራርነት ከመጡ በኋላም ችግሩን በመፍታት የቤተ ክርስቲያንን ጥቅም ለማስከበር ረጅም ርቀት ከተጓዙ፥ ክብርት ከንቲባ አዳነች አቤቤና ካቢኔያቸው የቤተ ክርስቲያን ጥያቄ ተገቢነት ያለውና ምላሽ ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን በማመን በካቢኔ ውሳኔ ሰጥተው

ቦታውን ለቤተ ክርስቲያን ለማስረከብ ይቻል ዘንድ ለአራት ኪሎ መጥምቃውያን ቤተ ክርስቲያን ተለዋጭ ቦታ ከሰጡ በኋላም ቢሆን፥ በቀደመ ታሪካቸው የቤተ ክርስቲያን ይዞታ እንዳይመለስ ሲያደርጉ የነበሩ የቤተ ክህነቱ የሥራ ኃላፊዎች ካለፈው ክፉ ታሪካቸው ሳይማሩ አሁንም ውስጣዊ የሴራ ሥራ በመሥራት መጥምቃውያኑ የፍርድ ቤት ዕግድ እንዲያመጡ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር 'ከቤተ ክርስቲያን እየጐረሱ ከመጥምቃውያን የሚውጡ' ጥቅመኞች ችግር ፈጥረው እንደነበር አይዘነጋም።

ይሁንና ችግሩ እንደተፈታ ቦታው ለቤተ ክርስቲያን እንዳይመለስ፥ ይልቁንም ደግሞ በብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ዘመነ ሢመት እንዳይመለስ የሚፈልጉ አንዳንድ የቤተ ክህነቱ የሥራ ኃላፊዎች እንቅስቃሴ በተጠናከረ መልኩ እየቀጠለ መሆኑን የተረዱት ብፁዕነታቸው፥ ጉዳዩን በምሥጢር በመያዝና የራሳቸውን አካሄድ በመከተል ባደረጉት ጥረት መጥምቃውያኑ ያመጡ 'ሑከት ይወገድልን' ቀሪ እንዲሆን በማድረግ፥ ይጠቀሙበት የነበረው በቆርቆር የተሠራ አዳራሽ እንዲያፈርሱ ተደርጎ ቦታው በቤተ ክህነቱ ቅጽረ ግቢ ተካቶና አጥሩ ታጥሮ ርክክብ ተፈጽሟል።

ይህ ለአለፉት ሃምሳ ዓመታት ከቤተ ክርስቲያን ተነጥቆ የነበረ ሕጋዊ ይዞታ ለቤተ ክርስቲያን እንዲመለስ የተደረገው በብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጃችን ጥረትና በከተማ አስተዳደሩ ቀና ትብብር ሲሆን፤ በርካታ ውጣ ውረዶችን አልፎ እዚህ ደረጃ እንዲደርስ ትልቁን ሚና የተጫወቱት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ምስጋና ይገባቸዋል። ክብርት ከንቲባ አዳነች አቤቤና ካቢኔያቸውም የቤተ ክርስቲያናችንን የዘመናት ጥያቄ በመመለሳቸው ክብርና ምስጋና ሊቸራቸው ይገባል። እናም ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ባለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት ካከናወኗቸው በርካታ ስኬታማ ሥራዎች የላቀውና በትውልድ ሁሉ ሲታወሱ እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው ይህ ተግባር፥ በቤተ ክርስቲያናችን የታሪክ መዝገብ ተመዝግቦ ሲተረክ የሚኖር ሲሆን፤ የሃምሳ ዓመታት ችግር በብፁዕነታቸው ዕልባት ማግኘት መቻሉ በቀላሉ የሚታይ እንዳልሆነ ጭምር ታሪክ መዝግቦት እንዲቀመጥ የዚህ ጽሑፍ አካል አድርገነዋል።

የቢሮዎች ጽዳት

የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ ሥራዎች የሚከናወኑባቸው ቢሮዎች ዘመኑን የሚመጥኑና ውብና ማራኪ እንዲሆኑ ማድረግ የቤተ ክርስቲያን ክብር ጭምር የሚገለጽባቸው በመሆናቸው ምክንያት የግድ ሊጸዱና ሊዋቡ ይገባ ነበር። በተለይም የብፁዕ ሥራ አስኪያጁና የብፁዕ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሓፊ ቢሮዎች በርካታ እንግዶች፥ የመንግሥት ባለሥልጣናት፥ ዲፕሎማቶችና የሃይማኖት አባቶች የሚስተናገዱባቸው በመሆናቸው የቤተ ክርስቲያናችንን ሉዐላዊነትና ታላቅነት በሚመጥን መልኩ መደራጀት፥ መዋብና በማቴርያል መሟላት ይኖርባቸዋል።

ይህንን እውነታ የሚረዱት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስና ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ቢሮዎቻቸውን በዘመናዊ መልኩ በማስዋብና በማደራጀት ቤተ ክርስቲያናችንን የሚመጥኑ እንዲሆኑ አድርገዋቸዋል። ቢሮዎች በሚገባ የተደራጁት፥ የተዋቡትና ቤተ ክርስቲያንን ሊመጥኑ የሚችሉ እንዲሆኑ ተደርገው የተሠሩት በባለሙያዎችና በበጎ አድራጊ ምእመናን ወጪያቸው ተሸፍኖ መሆኑ ደግሞ ሁለቱ አባቶች ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ ሥራ ለመሥራት የሚችሉ መሆናቸውን ያረጋገጡበት እውነታ ነው።

ቢሮዎቹ በአሁኑ ጊዜ ለሥራ፥ ለስብሰባ፥ ለሚድያ ኮንፈረስ እንዲሁም የክብር እንግዶችን በተገቢው መልኩ ለማስተናገድ በሚያስችል ሁኔታ ተደራጅተውና ተውበው የሚገኙ ሲሆን፤ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ቅጽረ ግቢን ለማስዋብ ከተደረገው ጥረትና ከተገኘው ውጤት ጋር ሲተያይይ ቢሮዎቹና ቅጽረ ግቢው የቤተ ክርስቲያናችንን ክብርና ልዕልና የሚመጥኑ መሆን ችለዋል።

ይህ ደግሞ የብፁዕነታቸው ያለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት የሥራ አፈጻጸም ውጤት በተግባር የተመዘገበበት በመሆኑ በቤተ ክርስቲያናችን የዘመናዊ አስተዳደር ሥርዐት ግንባታ ውስጥ አጠቃላይ የዲጂታል ሥርዐትና የመሠረት ልማት ዝርጋታ ጋር በቅርቡ እውን ከሚደረገው የቴክኖሎጂ ሥርዐት ትግበራ ጋር ተዳምሮ ብፁዕነታቸውን የዘመናዊ ቢሮ፥ አሠራርና አደረጃጀት ባለቤት በማድረግ በቤተ ክርስቲያናችን የዘመናዊ አስተዳደር ሥርዐት ዝርጋታ ውስጥ ዳግም በወርቅ ቀለም ተጽፎ ታሪካቸው በትውልድ ዘንድ ሲዘከር እንዲኖር እነሆ የዚህ ታሪካዊ መጽሔታችን አካል በማድረግ ዘግበነዋል።

የኦፅሲቲና የዲጂታል ቴክኖሎጂ ሥርዐት ግንባታ በቤተ ክርስቲያን፤

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዶግማዋን፥ ቀኖናዋንና ሥርዐቷን በጠበቀ መልኩ መንፈሳዊ አገልግሎቷን ለማጠናከር ከምታከናውናቸው በርካታ ተግባራት መካከል ዘመኑ የደረሰበት የአይሲቲና የዲጂታል ሽግግር ሥራ ዋነኛው መሆኑ ይታወቃል።

ይህ ሥራ በዚህ የቴክኖሎጂ ዘመን ወሳኝና እጅጉን አስፈላጊ መሆኑን የተረዱት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ፥ ሥራውን በበላይነት የሚመራና የሚያስተባብር ጽ/ቤት በማቋቋም ወደ ሥራ እንዲገባ አድርገዋል።



የዲጂታል ሥርዐቱ አካል እንዲሆኑ የሰጡትን አመራር ተከትሎ፥ ሰነዶቹን የማደራጀት፥ የመለየትና ወደ ዲጂታል የመቀየሩ ሥራ በመከናወን ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ ለዚሁ አገልግሎት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በሚገባ በማሟላትም የቤተ ክርስቲያን ሰነዶች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ጭምር ተደራጅተው እንዲቀመጡ የማድረግ ሥራን እየሠሩይገኛሉ።

ይህ ወቅትና ጊዜን ዋጅቶ ቤተ ክርስቲያንን ከአዲሱ ትውልድ ጋር በቀላሉ የሚያዋሕድ ቤተ ክርስቲያን እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስም የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንድትሆን ጥብቅ መመሪያን አስተላልፈዋል።

ሥራውን የበለጠ ውጤታማ ማድረግ ይቻል ዘንድ የአይሲቲ ፖሊሲ፥ የአይሲቲ መምሪያ ማቋቋሚያ ደንብ፥ የአይሲቲ የአምስት ዓመታት ስትራቴጂካዊ ዕቅድና የአይሲቲና የዲጂታል ሽግግር አማካሪ ኮሚቴ የሥራ መመሪያ በቅዱስ ሲኖዶስ እንዲጸድቅና ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግም ስኬታማ ሥራን ሠርተዋል። በዚህም በቤተ ክርስቲያን መዋቅር ውስጥ ያሉና በየጊዜው የሚከናወኑ ከኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማቶች ጋር የተያያዙ ማናቸውም ዓይነት ተግባራትም ቅዱስ ሲኖዶስ ባወጣቸው የአይሲቲ ፖሊሲና መመሪያዎች መሠረት ብቻ መከናወን እንደሚኖርባቸው መመሪያ አስተላልፈዋል።

ቤተ ክርስቲያን የዘመናዊ አሠራር ሥርዐት ባለቤት እንድትሆንና አዲሱ ትውልድ ዘመኑን በዋጀ መልኩ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት እንዲያስፋፋ የሚያደርግ መሠረት በመጣልም ለዘመናዊ የአሠራር ሥርዐት ዝርጋታ ልዩ ትኩረት የሰጡ ባለ ራእይ አባት መሆናቸውን ያረጋገጠ ተግባር በመፈጸምም በቤተ ክርስቲያን የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ሥርዐት ዝርጋታ ውስጥ ስማቸው በወርቅ ቀለም ተጽፎ በመጪው ትውልድ ሊዘከር ግድ ሆኖ የዚህ ታሪካዊ መጽሔት አካል ሆኗል።

በሌላኛው ጫፍ ደግሞ ቤተ ክህነቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የነበሩ ፋይሎች፥ መዝገቦች፥ ታሪካዊ ሰነዶች፥ የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔዎች፥ የአስተዳደር ጉባኤ ቃለ ጉባኤዎች፥ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት፥ ከዓለም አቀፍ ተቋማት፥ ከአህት አብያተ ክርስቲያናት ወዘተ. ጋር ያደረገቻቸውን ግንኙነቶች የሚገልጹ ሰነዶች በመዝገብ ቤትና ለአደጋ በተጋለጠ ሁኔታ መቀመጡ አግባብ አለመሆኑን የተገነዘቡት ብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ሰነዶቹ ወደ ዲጂታል ሥርዐት እንዲለወጡ፥ አስፈላጊው ሰነዶች በሙሉ ተለቅመው እንዲደራጁና አሠራር እንዲዘረጋ ብዙ ጊዜ ብዙዎች የጠየቁት፥ ምላሽ ያላገኙለትና በዚህ ጊዜ ምላሽ ያገኘል ብለው ያላሰቡት ቢሆንም፤ በብፁዕነታቸው አርቆ አሳቢነት፥ የአመራር ጥበብና ብቃት ተግባራዊ ምላሽ ያገኘ የዐሥራ ስድስቱ ወራት ስኬታማ የሥራ ውጤት ሆኖ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተመዝግቧል።

የጎንደር ረቃውንትና ብፁዕ ጠቅላዩ ሥራ አስኪያጁ፤

በ2018 ዓ.ም ጥር ወር ላይ በጎንደር ሐዋርያዊ ጉዞ በማድረግ የጥምቀት በዓልን በዚያ ያከበሩት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ፥ የደቡብ ምዕራብ ሸዋና የሸገር ከተማ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፥ በጎንደር የመ/መ/መድኀኔ ዓለም የፀ፟ቱ መጻሕፍት ጉባኤያት ትርጓሜ ምስክር ቤትን የጎበኙ ሲሆን፤ በዚሁ ጊዜ ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ የመ/መ/መድኀኔ ዓለም የፀ፟ቱ ጉባኤ መጻሕፍት ትርጓሜ ቤት ምስክር መምህርና የደብሩ አስተዳዳሪ፥ የጉባኤ ቤቱን ታሪክና አሁናዊ ሁኔታ በማስመልከት ገለጻ አድርገውላቸዋል።



በዚሁ ጊዜ የጉባኤ ቤቱ መምህር ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ ወርኃዊ ደመወዝ ብር 3,200 ብቻ እንደሆነና መምህሩ ከሚሰጡት አገልግሎትና ካላቸው መንፈሳዊ ዕውቀት አንጻር የሚከፈላቸው ደመወዝ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን በመግለጽ የሀገረ ስብከቱ የሥራ ኃላፊዎችና ተማሪዎች የደመወዛቸውን ጉዳይ አደራ በማለት ላቀረቡት ጥያቄ፥ ብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ በእጅጉ በማዘን "እናየዋለን፤" በማለት ምላሽ ሰጧቸው።

በጎንደር የነበራቸውን ሐዋርያዊ አገልግሎት አጠናቀው ወደ አዲስ አበባ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የተመለሱት ብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ፥ የካቲት 2 ቀን 2018 ዓ.ም በሰጡት ትእዛዝ ለሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ የብር 11,800 ጭማሪ በማድረግ ደመወዛቸውን ወደ ብር 15,000 (ዐሥራ አምስት ሺህ ብር) ከፍ እንዲል አድርገውላቸዋል። በተጨማሪም በወር 90 ብር ይከፈላቸው ለነበሩ ምክትል መምህራን ደግሞ ብር 4,910 ተጨማሪ በማድረግ ደመወዛቸው ብር 5,000 (አምስት ሺህ) እንዲደርስ ሲያደርጉ፤ ምንም ዓይነት ደመወዝ ላልነበራቸው ለመምህር ፍቅረ ማርያም ጌትነት፥ ለመምህር ዲበኩሉ ስጦታው፥ ለመምህር ዘለዓለም አዲስ፥ ለመምህር ሙሴ ባየ ለእያንዳንዳቸው ብር 4,910 (አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዐሥር) በጀት በመፍቀድ ከየካቲት 2018 ዓ.ም ጀምሮ እንዲከፈላቸው በማድረግ በጎንደር የገቡትን ቃል በመተግበር ለዘመናት አስታዋሽ አጥተው የኖሩ ዐይናማ መምህራንን ዕንባ በማበስ የአብነት መምህራን ዋስ ጠበቃ መሆናቸውን በተግባር ያሳዩ ሲሆን፤ ለጉባኤ ቤቱ ማጠናከሪያ ይሆን ዘንድ የአንድ ሚሊየን ብር ድጋፍም አድርገዋል።

ከዚህ በተጨማሪ በማእከላዊ ጎንደር ሀገረ ስብከት ደብረ ኃይል ወደብረ ጥበብ በዓታ ለማርያም ካቴድራል ከ1500 በላይ መምህራን በማስተማርና በማስመረቅ ያለምንም ዕረፍት ቀንና ሌሊትም ለረጅም ዓመታት እያስተማሩ የሚገኙት መጋቤ አዕላፍ ክቡር ጥላሁን ቤተ ክርስቲያን አሉኝ ከምትላቸው አንጋፋ መምህራን መካከል ግንባር ቀደሙ ሲሆኑ፤ በወር የሚከፈላቸው ደመወዝ ብር 1,200 ሲሆን፤ ብር 13,000 ተጨምሮ በየወሩ ብር 15,000.00 /ዐሥራ አምስት ሺህ/ ከሐምሌ ወር 2018 ዓ/ም ጀምሮ እንዲከፈላቸው አድርገዋል።

በሌላ በኩል በማእከላዊ ጎንደር ሀገረ ስብከት መካነ ስብሐት ቅድስት ልደታ ለማርያም አራቱ ጉባኤያት መምህር የሆኑት አራት ዐይና መምህር ቆሞስ አባ ገብረ ማርያም ጌጡ ምንም ዓይነት ደመወዝ ያልነበራቸው ሲሆን፤ በወር ብር 15,000 (ዐሥራ አምስት ሺህ) እንዲበጀትላቸው አድርገዋል። በተጨማሪም ለምክትሎቻቸው ለመ/ር ጥበቡ ሰሎሞን፥ ለመ/ር መሠረት አገኘው፥ ለመ/ር ሳሙኤል ስንታየሁና ለመ/ር አብርሃም ደሳለኝ ለእያንዳንዳቸው በየወሩ ብር 5,000.00 /አምስት ሺህ ብር/ ከሐምሌ ወር 2018 ዓ/ም ጀምሮ እንዲከፈላቸው አድርገዋል።

ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ዘመን የማይሽራቸው ወርቃማ ውሳኔዎችን በማስተላለፍ የሊቃውንቱን ማቆሚያ ያጣ ዕንባ ያበሱት ብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ፥ በጎንደር ነሐሴ 30 ቀን 2018 ዓ.ም «በቤተ ክርስቲያን የወደፊት ጉዞ፥ የቤተ ክርስቲያን አባቶችና የወጣቶች ሚና» በሚል ርእስ የተዘጋጀውን ሥልጠና ሙሉ ወጪ በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት እንዲሸፈንና ከማድረጋቸውም በላይ፥ አሠልጣኝ መምህራንን በመመደብ ጭምር የተሳካ ሥልጠና እንዲሰጥ በማድረግ የጎንደር ሊቃውንት በተጠቀሰው ርእሰ ጉዳይ መፍትሔ የሚሆን አቅጣጫ ያስቀመጠ የአቋም መግለጫ በማውጣት ሥልጠናቸውን እንዲያጠናቅቁ አድርገዋል።

በአጠቃላይ ብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ባለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት በመንፈሳዊ፥ በአስተዳደራዊ፥ በልማታዊ፥ በማኅበራዊና በቴክኖሎጂ ሽግግር ዘርፎች ካመስመዘገቧቸው እጅግ ውጤታማ ተግባራት መካከል የብዙዎችን ቀልብ የሳበና የዘመናት የሊቃውንትን ዕንባን ያበሰው የአብነት መምህራን ደመወዝ ጭማሪ ጉዳይ እጅጉን የሚያስደስትና ለጎንደር ሊቃውንት ትልቅ ተስፋ የሆነ ተግባር ከመሆን አልፎ፥ ብፁዕነታቸውን በሊቃውንቱ ዘንድ የማይረሱ አባት የሚያደርጋቸው በመሆኑ፥ ይህ የሊቃውንቱን አንጀት ያራሰ ድንቅ ሥራቸው የታሪካቸው አካል ሆኖ በትውልድ ዘንድ ሲዘከር እንዲኖር እነሆ በዚህ መልኩ ለንባብ ስናቀርበው፥ ብፁዕነታቸው ባለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት በገዘምታ ያሳኩት ትልቁ ሥራቸው በመሆን ታሪክ እንዲመዘግበው ለማድረግ ነው።

ተግዳሮቶች

ከፍ ሲል ባለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት የተመዘገቡ የመልካም አስተዳደርና የልማት ሥራዎች ሁሉ አልጋ በአልጋ በሆነ ሁኔታ፥ ያለምንም ችግርና እንቅፋት የተከናወኑ አይደሉም። ይልቁንም በበርካታ ተግዳሮቶች የታጀቡ፥ በፈተናና እልህ አስጨራሽ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ታልፎ የተከናወኑ በመሆናቸው ውጤታቸው እጅጉን ያማረና የሰመረ መሆን ችሏል። በእርግጥ የቤተ ክህነታችንን ሁለንተናዊ ጥንካሬና ድክመት፥ የአመራሮችን አቅምና ችሎታ ጠንቅቀው የሚያውቁት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ፥ የገጠሟቸውን ተግዳሮቶች ሁሉ በብልሃት፥ በትዕግሥትና በኃላፊነት መንፈስ በመሻገር ያስመዘገቧቸው ውጤቶች መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል።

በእነዚህ ዐሥራ ስድስት ወራት ውስጥ በርካታ አሉባልታዎች፥ የፈጠራ ወሬዎች፥ የግጭት ጥንሰሶች፥ የሚድያ ዘመቻዎች፥ አድማዎችና ስም ማጥፋቶች በስፋት ሲሰነዘሩ የቆዩ ቢሆንም፥ ብፁዕነታቸው ዋና ትኩረታቸውን በሥራ ላይ ብቻ ማድረግ በመቻላቸው ባለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት የተመዘገቡት ውጤቶች በዓመታት፥ አንዳንዶቹም በዘመናት የማይፈጸሙ ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ከሁሉም ስኬቶች ጀርባ የብፁዕነታቸው ታጋሽነት፥ ሀቀኛነትና የዓላማ ጽናት በጉልህ ወጥቶ ታይቷል። በተለይም ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስን ከብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ጋር ለማለያየትና ለማጣላት የተደረገው ጥረት ዓላማና ግቡ ለብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ በሚገባ ግልጽ ስለነበር፥ የፀብ አጫሪዎችን ተንኮል በመበጣጠስ አንድነታቸውን አጽንተው መያዝ በመቻላቸው አዛኝ መስለው ሥራቸውን ለማበላሸት ሲጥሩ የቆዩትን መሰሪዎች ሐሳብ ያመከኑ፥ በአንድነት ውስጥ ውጤታማነትን ማረጋገጥ እንደሚቻል ያሳየ ድንቅ ተግባር ፈጽመዋል።

ከሦስት ዐሥርተ ዓመታት በላይ የዘለቀ ወንድማማችነትን ለመናድና ዘመነ ሢመታቸውን በንትርክና በጭቅጭቅ እንዲጨርሱ በማድረግ፥ ቀድሞም አቅመ ቢስ እንደሆኑ አድርገው ያስወሩትን ወሬ እውነት ለማስመሰል ሌት ከቀን ሲደክሙ የነበሩትንም ሐሳባቸውን በማምከን ከወንድማቸው ከብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ጋር በመቆም የአቅም ብቻ ሳይሆን የወንድምነትን ልክ በማሳየት ጀግና መሪ መሆናቸውን ያሳዩ ድንቅ አባት ናቸው።

ይህን ሁሉ እምቅ አቅም የያዙት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ በሰው እንደሚመሩ ለማስመሰል፥ ከጀርባቸው እገሌ የሚባል ሰው እንደሚዘውራቸው በማስወራት ዘመነ ሢመታቸውን ለማመስ ላይ ታች ሲሉ የሰነበቱ ድኩማንም ብፁዕነታቸው ሠርተውና መርተው የሚታይና የሚዳሰስ ውጤት በማስመዝገብ በድል አድራጊነት በወጡ ማግስት፥ ኔትወርክ ዘርግተው፥ የሚድያ ሠራዊት አዝምተው ራሳቸውን እንደ ጻድቅ በመቁጠር ቤተ ክርስቲያንን ሲያቆረቁዙ የነበሩትን ሁሉ የሚገባቸውን ዋጋ በመስጠት፥ ዳግም ባለ ሙሉ አቅም መሪ መሆናቸውን በተግባር አሳይተዋል።

እናም ብፁዕነታቸው በሴረኞች የተተበተበውን ተግዳሮት በጥበብና በብልሃት በመፍታት ቤተ ክርስቲያንን በሚገባት ደረጃ ላይ ለማድረስ የሚሠሩ፥ ሠርተው ውጤት የሚያስመዘግቡ ባለ ብሩህ አእምሮ የሥራ መሪና ጠንካራ መንፈሳዊ አባት በመሆን ያለፉትን ዐሥራ ስድስት ወራት በስኬት የመሩ ድንቅ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ በመሆን ታሪክ እንደሚያስታውሳቸው አያጠራጥርም።

ማጠቃለያ

የብፁዕ አቡነ ሳዊሮስን ያለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት የሥራ አፈጻጸም በመጠኑ በቃኘንበት በዚህ ጽሑፋችን ሁሉንም ሥራዎቻቸውንና ውጤቶቹን በዝርዝር ለማቅረብ ጊዜና ቦታ የማይበቃን ስለሆነ በዚህ መልኩ ለማጠቃለል ተገደናል።

ከፍ ሲል በወፍ በረር እንደቃኘነው፥ ብፁዕነታቸው ውጤታማ ሥራዎችን ያከናወኑት፦ ጥበብን፥ የመሪነት አቅምንና መንፈሳዊነትን ታጥቀው እንደሆነ የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ በሚገባ ይገነዘባል። በተለይም ባለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት የተከናወኑ የብፁዕነታቸው ሥራዎች ፍሬያማ መሆን የቻሉት ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖትና ከብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሓፊና የራያ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ጋር በመናበብና በፍጹም መቀናጀት መሥራት በመቻላቸው፥ እንዲሁም ሥራዎቻቸውን ሁሉ በቋሚ ሲኖዶስና በአስተዳደር ጉባኤ በማስወሰን በመሥራታቸው ምክንያት እንደሆነ ጥርጥር የለውም።

ብፁዕነታቸው በዘመነ ሢመታቸው በጋራ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ከተጠሩት ከብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ጋር በመመካከር፥ ከጠቅላላ ቤተ ክህነት ድርጅቶችና መምሪያ ኃላፊዎች ጋር ተልዕኮ ሰጥቶ በመቀበል የአመራር ጥበብ ሥራቸውን በመምራታቸው ምክንያት ያለፉት ዐሥራ ስድስት ወራት እጅግ ውጤታማ ሥራ የተመዘገበባቸው ወራት በመሆን በብፁዕነታቸውና በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ በጉልህ የወርቅ ቀለም ተጽፎ ለትውልድ የሚተላለፍ ስኬት አስመዝግበዋል።

እኛም ዘመናዊውን የቤተ ክርስቲያናችንን አዳራሽ ምርቃት በማስመልከት የምናውቀውንና ያየነውን መሠረት በማድረግ ያዘጋጀነውን ጽሑፍ የምንቋጨው ከብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁችን መልካም የሥራ ጊዜና መልካም አዲስ ዓመት እንዲሆንላቸው በመመኘት ነው።



የቤተ ክርስቲያናችንን ታሪክና ክብር የሚመጥን ዓለም አቀፍ የስብሰባ ማእከል

በተመስገን ቸማስ

መግቢያ

ጥንታዊት፥ ታሪካዊትና ብሔራዊት የሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከመንፈሳዊ ተልዕኮዋ ባሻገር፥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየዘመነ ከመጣው ዓለም አቀፍ ቴክኖሎጂና ተቋማዊ አደረጃጀት እመርታ ጋር በአብሮነት ለመጓዝ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እያደረገች ትገኛለች። ለአብነትም የራሷ ዘመናዊ መድረክ ባለቤት ለመሆን በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ቅጽር ያስጀመረችውን እጅግ ታላቅና በቴክኖሎጂ ውጤቶች የደረጀ ዘመናዊ የስብሰባ ማእከል ግንባታ ከፍጻሜ በማድረስ የላቀ ታሪክ አስመዝግባለች።

በዚህ ጽሑፍ በአባቶቻችን ጸሎት፥ በቤተ ክርስቲያኒቱ ከፍተኛ አመራሮች ትጋትና ቁጥጥር፥ በግንባታ ድርጅቱና በአማክሪ መሐንዲሶች ድምር ጥረት ዛሬ ለምርቃት የበቃው ግዙፍ የስብሰባ ማእከል፥ ከዕንሰ-ሐሳብ እስከ ፍጻሜው የተጓዘበትን ውስብስብና እልህ አስጨራሽ ሂደት፥ እንዲሁም ማእከሉ ዘመናዊ የሥነ-ሕንጻ ንድፍን ከዲጂታል ቴክኖሎጂ ጋር በማጣመር የደረሰበትን አመርቂ ደረጃ በአጭሩ ለመዳሰስ ተሞክሯል።

ይህ ዓለም አቀፍ የስብሰባ ማእከል የቤተ ክርስቲያኒቱን ታሪክና ክብር የሚመጥን ሆኖ በመቆሙ ከሚያሳድረው ልዩ መንፈሳዊ ኩራት በተጓዳኝ፥ የኦርቶዶክሳውያን ጽኑ ምልክት ሆኖ ለቀጣዩ ትውልድ የሚተላለፍ ሕያው ምስክር ይሆናል።

ክፍል 1

ዓለም አቀፍ የስብሰባ ማእከሉ አስፈላጊነት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጥንታዊነቷ፥ በሰፊ የታሪክና የባህል አሻራዋ እንዲሁም በብዙ ሚሊዮኖች በሚቆጠሩ ምእመናኖቿ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ የምትጫወተው ሚና እጅግ የጎላ ነው። ይህንን ታሪካዊ፥ መንፈሳዊ፥ ባህላዊና ማኅበራዊ አገልግሎቷን በዘመናዊ አሠራርና በላቀ ከፍታ ለማከናወን፥ ጠንካራና የዘመኑን ዕድገት የሚመጥን ተቋማዊ አደረጃጀት አስፈላጊ በመሆኑ፤ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የቤተ ክርስቲያኗ ማእከላዊ አስተዳደር፥ የመንፈሳዊ መመሪያዎች ማፍለቂያና የታላላቅ ውሳኔዎች ማእከል በመሆን ላለፉት ረጅም ዘመናት ወሳኝ አባታዊና ተቋማዊ ድርሻ ሲወጣ ቆይቷል።

በጊዜ ሂደት የቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን ቁጥር እጅግ ከመጨመሩም በላይ፥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላት መንፈሳዊ ተፅዕኖ፥ የአህጉረ ስብከት ስፋትና ከሌሎች አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ አብያተ ክርስቲያናትና ድርጅቶች ጋር ያላት ግንኙነት በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ መጥቷል። ይህንን እያደገ የመጣውን ሰፊ ተቋማዊና ዓለም አቀፋዊ እንቅስቃሴ በብቃት ማስተናገድ ይቻል ዘንድ፥ ከዘመኑ ቴክኖሎጂና የሥልጣኔ ደረጃ ጋር

የሚሄዱ ዘመናዊ መሠረተ ልማቶችን መገንባትና ማስፋፋት አማራጭ የሌለው አጣዳፊ ተቋማዊ አስፈላጊነት ሆኖ ተገኝቷል።

የቤተ ክርስቲያኗ ከፍተኛ የውሳኔ ሰጪ አካል የሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ ዓመታዊና ድንገታዊ ጉባኤያቱን ዘመናዊ የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች ታግዞ የሚያካሂድበት፥ ከዓለም ዙሪያ የተውጣጡ በሺዎች የሚቆጠሩ የሰበካ ጉባኤ ተወካዮች የሚሳተፉባቸውን ታላላቅ ሀገራዊና አህጉራዊ ስብሰባዎችን የሚያስተናግድበት፥ እንዲሁም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤትና የዲፕሎማሲ መድረኮችን ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ የሚታደሙበትን ሰፊና ዘመናዊ የስብሰባ ማእከል ማስገንባት እንደሚገባው ከታመነበት ረዘም ያለ ጊዜ ተቆጥሯል። በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያኗን ጥንታዊ ቅርሶች፥ ታሪክና መንፈሳዊ ሀብቶች ለዓለም ለማስተዋወቅ የሚረዱ ጥናታዊ ሲምፖዚየሞችና ማኅበራዊ ክስተቶችን በላቀ ጥራት ለመምራት የሚያስችል፥ የቤተ ክርስቲያኗን ታላቅነትና የሚያንጸባርቅ ዓለም አቀፍ አዳራሽ ማግኘት የቆየ፥ ትውልድ ተሻጋሪ ተቋማዊ ፍላጎትና የዘመናት ሕልም ነበር። የዚህ ማእከል እውን መሆንም ቤተ ክርስቲያኗ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ያለችበትን ዘመናዊ ተቋማዊ ዕድገት የሚያበሥርና ለአገልግሎቷ አዲስ ምዕራፍ የከፈተ ታላቅ በረከትና አቅም ሆኗል።

የፕሮጀክቱ ጽንሰ-ሐሳብ፥ የራዕይ መነሻና የአበው ሚና

ይህ የልማትና የዕድገት ራዕይ በታላቁ አባት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ አርቆ አሳቢነት የታገዘ ሲሆን፥ ቅዱስነታቸው የፕሮጀክቱን የመሠረት ድንጋይ በማንበር የመጀመሪያውን ታሪካዊ ሀሳብ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዲሸጋገር አድርገዋል።





ከቅዱስነታቸው ጎልፈት በኋላ መንበረ ፓትርክናውን የተረከቡት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ደግሞ፣ የቀደሙ አባታቸውን አርቆ አሳቢ የልማት ራእይ በጽናትና በጥንካሬ በማስቀጠል፣ ሕንጻው መንፈሳዊ ክብሩንና ዘመናዊ ደረጃውን ጠብቆ እውን እንዲሆን ታላቅ አባታዊ መሪነት አበርክተዋል። ቅዱስነታቸው ግንባታውን ከማስጀመር ባሻገር፣ በሥፍራው በአካል በመገኘት ሕንጻውንና የግንባታ ሂደቱን በአባታዊ ቡራኬና በጸሎት ባርከዋል። እንዲሁም በተለያዩ ጊዜያት የመስክ ምልከታዎችን በማድረግ፣ የሥራውን ሂደት በቅርበት በመከታተል እና ለሚመለከታቸው አካላት መንፈሳዊና አስተዳደራዊ መመሪያዎችን በመስጠት ፕሮጀክቱ ተጀምሮ ለተሳካ ፍጻሜ እንዲበቃ አብነት የሚሆን ጽኑ አባታዊ ተልእኮአቸውን ተወጥተዋል። በዚህም መሠረት ሕንጻው ዛሬ ለደረሰበት ግርማ ሞገስና ዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲበቃ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ያልተቋረጠ አባታዊ ጸሎትና ጥብቅ ክትትል የፕሮጀክቱ ዋና የጀርባ አጥንት እና የማዕዘን ድንጋይ ሆኖ አልፏል።









ይህንን ታላቅ አስፈላጊነትና ራዕይ ገና በፕሮጀክቱ የመንደርደሪያ ጥናት ወቅት በቅዱስ ሲኖዶስ ጸሐፊነታቸው፥ በኋላም በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅነታቸው በባለቤትነት የመሩት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ አዳራሹ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችንና ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን ያሟላ እንዲሆን የመጀመሪያውን አባታዊ አቅጣጫና የዲዛይን ጽንሰ-ሐሳብ በማስቀመጥ ረገድ ቁልፍ ሚና ተጫውተዋል። ብፁዕነታቸው በወቅቱ የሕንጻውን አስፈላጊነት በመረዳት ከሐሳብ ደረጃ ጀምሮ ፕሮጀክቱ መሠረት እንዲይዝ ካደረጉት አበው አንዱ እንደመሆናቸው መጠን፥ የዚህ ታላቅ ራእይ ባለቤትና መሪ ሆነው ታሪካዊ ድርሻቸውን ተወጥተዋል።

በዚሁ የመንፈሳዊ መሪዎች አባታዊ ጥላ ሥር፥ የፕሮጀክቱ የመንደርደሪያ ጥናትና ዝግጅት በስፋት የተከናወነው በወቅቱ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ አሁን የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ በሆኑት ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ እና በወቅቱ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሓፊ አሁን የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ አርቆ አሳቢነት፥ የላቀ ተቋማዊ ራእይና የተቀናጀ ጥረት ነበር። አበው ሊቃነ ጳጳሳቱ ቤተ ክርስቲያናችን ዓለም አቀፋዊ ግርማዋን የሚመጥን፥ ለታላላቅ አህጉራዊና መንፈሳዊ ጉባኤዎች አገልግሎት የሚሰጥ የራሷ ዘመናዊ የስብሰባ ማእከል እንዲኖራት ባላቸው የጠበቀ ፍላጎት መሠረት፥ የመጀመሪያውን የዲዛይን ጽንሰ-ሐሳብና የማስጠናት ሥራዎች በበላይነት መርተው ለአፈጻጸም ዝግጁ እንዲሆን አድርገዋል።

የፕሮጀክቱ ዋና ዋና ዓላማዎች

የዚህ ግዙፍ ሁለገብ ዓለም አቀፍ የስብሰባ አዳራሽ ግንባታ የቤተ ክርስቲያናችንን መንፈሳዊ፥ ተቋማዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ታስቦ የተካሄደ ሲሆን፥ የሚከተሉትን ዋና ዋና ዓላማዎች ታሳቢ ተደርገዋል።

- የቤተ ክርስቲያኗን ከፍተኛ የውሳኔ ሰጪ አካል የቅዱስ ሲኖዶስን መደበኛና አስቸኳይ ጉባኤያት፥ ዓለም አቀፍ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤዎችን፥ እንዲሁም የአህት አብያተ ክርስቲያናትንና የዓለም አቀፍ ሃይማኖታዊ ተቋማትን የጋራ ጉባኤዎች በሙሉ ነፃነት፥ ምቾትና ዘመናዊ የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች ታግዞ በብቃት የሚያስተናግድ ማእከል መፍጠር፤
- የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነትን አስተዳደራዊ፥ መሠረተ-ልማታዊና የዲፕሎማሲ አቅም በማጠናከር፥ ቤተ ክርስቲያናችን በሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ መድረኮች ያላትን ታሪካዊ ግርማ ሞገስ፥ ተጽዕኖና ዘመናዊ መዋቅር በተግባር ማሳየትና ማጎልበት፤
- ሕንጻው ከስብሰባ አዳራሽነት ባሻገር ለልዩ ልዩ መንፈሳዊ፥ ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ ኩነቶች የሚውሉ ዘመናዊ ቢሮዎችን፥ አነስተኛ የስብሰባ ክፍሎችን፥ ጥናታዊ ሲምፖዚየሞች የሚካሄዱባቸውን መድረኮችና ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎችን በማካተት ሁለገብ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ ሌላው፤
- የቤተ ክርስቲያናችንን ታሪካዊ የልማትና የዕድገት ጉዞ የሚያንጸባርቅ፥ በቴክኖሎጂ አደረጃጀቱና በግንባታ ጥራቱ የላቀ ዘመናዊ ቅርስ በማስቀመጥ፥ ለተኪው ትውልድ የሚሸገርና የትውልዶችን መንፈሳዊና ተቋማዊ ፍላጎት በዘላቂነት የሚያሟላ ታላቅ መሠረት መጣል ናቸው

ክፍል 2

የአበው ሊቃነ ጳጳሳት አሻራ እና የተቋማዊ አመራር ቅብብሎሽ

የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ሁለገብ ዓለም አቀፍ አዳራሽ ግንባታ ዛሬ ለደመቀ ፍጻሜና ለታላቅ ምረቃ ከመብቃቱ በስተጀርባ፥ በየዘመናቱ የተተኩ ቅዱሳን ፓትርያርኮች እና ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት የተካነ መሪነት፥ ጥበብ የተሞላበት ራዕይ እና ተቋማዊ የሥራ ቅብብሎሽ ታላቅ አሻራ ያረፈበት ታሪካዊ ክስተት ነው። አንድን ግዙፍና ውስብስብ ፕሮጀክት ከሀሳብ ደረጃ ጀምሮ ወደ ተግባር በመቀየር፥ ያጋጠሙ ጥልቅ ፈተናዎችን በጽናት በመሻገር እና ለስኬታማ ፍጻሜ በማብቃት ረገድ የአበው አባታዊ አመራር፥ ሃይማኖታዊ መመሪያና ያልተቋረጠ ክትትል ዋናው የማዕዘን ድንጋይ ሆኖ አልፏል።

የዚህ ታላቅ ሁለገብ ሕንጻ ግንባታ የመጀመሪያ የመሠረት ድንጋይ የተጣለው በታላቁ ባለራዕይ አባት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የፓትርያርክነት ዘመን ነበር። ቅዱስነታቸው ቤተ ክርስቲያናችንን ወደ ዘመናዊ ዕድገትና ዓለም አቀፍ ደረጃ ለማሸጋገር በነበራቸው ከፍተኛ አርቆ አሳቢነትና የልማት አባትነት፥ የዚህን ግዙፍ ማእከል የመሠረት ድንጋይ በማስቀመጥ የመጀመሪያውን ታሪካዊ ሀሳብና መነሻ ተክለዋል።

ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ዕልፈት በኋላ መንበረ ፓትርክናውን የተረከቡት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፥ የቀደሙት አባታቸውን አርቆ አሳቢ የልማት ራዕይ

በጽናት በማስቀጠል፥ ሕንጻው ዘመናዊ ደረጃውን ጠብቆ እንዲገነባ አባታዊ ቡራኬያቸውን፥ ያልተቋረጠ መመሪያቸውንና ክትትላቸውን በመስጠት የፕሮጀክቱ ዋና ደጋፊና መሪ በመሆን ታላቅ ታሪካዊ ድርሻቸውን ተወጥተዋል።



በዚሁ የመንፈሳዊ መሪዎች አባታዊ ጥላ ሥር፥ የፕሮጀክቱ የመንደርደሪያ ጥናትና ዝግጅት በስፋት የተከናወነው በወቅቱ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ በነበሩት በብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ (አሁን የቅዱስ ሲኖዶስ ጸሐፊ) እና በወቅቱ የቅዱስ ሲኖዶስ ጸሐፊ በነበሩት በብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ አርቆ አሳቢነትና የተቀናጀ ጥረት ነበር። በተለይም ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ በወቅቱ በነበራቸው ከፍተኛ ተቋማዊ ራዕይ፥ የማይታክት ጥረትና የበሰለ አስተዳደራዊ ጥበብ፥ ቤተ ክርስቲያናችን ዓለም አቀፋዊ ግርማዋን የሚመጥን፥ ለታላላቅ አህጉራዊና መንፈሳዊ ጉባኤዎች አገልግሎት የሚሰጥ የራሷ ዘመናዊ ማእከል እንዲኖራት ባላቸው የጠበቀ ፍላጎት መሠረት፥ የመጀመሪያውን የዲዛይን ጽንሰ-ሐሳብና የማስጠናት ሥራዎች በከፍተኛ ትጋትና በበላይነት መርተዋል። ይህ የጥናትና የዲዛይን ሥራ ለዛሬው ግዙፍና ዘመናዊ ማእከል መፈጠር ወሳኝ መሠረት የጣለ የራዕይ ምዕራፍ ነበረ።



ይህንን የተወጠነ ራዕይ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለማሸጋገር በወቅቱ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ በነበሩት በብፁዕ አቡነ ያሬድ ቁርጠኝነትና የነቃ ክትትል በ265 ሚሊዮን ብር የበጀት ውል ከአተም ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ (Atom Construction) ጋር የመጀመሪያው የግንባታ ስምምነት ተፈረመ። ብፁዕነታቸው ፕሮጀክቱ እውን እንዲሆን በነበራቸው ታላቅ የልማት ፍላጎትና አባታዊ ትጋት፥ በቦታው ላይ የነበረውን አሮጌ አዳራሽ የማንሣት፥ የቦታው ወሰን የማስከበርና የመሬት ዝግጅት የመሬት ዝግጅት ተዳፋትነትን በብቃት በመወጣት፥ ቦታው (Site) ጸድቶ የመሠረት ቁፋሮ ሥራ በጥቅምት ወር 2013 ዓ.ም እንዲጀመር አድርገዋል። በዚህ የመነሻ ምዕራፍ የሁለቱ የከርሰ-ምድር (Basement)፥ የምድር ቤት (Ground Floor) እና የመጀመሪያው ወለል የስትራክቸር ሥራዎች በብፁዕነታቸው የቅርብ የበላይ ክትትልና አባታዊ አመራር የተከናወኑ ሲሆን፥ አስፈላጊ የዲዛይን ማሻሻያዎችን (Amendment) በማካተት የሕንጻው ግንባታ 32 በመቶ አፈጻጸም ላይ እንዲደርስ አስደናቂ መሠረት ጥለዋል።





በመቀጠልም ኃላፊነቱን የተረከቡት ብፁዕ አቡነ አብርሃም በጠቅላይ ዋና ሥራ አስኪያጅነት በነበሩበት ወቅት፥ ፕሮጀክቱ አዲስ የመፋጠንና የሥራ ትጋት ምዕራፍ እንዲያይ አድርገዋል። ብፁዕነታቸው ለሕንጻው ግንባታ በሰጡት ልዩ ትኩረት፥ ቅድሚያ የሚሰጠው የልማት ግብ አድርገው በመያዝና የግንባታውን እንቅስቃሴ በየዕለቱ በቅርብ በመከታተል፥ የሕንጻው አጠቃላይ የስትራክቸር ሥራዎች ሙሉ በሙሉ እንዲጠናቀቁ ታላቅ አባታዊ ሚና ተጫውተዋል፤ በዚህም ግንባታው ወደ ማጠናቀቂያ ሥራዎች ማለትም የግድግዳ መክፈያዎች፥ የጣራ ሥራዎች ወዘተ. እንዲሸጋገር አድርገዋል። በተጨማሪም ሕንጻው ዓለም አቀፋዊ ግርማ ሞገስና ዘመናዊ አደረጃጀት እንዲኖረው ለማስቻል የዲዛይን ክለሳ ተደርጎ የመግቢያ (Entrance) ለውጥ በመደረጉ ተጨማሪ ስትራክቸር እንዲገነባ ተደርጓል፤ ይህም አጠቃላይ በጀቱ ቫትን አካቶ ወደ 429 ሚሊዮን ብር ከፍ እንዲልና አዲስ ውል እንዲፈረም ምክንያት ሆኗል። በብፁዕ አቡነ አብርሃም ያልተቋረጠ ጥረትና አባታዊ አመራርም ሕንጻው ገና ሙሉ በሙሉ ሳይጠናቀቅ በ2017 ዓ.ም ታሪካዊውን ዓለም አቀፍ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን በብቃት ለማስተናገድ የበቃ ሲሆን፥ የቅዱስ ሲኖዶስ መደበኛ ስብሰባ አዳራሽም በዚሁ አዲስ ሕንጻ ውስጥ እንዲካተት የተወሰነው በዚሁ ወቅት እንደነበር የፕሮጀክቱ መሐንዲሶች ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ።

ይህን ዘመናት የተሻገረ ግዙፍና ታሪካዊ ፕሮጀክት ወደ ፍጻሜ ለማድረስና ለዚህ ውብ የምረቃ ደረጃ ለማብቃት ኃላፊነቱን የተረከቡት የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና የካፋ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የላቀ መንፈሳዊ ቁርጠኝነት፥ የተካነ ተቋማዊ የመሪነት ክህሎትና የማይታክት አባታዊ ትጋት የሕንጻውን የመጨረሻና ወሳኝ ምዕራፍ በላቀ ፍጥነትና ጥራት ሊጠናቀቅ ችሏል።

ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅነትን መንበር ከተረከቡበት ቅጽበት ጀምሮ የግንባታውን ሂደት በቅርብ በመከታተልና በባለቤትነት በመመምራት ረገድ አዲስ ምዕራፍ ከፍተዋል። በየዕለቱና በየሳምንቱ ከግንባታው ቦታ በመገኘት የቀንና የሌሊት የቅርብ ፍተሻና ክትትል በማድረግ የግንባታውን ጥራትና የጊዜ ሰሌዳ በበላይነት ተቆጣጥረዋል። በሀገሪቱ ያጋጠሙትን አስቸጋሪ የኢኮኖሚ ሁኔታዎች፥ የቁሳቁስ ዋጋ ንረትና የፋይናንስ እጥረት ጨምሮ አሠራርን የሚያደናቅፉ ውስብስብ ማነቆዎችን በከፍተኛ አስተዳደራዊ ብልሃት፥ በጠንካራ ውሳኔ ሰጪነትና የሀብት ማሰባሰብ ጥረት ችግሮች ፈትተዋል። በተጨማሪም ከፕሮጀክቱ መሐንዲሶች፥ ከአማካሪዎችና ከተቋራጮች ጋር የነበራቸውን ግንኙነት በማጠናከር፥ ችግሮች

በቦታው ላይ ወዲያውኑ እልባት እንዲያገኙ በማድረግ፥ ባለሙያዎችንና ሠራተኞችን በየዕለቱ በማበረታታትና አቅጣጫ በመስጠት ግንባታው ለፍጻሜ እንዲበቃ አድርገዋል። ይህም የሚያሳየው ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የዚህን ታላቅ ፕሮጀክት ሕልምና ጽንሰ-ሐሳብ በቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሓፊነታቸው ከጣሉት ከመጀመሪያው ቀን አንሥቶ፥ በጠቅላይ ዋና ሥራ አስኪያጅነታቸው የመጨረሻውን የምረቃ ቁልፍ እስከጨበጡበት ዕለት ድረስ የፕሮጀክቱ ባለቤትና ዋና መሪ ሆነው ዘመናትን የተሻገረ ታሪካዊ አሻራ ማኖራቸውን ነው።

በአጠቃላይ በታላቁ ባለ ራእይ አባት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ የመሠረት ድንጋይ ማኖር የተጀመረው፥ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ አባታዊ ቡራኬና አጠቃላይ መሪነት የጸናው፥ እንዲሁም በብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ፥ በብፁዕ አቡነ ያሬድና በብፁዕ አቡነ አብርሃም ከፍተኛ ጥረትና ተቋማዊ ቅብብሎሽ የመጣው ይህ ግዙፍ ማእከል፤ የመጨረሻውንና ወሳኙን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ ባጠናቀቁት በብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የማይበገር ቁርጠኝነት፥ የታየበት ተቋማዊ መሪነትና አባታዊ ቡራኬ ምክንያት ዛሬ ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል። ይህ ታላቅ ሕንጻ የቤተ ክርስቲያናችንን ገናናነት የሚያሳላ፥ ዓለም አቀፋዊ ግርማ ሞገስ የሚያጐናጽፋት፥ ዘመናዊ የአገልግሎት አቅሟን የሚያሳድግና ለተኪው ትውልድ የሚሸገር ታላቅ መንፈሳዊና ተቋማዊ ቅርስ ሆኖ ለዚህ ደመቅ ያለ የምረቃ በዓል ለመብቃት ችሏል።

ክፍል 3

የሥነ-ሕንጻ፥ የዲዛይን ጽንሰ-ሐሳብ እና የአበው አመራር አሻራ (Architectural & Interior Design Concept and Leadership Role)

ይህ ታላቅ ሁለገብ የሃይማኖታዊና የመንፈሳዊ አገልግሎት ማእከል አዳራሽ በሥነ-ሕንጻ ጥበቡ (Architecture)፥ በውጫዊ ግርማ ሞገሱና በውስጥ ማጠናቀቂያ አደረጃጀቱ (Interior Design) የዘመኑን የመጨረሻ የምሕንድስና ደረጃ ከቤተ ክርስቲያናችን ጥንታዊ መንፈሳዊ ማንነት፥ ታሪክና ባህላዊ እሴቶች ጋር በጥበብ አዋሕዶ የያዘ ድንቅ የምሕንድስናና የኪነ-ሕንጻ ውጤት ነው። ሕንጻው በይዘቱ የቀደመውን ታሪካዊ ቅርስና የወደፊቱን ዘመናዊ ራእይ የሚያገናኝ



ሕያው ድልድይ ሆኖ የተቃኘ ሲሆን፤ አጠቃላይ የንድፍ ጽንሰ-ሐሳቡም የተቋሙን ዓለም አቀፋዊ ግርማ ሞገስ፥ ተግባራዊ አገልግሎትንና የላቀ ውበትን ማእከል አድርጎ የተገነባ ነው።

አንድን ግዙፍ ሕንጻ ከወረቀት ላይ የ3D ንድፍ ጽንሰ-ሐሳብ ተነሥቶ ለዚህ ተጨባጭና ውብ የማጠናቀቅ ደረጃ እንዲበቃ ማድረግ ከምሕንድስና ባለሙያዎች ጥረት ባሻገር፥ የተካነ ተቋማዊ አመራርና አባታዊ ክትትልን የሚጠይቅ ታላቅ ሂደት ነበር። በዚህ ረገድ በየዘመናቱ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ በመሆን ያገለገሉት ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት ያበረከቱት አስተዋጽዖ ታሪካዊና ትልቅ ዋጋ ያለው ነው። በብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ጥናትና አርቆ አሳቢነት የሕንጻው የመጀመሪያ የዲዛይንና የስነ-ሕንጻ ጽንሰ-ሐሳብ መሠረት ሲጣል፤ በብፁዕ አቡነ ያሬድ ቁርጠኝነትና የነቃ ክትትል ደግሞ ቦታውን የማጽዳት፥ ወሰን የማስከበርና የመነሻ ስትራክቸር ሥራዎች እውን ሆነዋል። በመቀጠልም በብፁዕ አቡነ አብርሃም ልዩ ትኩረትና የበላይ አመራር የስትራክቸር ሥራው 100% ተጠናቆ፥ የመግቢያ (Entrance) እና የቅዱስ ሲኖዶስ አዳራሽ የዲዛይን ክለሳዎች በስኬት ተካተዋል።

የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የፕሮጀክቱ የመጨረሻና ወሳኝ ምዕራፍ በሆነው በፊኒሺንግ፥ በአኩስቲክስ፥ በብርሃንና በላንድስኬፕ ሥራዎች ላይ ያሳዩት የማይበገር አባታዊ ቁርጠኝነትና በየዕለቱ በቦታው በመገኘት ያደረጉት የቅርብ ክትትል ለዚህ ድንቅ ፍጻሜ እንዲበቃ ዋና ምክንያት ሆኗል። ብፁዕነታቸው እያንዳንዱ የሥነ-ሕንጻ ዝርዝር ከውጭ ግድግዳ ክላዲንግ እስከ ውስጡ 3D አኩስቲክ ፓነሎች የቤተ ክርስቲያናችንን ክብር በሚመጥን ጥራትና ፍጥነት እንዲጠናቀቅ የሰጡት አባታዊ መመሪያ፥ የቀደሙት አበው የተከሉትን ራእይ ወደ ሙሉ ፍሬነት ያሸጋገረ ታላቅ የተቋማዊ አመራር አሻራ ነው።

ይህ ምዕራፍ የሕንጻውን የውጭ ገጽታ፥ የታላቁን መግቢያና የፏፏቴ አደባባይ ቅርጻ ቅርጽ፥ የውስጥ አኩስቲክስና የጣሪያ ዲዛይን፥ እንዲሁም የውስጥ ቦታዎችንና የተፈጥሮ ብርሃን አደረጃጀት ከእነዚህ ብፁዓን አበው በተለይም ከብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የቅርብ ክትትልና አመራር አሻራ ጋር አጣጥሞ በዝርዝር ያቀርባል።



የሕንጻው ውጫዊ ገጽታና የሥነ-ሕንጻ ዕድገት (Exterior Facade & Architectural Evolution)

የሕንጻው ውጫዊ ገጽታ የጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎችን ታሪካዊ ግርማ ሞገስ ከዘመናዊው የሥነ-ሕንጻ ጥበብ ጋር እጅግ በተዋጣለት መልኩ ያስታርቃል። የፊቱ ገጽታ (Main Facade) ሲታይ፥ በአንድ በኩል የታሪካችንን ጥንካሬና ጽናት፥ በሌላ በኩል ደግሞ ወደፊት የሚራመደውን ዘመናዊ ማንነታችንን በአንድ ላይ አጣምሮ የሚናገር ሕያው የኪነ-ሕንጻ ምስል ሆኖ ይታያል።

የሕንጻው የፊት ለፊት ገጽታ ረጅምና ቀጥተኛ የኮንክሪት አምዶች (Vertical Columns) የተከበበ ሲሆን፥ እነዚህ አምዶች የሕንጻውን ግዙፍነትና ከፍታ አጉልተው የሚያሳዩ ከመሆናቸውም በላይ፥ ወደ ላይ የመጠቆም ባህሪያቸው በመንፈሳዊ እይታ ወደ ፈጣሪ የሚደረግን ምልጃና ተስፋ ይወክላሉ። በአምዶቹ መካከል የተዘረጉት ሰፋፊና ረጅም የመስታወት ግድግዳዎች (Glass Curtain Walls) ደግሞ ለሕንጻው ግልጽነትን፥ ዘመናዊነትንና ክፍትነትን ያበሥራሉ። በቀን ውስጥ ሰማዩንና አካባቢውን እንደ መስታወት እየተመለሱ የሚያንፀባርቁ ሲሆን፥ በምሽት ደግሞ ከውስጥ የሚወጣው ማራኪ ብርሃን በመስታወቶቹ በኩል አልፎ ወደ ውጭ ሲፈስ ሕንጻውን በአካባቢው ላይ እንደበራ ታላቅ የመብራት ፋኖስ አድርጎ ያደምቀዋል። በውጫዊ ማጠናቀቂያው ላይ የነጫጭና የግራጫ ድንጋይ ክላዲንግ (Natural Stone Cladding) ከተወለወሉ የብረትና የአሉሚኒየም ፍሬሞች ጋር ተጣጥመው ጥቅም ላይ ውለዋል። የድንጋዩ ጠንካራ ገጽታ የታሪክንና የመሠረትን ጽናት ሲያሳይ፥ የብረቱና የመስታወቱ ቅልጥፍና ደግሞ የዘመናዊውን ምጎንድስና ጥበብ ያመለክታል።

የሕንጻው ውጫዊ ገጽታ ከመነሻው የ3D ንድፍ ተነስቶ ወደ ተጨባጭ ግንባታ ሲሸጋገር በየደረጃው የጎለበተ የዲዛይን ዕድገት አሳይቷል። በብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ጊዜ የመነሻ ንድፉ ከተጠና በኋላ፥ በብፁዕ አቡነ ያሬድና በብፁዕ አቡነ አብርሃም ዘመን የመግቢያ ቦታዎችና የስትራክቸር ክለሳዎች ተደርገዋል። በተለይም ደግሞ አሁን የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ኃላፊነቱን ከተረከቡ በኋላ፥ የውጭ ገጽታው ጥራት ሳይጎድልና የቤተ ክርስቲያናችንን ክብር በሚመጥን መልኩ እንዲጠናቀቅ በየሳምንቱ በቦታው በመገኘት የክላዲንግና የመስታወት ገጠማ ሥራዎችን በቅርብ ተከታተልዋል። ብፁዕነታቸው የውጭ ማጠናቀቂያው የጊዜ ሰሌዳውን ጠብቆ እንዲጠናቀቅና ጥራቱ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን በየዕለቱ የመሩት የበላይ ቁጥጥርና የሰጡት አባታዊ መመሪያ ለሕንጻው አጠቃላይ ግርማ ሞገስ መፈጠር ወሳኝ ሚና ተጫውቷል።

የዋናው መግቢያ በር እና የግቢው ቅርጻ ቅርጽ (Monumental Entrance & Plaza Features)

የማእከሉ ዋና መግቢያና የፊት ለፊት አደባባይ (Plaza) ወደ ሕንጻው የሚገቡ ሰዎችን ቀልብ የሚገዙ፥ የመንፈሳዊነትን ሰላምና የታላቅነትን ስሜት በሰብእና ውስጥ የሚፈጥሩ የንድፍ አካላት ናቸው። ይህ ክፍል በቀላሉ ከውጭ ወደ ውስጥ መሸጋገሪያ ብቻ ሳይሆን፥ የተጠቃሚውን ስሜት ለታላቅ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ መርሐ-ግብር የሚያዘጋጅ ድንቅ የስነ-ሕንጻ መድረክ ነው።

በሕንጻው ቀኝ በኩል ባለው ዝቅተኛው መዋቅር አናት ላይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ዘይቤ የተሠሩና መስቀል ያረፈባቸው ጉልላቶች (Domes) ይታያሉ። እነዚህ ጉልላቶች ለሕንጻው የጸሎትና የቅድስና ስሜት የሚሰጡ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፥ የሕንጻውን ዓላማና የባለቤቱን ተቋማዊ ማንነት ከሩቅ ለሚያይ ሰው በግልጽ የሚያበሥሩ ታሪካዊ ምልክቶች ናቸው። የሕንጻው ዋና መግቢያ ደግሞ በግዙፍና ሰፊ የኮንክሪት ካኖፒ (Canopy) የተጠበቀ ሲሆን፥ ለብዙዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፥ ለሃይማኖት አባቶችና ለክብራን እንግዶች ተመጣጣኝና ታላቅ አቀባበል ለማድረግ በሚያስችል መልኩ የተቃኘ ነው። የመግቢያው ሰፊነት በርካታ ሕዝብ በአንድ ጊዜ በሚንቀሳቀስበት ወቅት ከአየር ጠባይ (ከዝናብና ከፀሐይ) ከለላ የሚሰጥ ሲሆን፥ ከውጭ ወደ ውስጥ የሚደረገውን የሰዎች ፍሰት እጅግ የተሳለጠና ምቹ ያደርገዋል።

ወደ ዋናው መግቢያ የሚያመሩት ሰፊና ግርማ ሞገስ ያላቸው የውጭ ደረጃዎች የሕንጻውን ከፍታና ክብር አጉልተው የሚያሳዩ ሲሆን፥ ከደረጃዎቹ ጎን ለጎን የተዘረጉት ምቹ የረምፕ (Ramp) መተላለፊያዎች ደግሞ ለአረጋውያን፥ ለአካል ጉዳተኞችና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ወገኖች ያለምንም እንቅፋት በነጻነት የመንቀሳቀስ መብትን የሚያረጋግጡ የዘመናዊ ሥነ-ሕንጻ አካታች (Inclusive Design) መመሪያዎችን የተከተሉ ናቸው። በተጨማሪም በሕንጻው የፊት ለፊት አደባባይ መሀል ላይ የተገነባው ባለ ስድስት ጎን (Hexagonal) ፍሬም ያለውና በውስጡ የመስቀል ቅርጽ የታቀፈበት የፏፏቴና የቅርጽ ሥራ የማእከሉ ዋና መንፈሳዊ መታወቂያ ነው። ባለ ስድስት ጎኑ ፍሬም የጽናትና የውበት ምልክት ሲሆን፤ በውስጡ የሚገኘው የመስቀል ቅርጽ ደግሞ የቤተ ክርስቲያኗን ጥንታዊነትና እምነት ይወክላል፤ በቅርጹ ዙሪያ የሚፈሰው ውሃና የተደረደሩት የተፈጥሮ



ድንጋዮች በአካባቢው ላይ የፀጥታ፥ የዕረፍትና የምስጋና መንፈስን ይፈጥራሉ። ከመግቢያው ፊት ለፊት ያለው ሰፊ ክፍት ቦታ በተመረጡ የተፈጥሮ የድንጋይ ንጣፎች (Paving Stones) እና በጥንቃቄ በተዘጋጁ የላንድስኬፕ (Landscaping) አረንጓዴ ስፍራዎች የተሸፈነ በመሆኑ፥ አደባባዩ ሕዝቡ ከመርሐ-ግብር በፊትና በኋላ ተሰብስቦ የሚወያይበትና መንፈሳዊ ወንድማማችነትን የሚያጠናክርበት ሕያው አደባባይ እንዲሆን ያስችለዋል።

የግቢው አደባባይ (Plaza)፥ የመግቢያው ካኖፒ እና የአካታችነት ዲዛይኑ በዚህ ደረጃ ጥራታቸውን ጠብቀው እውን እንዲሆኑ የብዑዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት የበላይ አመራር ከፍተኛ ድርሻ ነበረው። በተለይም ደግሞ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጁ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የዚህን ክፍል ወሳኝነት በመገንዘብ ለአረጋውያንና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ወገኖች የተዘረጉት የረምፕ መተላለፊያዎች እንዲሁም የመስቀል ቅርጽ ያለው የፏፏቴ ሥራ የቤተ ክርስቲያናችንን የእናትነት እቅፍና መንፈሳዊ ማንነት በሚገልጽ መልኩ እንዲከናወኑ በየዕለቱ በቦታው በመገኘት የቅርብ ክትትል አድርገዋል። ብፁዕነታቸው የላንድስኬፕና የድንጋይ ንጣፍ (Paving) ሥራዎቹ በጥራት መከናወናቸውን በአካል ተገኝተው በመፈተሽና አስፈላጊውን አባታዊ መመሪያ በመስጠት የሰጡት አመራር የመግቢያው አካባቢ ለታላቅ አቀባበልና ለሕዝቡ መንፈሳዊ ዕረፍት የተዘጋጀ ማእከል እንዲሆን አድርጎታል።

የውስጥ አኮስቲክስ እና የጣሪያ ዲዛይን
(Acoustics & Ceiling Architecture)

የአዳራሹ የውስጥ ክፍሎች ንድፍ የተቃኘው ከፍተኛ ቁጥር ያለው ታዳሚ በሚሰበሰብበት ወቅት ፍጹም የሆነ የድምፅ ጥራት፥ የብርሃን ሥርጭትና የመንፈስ እርካታ በሚሰጥ ውበት ላይ ተመሥርቶ ነው። የሕንጻው የውስጥ አካል የሥነ-ውበት (Aesthetics) እና የምሕንድስና (Engineering) ጥበብ እጅጉን ተዋሕደው የታዩበት ድንቅ ሥራ ነው።

በዋናው አዳራሽ ውስጥ የሚካሄዱ ስብሰባዎችና ሌሎች መርሐ ግብሮች ለአዳራሹ ታዳሚዎች ያለ ምንም መስተጋባት (Echo) እና መደራረብ በግልጽ እንዲደርሱ ለማድረግ ዘመናዊ የአኮስቲክ ቴክኖሎጂ ሥራ ላይ ውሏል። የውስጥ ግድግዳዎቹ ባለ 3D

የካራ እና የሶስት ማዕዘን የእንጨት አኮስቲክ ፓነሎች (3D Wooden Acoustic Panels) የተሸፈኑ ሲሆን፥ እነዚህ ፓነሎች ከመጠን በላይ የሚፈጠርን የድምፅ ድግግሞሽ በመምጠጥና በጥበብ በመበተን እያንዳንዱ ንግግር ውበቱን ጠብቆ ለሰሚው እንዲደርስ ያደርጋሉ። የአዳራሹ ጣሪያ ደግሞ ከተለመደው ዝርግ ዲዛይን ወጥቶ ማዕበላዊና ተለዋዋጭ (Curved/Fluid Design) የጂፕሰም ንድፎችን የተከተለ ነው። ይህ ቅርፅ ለአዳራሹ ሰፊ የከፍታ ስሜት የሚያበረክር ከመሆኑም በላይ፥ በውስጡ በተገጠሙ ዘመናዊ የተደበቁ የብርሃን ማሠራጫዎች (Recessed Spotlights & Ambient Strip Lighting) አማካኝነት በአዳራሹ ሙሉ አካል ላይ ዐይንን የማይጎዳ፥ ሞቅ ያለና ወጥ የሆነ ብርሃን እንዲሠራጭ ያስችላል።

በጣሪያውና በግድግዳው የሥነ-ሕንጻ ቅንብር ውስጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ጥንታዊ ታሪክና ሃይማኖታዊ ጥበብ የሚያንፀባርቁ የጂኦሜትሪክ ንድፎችና ቅርጻ ቅርጾች በጥበብ ተካተዋል። እነዚህ ቅርጾች አዳራሹ ዘመናዊነቱን ጠብቆ ሳለ ሀገራዊና መንፈሳዊ ማንነቱ ሳይደበዝዝ ጎልቶ እንዲወጣ የሚያደርጉ ናቸው። በተጨማሪም ከጣሪያውና ከጎን ግድግዳዎች በኩል የተገጠሙት የብርሃን ማግኛዎች በቀን ክፍለ-ጊዜ የተፈጥሮ ብርሃን በበቂ ሁኔታ ወደ ውስጥ እንዲገባ የሚያደርጉ ሲሆን፥ በምሽት ደግሞ የውስጡ ዘመናዊ የኤል.ኢ.ዲ (LED) ብርሃናት ከአኮስቲክ እንጨቶቹ ሞቅ ያለ ቀለም ጋር ተዋሕደው ለአዳራሹ ድንቅና መንፈሳዊ ግርማን ያጎናጽፉታል።

የአዳራሹ የውስጥ አኮስቲክስና የጣሪያ ዲዛይን ሥራዎች ከፍተኛ የፋይናንስ ወጪን፥ የቴክኖሎጂ ጥንቃቄንና የባለሙያዎችን ትጋት የሚጠይቁ በመሆናቸው፥ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጁ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ በየዕለቱ ከባለሙያዎች፥ ከመሐንዲሶችና ከሥራ ተቋራጮች ጋር በመወያየት ሥራውን በበላይነት መርተዋል። ብፁዕነታቸው በአዳራሹ ውስጥ የሚነገሩ መንፈሳዊ ቃላት፥ ስብከቶችና ዝማሬዎች ለአኮስቲክ መዛባት ሳይዳረጉ በግልጽ እንዲሰሙ የ3D አኮስቲክ ፓነሎች፥ የጂፕሰም ማዕበላዊ ጣሪያና የብርሃን መስመሮች በትክክለኛው የኢንጂነሪንግ ስፔስፊኬሽን መገጠማቸውን በየጊዜው በአካል ተገኝተው በመፈተሽ የቅርብ ክትትል አድርገዋል። ይህ የብፁዕነታቸው የማይታክት ቁጥጥርና አባታዊ መመሪያ አዳራሹ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ፍጹም ድምፅና ማራኪ የብርሃን ሥርጭት እንዲኖረው ያስቻለ ወሳኝ አሻራ ሆኖ አልፏል።

የሕንጻው የውስጥ እንቅስቃሴ እና የብርሃን አደረጃጀት (Interior Spatial Circulation & Daylight Integration)

የማእከሉ የውስጥ ክፍሎች እንቅስቃሴ (Circulation) እና የተፈጥሮ ብርሃን አጠቃቀም አደረጃጀት ሰፊ ሰዎችን በሚያስተናግድበት ወቅት ምቾትን፥ ደህንነትን እና መንፈሳዊ ድምቀትን ታሳቢ አድርጎ የተገነባ ነው። ወደ ዋናው አዳራሽ፥ ሰገነቶች (Balconies) እና ልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍሎች የሚያመሩት ሰፋፊና ባለ ሁለት ክንፍ የኮንክሪት ደረጃዎች (Grand Curved Staircases) በሕንጻው ውስጥ በርካታ ሕዝብ በተመሳሳይ ጊዜ በሚንቀሳቀስበት ወቅት መጨናነቅ እንዳይኖር ያደርጋሉ። የመተላለፊያ ኮሪደሮችና የመውጫ በሮች በስትራቴጂካዊ ቦታዎች ላይ መዋቀራቸው ለዕለታዊ እንቅስቃሴ ምቾት ከመስጠቱም በላይ በአደጋ ጊዜ ፈጣን መልቀቅን (Emergency Evacuation) የሚያረጋግጡ ናቸው። በጣሪያው በኩል በጥንቃቄ የተገጠሙት ክብ ቅርጽ ያላቸው የተፈጥሮ ብርሃን ማግኛዎች (Skylights) በቀን ክፍለ-ጊዜ የተፈጥሮ ብርሃን ቀጥታ ወደ አዳራሹ መሃል እንዲሰርፅ ያደርጋሉ፤ ይህም የኤሌክትሪክ ኃይል አጠቃቀምን በከፍተኛ ሁኔታ ከመቀነሱም በላይ፥ ከላይ ወደ ታች የሚወርደው ብርሃን በውስጥ ክፍሉ ላይ የተለየ መንፈሳዊና ቅዱስ ስሜትን ይፈጥራል።

በሕንጻው ጎኖች ላይ ያሉት ሰፋፊ የመስታወት ግድግዳዎች የተፈጥሮ ብርሃን ወደ ተለያዩ የመተላለፊያ ክፍሎችና የፍሎር ደረጃዎች በበቂ ሁኔታ እንዲገባ የሚያደርጉ ሲሆን፥ ይህም በውስጥ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ታዳሚዎች ከውጭው አደባባይና አረንጓዴ ስፍራ ጋር የእይታ ቁርኝት እንዲኖራቸው በማድረግ የቦታ ጥብብነት ስሜትን ያስቀራል። በተጨማሪም የውስጥ ቦታዎች አደረጃጀት የተፈጥሮ አየር በነፃነት እንዲዘዋወር (Cross-Ventilation) በሚያስችል መልኩ የተቃኘ ሲሆን፥ የታችኛው ዋና አዳራሽ፥ የቪ.አይ.ፒ (VIP) ማረፊያዎች፥ የሰገነት መቀመጫዎችና የአስተዳደር ክፍሎች እርስ በእርስ ሳይረበሹ አገልግሎት መስጠት የሚያስችላቸው ግልጽ የሆነ የሥራ ክፍፍልና ወሰን ተበጅቶላቸዋል።

ክፍል 4

የሕንጻው ሁለገብ አገልግሎቶች፥ የቴክኖሎጂ አደረጃጀት እና የክፍሎች ሥርጭት (Multi-Purpose Services, Technological Infrastructure & Spatial Distribution)

ይህ ታላቅ ሁለገብ የመንፈሳዊና የሃይማኖታዊ ማእከል ዘመናዊ አቀራረብንና ዓለም አቀፍ የሕንጻ አገልግሎት መስፈርቶችን (International Building Standards)

ማእከል አድርጎ የተገነባ የዘመናችን ድንቅ የምሕንድስና ውጤት ነው። ሕንጻው ዘመናዊ አገልግሎቶችን በከፍተኛ ጥራት፥ ፍጥነትና ደህንነት ለማቅረብ በሚያስችል መልኩ የተቃኘ ሲሆን፥ የተለያዩ መንፈሳዊ፥ ባህላዊ፥ ማኅበራዊ፥ ሳይንሳዊና አስተዳደራዊ ተግባራትን ያለ ምንም የቦታና የጊዜ መደራረብ ጎን ለጎን ለማስተናገድ የሚያስችሉ እጅግ ዘመናዊ ክፍሎችን በውስጡ አካታቶ ይዟል። ማእከሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያለችበትን ዘመናዊ የታሪክ ምዕራፍና ዓለም አቀፋዊ ተጽዕኖ ታሳቢ ያደረገ በመሆኑ፥ ከቤተ ክህነት አገልግሎቶች እስከ ዓለም አቀፍ ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ጉባኤዎች ድረስ ሁሉንም ዓይነት ኩነቶች በከፍተኛ ብቃት ማስተናገድ የሚያስችል የተሟላ መሠረተ-ልማት ተገንብቶለታል።

የማእከሉ አጠቃላይ የስፓሻል አደረጃጀት (Spatial Planning) ጥናት ታዳሚዎች፥ ከፍተኛ አመራሮች፥ የሃይማኖት አባቶች፥ አስተናጋጆችና የአገልግሎት ሠራተኞች በየራሳቸው የተለየና የተቀናጀ የመተላለፊያ መስመር (Circulation Paths) እንዲጠቀሙ ተደርጎ በተራቀቀ መልኩ የተዋቀረ ነው። ይህም በታላላቅ ክስተቶች ወቅት ከፍተኛ የሕዝብ ፍሰት ቢኖር እንኳ አላስፈላጊ መጨናነቅና የደህንነት ስጋት እንዳይፈጠር የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ፥ የእያንዳንዱን ክፍል ምሥጢራዊነትና ተቋማዊ ክብር በጠበቀ መልኩ አገልግሎት ለመስጠት ያስችላል። በተጨማሪም የሕንጻው የውስጥ ክፍል ሥርጭት የተለያየ አገልግሎት ያላቸው ክፍሎች እርስ በእርስ ሳይረበሹና ድምፅ ሳይደላለቅ ተግባራቸውን ማከናወን እንዲችሉ በአኮስቲክና በቦታ ክፍፍል ጥበብ ተከልለው የተገነቡ ናቸው።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የማእከሉን ሁለገብነትና ዘመናዊነት የሚያረጋግጡት ታላላቅ የስብሰባ አዳራሾች፥ ከመድረክ በስተጀርባ ያሉ የዝግጅትና የቀጥታ የትርጉም ክፍሎች፥ የኦዲዮ-ቪዥዋልና የቡድን ውይይት ቦታዎች፥ የዲጂታል ቤተ-መጻሕፍትና የሙዚየም ማእከላት፥ ዘመናዊ የመስተንግዶና የኢንዱስትሪ ኩሽና ክፍሎች፥ እንዲሁም የውስጥ ትራንስፖርትና የእንቅስቃሴ ሥርዐቶች በዝርዝር ቀርበዋል።

4.1 የዋና ዋና አዳራሾች አደረጃጀትና የቦታዎች አቅም (Main Halls Architecture & Spatial Capacity)

የሕንጻው ዋነኛ አስኳል የሆኑት የስብሰባና የመሰብሰቢያ አዳራሾች አነስተኛ ከሆኑ የቡድን ውይይቶች ጀምሮ እስከ ታላላቅ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ጉባኤዎች ድረስ በተለያዩ ደረጃዎች የሚካሄዱ ኩነቶችን በከፍተኛ ምቾትና ደረጃ ለማስተናገድ በሚያስችል መልኩ የተቃኙ ሲሆን፥ እያንዳንዱ አዳራሽ እንደየ አገልግሎት ባህሪውና እንደሚሰጠው ተቋማዊ አገልግሎት የተለየ የንድፍ፥ የቴክኖሎጂና የቦታ ስፋት አደረጃጀት ተበጅቶለታል። በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሰው ዋናው ታላቅ አዳራሽ (Main Hall/Grand Auditorium) በአንድ ጊዜ 2800 ታዳሚዎችን በሰፊው የማስተናገድ አቅም ያለው የማእከሉ ትልቁ ሁለገብ አዳራሽ ነው። ይህ አዳራሽ በሁለት ዋና ዋና የወለል ደረጃዎች የተዋቀረ ሲሆን፥ በምድር ወለል ደረጃ (Ground Level) ለ2,100 ተቀማጮች ሰፊና ለመድረክ እይታ ምቹ የሆነ ቦታ ያመቻቻል፤ በበላይኛው ክፍል የሚገኘው የሰገነት ደረጃ (Mezzanine Floor) ደግሞ ተጨማሪ 700 ተቀማጮችን የሚያስተናግድ ሆኖ፥ ከከፍታው አንጻር ወደ መድረኩ ጥራት ያለው ቀጥታ እይታ (Clear Line of Sight) እና የተሳለጠ የአኮስቲክስ ድምፅ ሥርጭት እንዲኖር ተደርጎ ተቀርጿል።

ለቤተ ክርስቲያኒቱ ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካላት የተዘጋጀው የቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ አዳራሽ (Holy Synod Hall) ደግሞ ለቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ስብሰባዎችና ውሳኔዎች የተዘጋጀ 120 ወንበሮች ያሉት የተከበረ አዳራሽ ሲሆን፥ ሙሉ በሙሉ ራሱን የቻለና ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚደረግበት እንደመሆኑ መጠን የራሱ የሆነ ልዩ የእንግዳ አቀባበል (Reception)፥ የቪ.አይ.ፒ የማረፊያ ቦታ (Waiting Area)፥ የተሟሉ የአስተዳደር ቢሮዎች እና ገለልተኛ የመፀዳጃ ቤቶች ተደራጅተውለታል። የሕንጻውን ሁለገብነት የሚያጎላው ከፋፋይ አዳራሽ (Syndicate Room/Partitionable Hall) በፍላጎትና በኩነቶች ዓይነት ላይ ተመሥርቶ በድምፅ መከላከያ ተንቀሳቃሽ ግድግዳዎች (Acoustic Movable Partitions) ሊከፈልና ሊያያዝ የሚችል ዘመናዊ አዳራሽ ሲሆን፥ ለሁለት ሲከፈል እያንዳንዱ ክፍል 250 ተቀማጮችን፥ ክፍፍሉ ተነሥቶ በአንድነት ሲያገለግል ደግሞ እስከ 600 ተቀማጮችን በአንድ ጊዜ የማስተናገድ አቅም አለው። በተጨማሪም በምድር ወለል ላይ የሚገኘው ሁለገብ አዳራሽ (Ground Floor Multipurpose Hall) ከ300 በላይ ወንበሮችን የሚይዝ ሆኖ ለማኅበራዊ ስብሰባዎች፥ ለጋዜጣዊ መግለጫዎች እንዲሁም ለይፋዊ የምግብና የመስተንግዶ ፕሮግራሞች (Catering Events) አገልግሎት የሚውል ክፍት ቦታ ነው። በመጨረሻም፥ ለከፍተኛ ደረጃ ሴሚናሮች፥ ለሥልጠናዎችና ለቪዲዮ ኮንፈረንስ ስብሰባዎች የተዘጋጀው የመልቲሚዲያ ስብሰባ አዳራሽ (Multimedia Conference Hall) 165 ወንበሮች ያሉት ሲሆን፥ በዘመናዊ የመገናኛና የዲጂታል ቴክኖሎጂዎች የተሟላ አገልግሎት ይሰጣል።

የዝግጅት ድጋፍ ሰጪ ክፍሎች እና

የትርጉም ማእከላት (Backstage Support Areas & Translation Infrastructure)

በዋናው አዳራሽና በሌሎች ኩነቶች ወቅት የሚከናወኑ መርሐ-ግብሮች በተሳለጠ፥ በተደራጀና ዓለም አቀፋዊ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እንዲመሩ ከመድረክ በስተጀርባና በትርጉም ክፍሎች በኩል የተሟላ የሥራ አካባቢ ተፈጥሯል። እነዚህ ክፍሎች የዝግጅት አቅራቢዎችን፥ የሃይማኖት አባቶችን፥ የአመራሮችንና የቴክኒክ ባለሙያዎችን ዕለታዊ እንቅስቃሴና ምቾት ታሳቢ በማድረግ በጥንቃቄ የተደራጁ ናቸው። የመድረክ በስተጀርባና የላይኛው መድረክ ክፍሎች (Backstage & Upper Backstage) በጥቅሉ እስከ 96 ወንበሮችንና የመቀመጫ ቦታዎችን የሚያስተናግዱ ሰፋፊ የዝግጅት ስፍራዎች ሲሆኑ፥ በዚህ ክፍል ውስጥ የመርሐ-ግብር መሪዎችና ከፍተኛ አካላት ስብሰባዎችንና ውይይቶችን የሚያካሂዱበት የአመራሮች የስብሰባ ክፍል (Managerial Meeting Room) ይገኛል። በተጨማሪም ተናጋሪዎች፥ ዘማሪያንና እንግዶች ለዝግጅት የሚጠቀሙባቸው የልብስ መቀየሪያ ክፍሎች፥ ለብቻቸው የተዘጋጁ ዘመናዊ የሻወር አገልግሎቶችና የመፀዳጃ ቤቶች ተሟልተውላቸዋል፤ ይህም ከተመልካችና ከተሳታፊዎች ፍሰት ገለልተኛ በሆነ መልኩ ለፕሮግራሞች በቂ ዝግጅት ለማድረግ ያስችላል።

በሌላ በኩል፥ ማእከሉ ዓለም አቀፋዊ ጉባኤዎችንና የበርካታ ሀገራት ተወካዮች የሚሳተፉባቸውን መርሐ-ግብሮች ለማስተናገድ የሚያስችሉ የቀጥታ የትርጉም ክፍሎች (Translation Booths) ተገጥመውለታል። እነዚህ ክፍሎች በአንድ ጊዜ እስከ 6 ለሚደርሱ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ቀጥታ የትርጉም አገልግሎት (Simultaneous Translation) መስጠት በሚያስችል ዘመናዊ የድምፅ መከላከያና የኦዲዮ ቴክኖሎጂ የታጠቁ በመሆናቸው፥ ከተለያዩ ሀገራት እና አካባቢ የሚመጡ እንግዶችና ተሳታፊዎች በቋንቋ እንቅፋት ሳይገደቡ የመርሐ-ግብሮቹ ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።

የኦዲዮ-ቪዥዋል እና የቡድን ስብሰባ ክፍሎች (AV Viewing & Group Meeting Rooms)

ማእከሉ አነስተኛና ማእከላዊ ቁጥር ያላቸው አካላት የሚመክሩባቸውን ንኡሳን ስብሰባዎች፥ የምርምር ውይይቶችንና የቪዲዮ/የድምፅ መመልከቻ መርሐ-ግብሮችን ለማስተናገድ የሚያስችሉ ልዩ ክፍሎችን በውስጡ አካትቷል። እነዚህ ክፍሎች በዘመናዊ የመገናኛ ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች የተደራጁ በመሆናቸው ለጥቃቅንና መካከለኛ ስብሰባዎች ከፍተኛ ምቾትና ቅልጥፍናን ይሰጣሉ። በዚህ ክፍል ውስጥ በግንባር ቀደምትነት የሚገኘው ባለ ሁለት ወለል ከፍታ ያለው የኦዲዮ-ቪዥዋል መመልከቻ አዳራሽ (AV Viewing Double Height Conference) 44 ወንበሮችን የሚይዝ ሲሆን፤ አየር የተሞላበትና ከፍታ ያለው አደረጃጀቱ ለረጅም ሰዓታት የሚካሄዱ ውይይቶችንና የቪዲዮ ማሳያዎችን ያለ ስልችት ለመከታተል ያስችላል። በተጨማሪም ለትንንሽ ቡድኖች ውይይት የተዘጋጀው የቡድን ስብሰባና የኦዲዮ-ቪዥዋል መመልከቻ ክፍል (Group Meeting AV Viewing) 18 ወንበሮች ያሉት ሲሆን፥ ገለልተኛ በሆነ አካባቢ የምርምርና የቴክኒክ ጉዳዮች የሚመከሩበት ስፍራ ነው። ከዚህ በተጨማሪ፥ ሰፋ ያሉ የቡድን ውይይቶችን ለማስተናገድ የተዘጋጁት ታላቅ የቡድን ስብሰባና የኦዲዮ-ቪዥዋል መመልከቻ ክፍሎች (Group Plus Meeting AV Viewing) እያንዳንዳቸው 20 ወንበሮችን የመያዝ አቅም ያላቸው ሁለት ገለልተኛ ክፍሎች (በጠቅላላው 40 ወንበሮች) ናቸው። እነዚህ ክፍሎች በዘመናዊ የድምፅና የምስል ማቅረቢያ ስክሪኖች (AV Systems) የተሟሉ በመሆናቸው ለኮሚቴ ስብሰባዎች፥ ለልኡካን ቡድን ውይይቶችና ለሥልጠናዎች እጅግ አመቺ ናቸው።

የዲጂታልና የኤግዚቢሽን ማእከላት (Digital & Heritage Facilities)

ማእከሉ ታሪካዊና መንፈሳዊ ቅርሶችን ከዘመናዊው የዲጂታል ቴክኖሎጂ ጋር በማዋሐድ ለትውልድ ለማስተላለፍና ለምርምር ሥራዎች ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር በርካታ ዘመናዊ አደረጃጀቶችን በውስጡ አካትቷል። እነዚህ ክፍሎች የቤተ ክርስቲያኒቱን ጥንታዊ ሀብቶችና የታሪክ ሰነዶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስተዋወቅና ተመራማሪዎችን ለማስተናገድ የሚያስችሉ ጥበበኛ የሥራ ክፍሎች ናቸው። በዚህ መዋቅር ውስጥ የሚገኘው ዲጂታል ቤተ-መጻሕፍት (Digital Library) ዘመናዊ የመረጃ መፈለጊያዎችን፥ የኤሌክትሮኒክስ መጻሕፍትንና የዲጅታል ሰነዶችን ያካተተ ማእከል ሲሆን፤ ተመራማሪዎች፥ ሊቃውንትና ተማሪዎች ጥንታዊና ዘመናዊ የመንፈሳዊና የባህል ድርሳናትን በቀላሉ በዲጂታል አማራጮች እንዲያገኙና እንዲያጠኑ ሰፊ ዕድል ይፈጥራል። በሌላ በኩል ዲጂታል ሙዚየሙ (Digital Museum) የታሪክ፥ የቅርሶችና የጥንታውያን ቅርጻ ቅርጾች መረጃዎችን በዘመናዊ የዲጂታል ቴክኖሎጂ፥ በምስልና በድምፅ አስደግፎ ለጎብኚዎች የሚያቀርብ ልዩ ማእከል በመሆኑ፥ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጎብኚዎች የቤተ ክርስቲያኒቱን ዘመናት ተሻጋሪ ታሪክና መንፈሳዊ ሀብት በአይን በሚታይና በሚዳሰስ የቴክኖሎጂ አቀራረብ እንዲረዱ ያስችላቸዋል።

የምግብ ዝግጅት፥ የመስተንግዶና የድጋፍ ሰጪ አገልግሎት ክፍሎች (Catering, Hospitality & Support Service Areas)

በማእከሉ ውስጥ የሚካሄዱ ታላላቅ ጉባኤዎችና ኩነቶች ያለ ምንም የመስተንግዶና የሎጅስቲክስ ችግር በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቁ፥ ዘመናዊ የምግብ ዝግጅትና የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች በከፍተኛ ጥራት ተደራጅተዋል። እነዚህ ክፍሎች ከፍተኛ ቁጥር ላላቸው ታዳሚዎችና ለክብራን እንግዶች በአንድ ጊዜ ጥራት ያለው የምግብና የመጠጥ መስተንግዶ ለመስጠት የሚያስችሉ የኢንዱስትሪ ደረጃቸውን የጠበቁ አደረጃጀቶች ናቸው። የዚህ ክፍል ዋና አስኳል የሆነው የኢንዱስትሪ ኩሽና (Industrial Kitchen) በ241 ካሬ ሜትር ሰፊ ቦታ ላይ ያረፈ ሲሆን፥ በዘመናዊ የምግብ ማብሰያ፥ ማዘጋጃና ማሞቂያ የኩሽና መሳሪያዎች የተሟላ በመሆኑ በታላላቅ የጉባኤ ቀናት በሺዎች ለሚቆጠሩ ታዳሚዎች በከፍተኛ መጠንና ፈጣን ሁኔታ ምግብ ለማብሰልና ለማቅረብ የሚያስችል አቅም አለው።

ከዋናው ኩሽና ጎን ለጎን የሥራ ፍሰቱን የተሳለጠ ለማድረግ በርካታ የደጋፊ አገልግሎት መስጫ ክፍሎች (Kitchen Supplements) ተደራጅተዋል። ከእነዚህም መካከል አትክልትና ጥሬ ዕቃዎች የሚዘጋጁበትና የሚታጠቡበት የጀርባ ቦታ (Backyard)፥ ለኩሽናና አስተናጋጅ ሠራተኞች የተዘጋጀ የልብስ መቀየሪያ ክፍል (Changing Room)፥ በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ የምግብ እቃዎችን በዝቅተኛ የሙቀት መጠን ጠብቆ ለማቆየት የሚያስችል የቅዝቃዜ ማከማቻ ጎተራ (Cold Store/Cold Room) እና አጠቃላይ የደረቅ ዕቃዎች ማከማቻ (General Store) ይገኛሉ። በተጨማሪም የሕንጻውን ዕለታዊ ጽዳት፥ የዕቃዎች ዝውውርና የመስተንግዶ ቁሳቁስ አስተዳደርን የሚያከናውኑ የጽዳትና የአገልግሎት ክፍሎች (Service Areas) የተዘጋጁ ሲሆን፥ እነዚህ ክፍሎች ከዋናው የታዳሚዎችና የእንግዶች መተላለፊያ ገለልተኛ በሆነ መንገድ መዋቀራቸው የመስተንግዶ ሥራው በአዳራሾቹ ሰላምና ጸጥታ ላይ ምንም ዓይነት መረበሽ ሳይፈጥር በጥንቃቄ እንዲከናወን ያስችላል።

4.6 የሕንጻው የውስጥ እንቅስቃሴ ሥርዐት (Vertical & Horizontal Circulation)

በማእከሉ ውስጥ የሚገኙ ታዳሚዎች፥ የሥራ ኃላፊዎችና የአገልግሎት ሠራተኞች ከወለል ወደ ወለል እንዲሁም በየክፍሎቹ መካከል በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ወቅት ፈጣን፥ ምቹና አስተማማኝ አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል የውስጥ የመተላለፊያ ሥርዐት ተዘርግቷል። ይህ አደረጃጀት በተለይም ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር በሚኖርበት ወቅት የሚፈጠርን የመተላለፊያ መጨናነቅ ሙሉ በሙሉ በሚያስቀር መልኩ የተቃኘ ነው። በግንባር ቀደምትነት የሕንጻውን የቁልቁልና የከፍታ እንቅስቃሴ የተሳለጠ ለማድረግ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተገነቡ አሳንሳሮች (Lifts/Elevators) የተገጠሙ ሲሆን፤ እነዚህ አሳንሳሮች ለአረጋውያን፥ ለአካል ጉዳተኞች፥ ለልዩ እንግዶች፥ እንዲሁም ለከባድ ዕቃዎች ዝውውር ፈጣንና ደህንነቱ የተጠበቀ አገልግሎት ይሰጣሉ። ከአሳንሳሮቹ በተጨማሪ በሕንጻው የተለያዩ ክንፎች ላይ የተዘረጉ ሰፋፊና ውብ የውስጥ ደረጃዎች (Grand Staircases) የታዳሚዎችን እንቅስቃሴ ለማስተናገድ የሚያስችሉ ናቸው። በጎንዮሽ እንቅስቃሴ በኩል ደግሞ፥ የተለያዩ ክፍሎችንና አዳራሾችን የሚያያዙት ሰፋፊ ኮሪደሮችና የመተላለፊያ ደጅዎች (Circulation Corridors) በርካታ ሰዎችን በነፃነት እንዲንቀሳቀስ ያስችላሉ። የመተላለፊያ መስመሮቹ ምቾት ያለው አገልግሎት ከመስጠታቸውም በላይ፥ ድንገተኛ አደጋ በሚከሠትበት ወቅት ታዳሚው በአጭር ጊዜ ውስጥ በጥንቃቄና በሰላም ወደ ውጭ መውጣት የሚያስችሉ የአደጋ ጊዜ መውጫዎችን (Emergency Exits) ታሳቢ አድርገው የተዋቀሩ ናቸው።

ክፍል 5

ተቋማዊ፥ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ፋይዳ (Institutional & Spiritual Significance)

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፍ የጉባኤ ማእከል ግንባታ የተለመደ የሕንጻ ውበት ወይም የዘመናዊ ምሕንድስና ስኬት ብቻ ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም። ይልቁንም የቤተ ክርስቲያኒቱን ዘመናት ተሻጋሪ ታሪክ፥ መንፈሳዊ ተልዕኮና ማኅበራዊ አገልግሎት ወደ ላቀ አዲስ የዕድገት ምዕራፍ ያሸጋገረ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው ታሪካዊ ክስተት ነው። ይህ ታላቅ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለረጅም ዘመናት ጠብቃ ያቆየቻቸውን ጥንታውያን ይዘቶች፥ መንፈሳዊ እሴቶችና ሃይማኖታዊ ባህሎች ከ21ኛው ክፍለ ዘመን የቴክኖሎጂና የሥነ-ሕንጻ ምጥቀት ጋር በጥበብ አዋሕዶ የያዘ ሕያው ምስክር ነው።

ማእከሉ በውስጡ ያካተታቸው ዘመናዊ አደረጃጀቶች፥ የላቁ የድምፅና የምስል ቴክኖሎጂዎች እንዲሁም ሁለገብ የአገልግሎት ክፍሎች ቤተ ክርስቲያኒቱ ዓለም አቀፋዊ ተጽዕኖዋን እንድታጎለብትና ከዘመኑ ፈጣን የመረጃና የሥልጣኔ እመርታ ጋር አብራ እንድትራመድ ያስችሏታል። በታሪክ አጋጣሚዎች ምክንያት በበቂ ሁኔታ ያልተጠቀመችባቸውን ዓለም አቀፍ የመድረክ ዕድሎች በባለቤትነት እንድትመራ፥ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሀብቶቿን ለዓለም ሕዝብ በበቂና በተደራጀ

የመገናኛ መንገዶች እንድታስተዋውቅ፥ እንዲሁም የውስጥ አስተዳደራዊና መንፈሳዊ ሥራዎቿን በከፍተኛ ቅልጥፍና እንድታከናውን ያስችላታል።

ይህ ታላቅ ማእከል የተቋሚን ህልውና የሚያጠናክር፥ የመንፈሳዊ አገልግሎቷን ወሰን የሚያሰፋና ማኅበራዊ አገልጋይነቷን የሚያጎላ ሁለገብ ተቋማዊ ሀብት ሆኖ ይቀጥላል። የማእከሉ ዋና ዋና ተቋማዊ፥ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ፋይዳዎች በሚከተሉት አበይት ነጥቦች ሥር በዝርዝር ይተነተናሉ።

ተቋማዊና ዲፕሎማሲያዊ ፋይዳ (Institutional & Diplomatic Capacity)

ይህ ታላቅ ማእከል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ተቋማዊ አቅምና ዓለም አቀፋዊ የዲፕሎማሲ ተዕዕኖ ወደ ላቀ ደረጃ የሚያሸጋግር ስትራቴጂካዊ መሠረተ ልማት ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱ ቀደም ሲል ይካሄዱ የነበሩ ታላላቅ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሃይማኖት ጉባኤዎችን፥ የሰላም መድረኮችንና የልኡካን ቡድኖች ስብሰባዎችን በሌሎች አዳራሾች ተከራይታ ለማስተናገድ ትገደድ የነበረበትን አሠራር ሙሉ በሙሉ ያስቀራል። በዚህ ማእከል የቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤያትን፥ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤያትን፥ የአህጉረ ስብከት ስብሰባዎችንና የዓለም አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች የሚሳተፉባቸውን ታሪካዊ ክስተቶች በራሷ ግቢ ውስጥ በሙሉ ነፃነትና ግርማ ሞገስ እንድታካሂድ ያስችላታል።

በሌላ በኩልም በማእከሉ ውስጥ የተገጠሙት በአንድ ጊዜ እስከ 6 ለሚደርሱ ቋንቋዎች ቀጥታ የትርጉም አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ ክፍሎች (Simultaneous Translation Booths) እና ዘመናዊ የመልቲሚዲያ የመገናኛ ዘዴዎች ተቋማዊ ዲፕሎማሲዋን እጅግ ውጤታማ የሚያደርጉ ናቸው። ይህም ከምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት፥ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል (WCC)፥ ከአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ (AACC) እና ከሌሎች ልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የሚደረጉ የሁለትዮሽና የብዙ ወገን ውይይቶችን ያለአንዳች የቋንቋና የቴክኖሎጂ እንቅፋት ለመምራት ያስችላታል። በዚህም ቤተ ክርስቲያኒቱ በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላትን ጥንታዊ የሃይማኖትና የታሪክ የበላይነት መድረክ መርታ የመግለጽ፥ የሰላም አምባሳደርነቷን የማጠናከርና ተቋማዊ ውሳኔዎቿን በከፍተኛ ቅልጥፍና የመፈጸም አቅሟን በከፍተኛ ሁኔታ ያጎለብተዋል።

መንፈሳዊና ትምህርታዊ አገልግሎት (Spiritual & Educational Impact)

ይህ ማእከል ከጉባኤ ማካሄጃነት ባሻገር የቤተ ክርስቲያኒቱን ዘመን ተሻጋሪ መንፈሳዊ አስተምህሮ፥ ስብከተ ወንጌልና የትምህርት አገልግሎት ወደ ላቀ ደረጃ የሚያደርስ የትምህርት ማእከል ነው። እጅግ ሰፊ፥ በቴክኖሎጂ የተደራጀና ምቾት ባላቸው 2,800 ወንበሮች የተሟላው ዋና አዳራሽ፥ ከፋፋይ ሁለገብ ክፍሎችና አነስተኛ የቡድን መወያያ ቦታዎች፥ ለመንፈሳዊ ጉባኤዎች፥ ለሃይማኖታዊ ሴሚናሮችና ለሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች መርሐ-ግብሮችን ለማዘጋጀት ሰፊ ዕድል ይፈጥራሉ። ይህም የቤተ ክርስቲያኒቱን ቅዱሳት ድርሳናትና የቀደምት አበውን አስተምህሮ ለአዲሱ ትውልድና ለዘመኑ ምሁራን በሚመጥን መልኩ በጥራትና በስፋት ለማስተላለፍ ያስችላል።

በተጨማሪም ማእከሉ ለአገልጋዮች፥ ለሰባክያነ ወንጌል፥ ለካህናትና ለሰንበት ትምህርት ቤት መምህራን ተከታታይነት ያላቸውን የሥልጠና መርሐ-ግብሮች (Capacity Building Workshops) ለመስጠት ከፍተኛ አመቺነት አለው። በዘመናዊ የድምፅና የምስል ቴክኖሎጂዎች (AV Systems) የተደራጁት ክፍሎች ትምህርቱን በንድፈ-ሐሳብ ብቻ ሳይሆን በምስልና በቪዲዮ የተደገፈ በማድረግ፥ ሰባክያንና መጋቢያን ዘመኑን የዋጀ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ እንዲከተሉ ያስችላቸዋል። ይህም ምእመናንን በሃይማኖት ዕውቀትና በኦርቶዶክሳዊ ሥነ-ምግባር አጽንቶ ለማቆየት፥ አደያዛቸውን ለማጠናከርና የተቋሚን መንፈሳዊ ተልዕኮ በውጤታማነት ለመወጣት የሚያስችል ታላቅ መንፈሳዊ መሠረት ነው።

የታሪክ፥ የቅርስና የዲጂታል ትውስታ ጥበቃ (Heritage Preservation & Digital Future)

ማእከሉ ጥንታውያኑን የመንፈሳዊና ባህላዊ ቅርሶች ባለቤትነት ከዘመን አመጣሽ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ጋር በጥበብ አዋሕዶ የያዘ የታሪክና የዕውቀት ማእከል ነው። በውስጡ የተደራጀው ዲጂታል ቤተ-መጻሕፍት (Digital Library) ጥንታውያን የብራና መጻሕፍትን፥ የታሪክ ሰነዶችንና መንፈሳዊ ድርሳናትን ወደ ዲጂታል ቅርጸት በመቀየር (Digitization) በከፍተኛ ጥራት ጠብቆ ለማቆየት ያስችላል። ይህም የቤተ ክርስቲያኒቱ ዘመናት ተሻጋሪ የዕውቀት ሀብቶች በተፈጥሮ አደጋ፥ በዕድሜ መግፋት ወይም በሰው ሠራሽ ምክንያት እንዳይበላሹና እንዳይጠፉ አስተማማኝ ዋስትና የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ፥ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ተመራማሪዎች፥ ለሊቃውንትና ለተማሪዎች በይነመረብን ያማከለ ሰፊ የምርምርና የጥናት ዕድል ይከፍታል።

በማእከሉ የተገነባው ዲጂታል መዘክር (Digital Museum) የቤተ ክርስቲያኒቱን የታሪክ ጉዞ፥ የጥንታውያን

ቅርጻ ቅርጾች፥ ንዋያተ ቅድሳትና ሃይማኖታዊ እሴቶች መረጃ በዘመናዊ የምስል፥ የድምፅና የባለ ሦስት አውታር (3D) መልቲሚዲያ ቴክኖሎጂዎች ታግዞ ለጎብኚዎች የሚያቀርብ ልዩ የመረጃ ማእከል ነው። ይህ አደረጃጀት በተለይም ለአዲሱ ትውልድና ለውጭ ሀገር ጎብኚዎች የታሪክና የቅርስ መረጃዎችን ማራኪና ፈጣን በሆነ አቀራረብ እንዲረዱ ያደርጋል። በመሆኑም ማእከሉ የቤተ ክርስቲያኒቱን ታሪካዊና መንፈሳዊ ትውስታ በቴክኖሎጂ አስደግፎ ለቀጣዩ ትውልድ የማስተላለፍ፥ ቅርሶቿን ዓለም አቀፋዊ ዕውቅና የማስጨበጥና ጥንታዊቷን ቤተ ክርስቲያን የዲጂታል ዘመን ባለቤት የማድረግ ታላቅ ሀገራዊና ተቋማዊ ፋይዳ አለው።

ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት (Social & Economic Contribution)

ይህ ታላቅ ማእከል ከተቋማዊና መንፈሳዊ ተልዕኮው ባሻገር፥ ለሀገራዊ ማኅበራዊ ትስስርና ለኢኮኖሚያዊ ዘላቂነት ከፍተኛ አስተዋዕኦ የሚያበረክት ሁለገብ ሀብት ነው። በውስጡ የተካተቱት ሰፋፊ አዳራሾች፥ የመሰብሰቢያ ክፍሎችና የኤግዚቢሽን ስፍራዎች ለሃይማኖታዊ ኩነቶች ብቻ ሳይሆን ለተለያዩ አገራዊና ማኅበራዊ ስብሰባዎች፥ ለሰላም ግንባታ መድረኮች፥ ለባህላዊ ሲምፖዚየሞችና ለሳይንሳዊ ጉባኤዎች ክፍት በመሆን ያገለግላሉ። ይህም ማእከሉ ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች፥ ምሁራንና የሕዝብ ተወካዮች የሚገናኙበት፥ ሀገራዊ መግባባትን የሚያጎለብቱበትና ማኅበራዊ እሴቶችን የሚያጠናክሩበት ማእከላዊ የስብሰባ አምባ እንዲሆን ያስችለዋል። ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አንጻር፥ ማእከሉ የገቢ ምንጭ በመሆን የተቋሚን የውስጥ ገቢ እንደሚያሳድግ ለመረዳት አያዳግትም።

በዚህ የሰብሰባ ማእከል ውስጥ በ241 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈው ዘመናዊ የኢንዱስትሪ ኩሽና፥ የምግብና የመስተንግዶ አገልግሎቶች እንዲሁም ሁለገብ አዳራሾች ለተለያዩ ይፋዊ ፕሮግራሞችና የራት ግብዣዎች (Catering & Banquet Events) በመከራየት ለቤተ ክርስቲያኒቱ ዘላቂና አስተማማኝ የገቢ ምንጭ ይፈጥራሉ። በተጨማሪም፥ የማእከሉ በከፍተኛ ደረጃ መደራጀት በዙሪያው ለሚገኙ ዜጎች ሰፊ የቴክኒክ፥ የጽዳት፥ የመስተንግዶና የደህንነት የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር ለከተማዋ የንግድና የስብሰባ ቱሪዝም (MICE Tourism) ዕድገት የጎላ ድርሻ ያበረክታል።

ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፍ የስብሰባ ማእከል ግንባታ ፕሮጀክት እውን መሆን ቤተ ክርስቲያኒቱ ከዘመኑ የቴክኖሎጂ፥ የሥነ-ሕንጻና የተቋማዊ አደረጃጀት እመርታ ጋር እጅ ለእጅ ተጨባብጣ ለመጓዝ የቆረጠችበትን ጽኑ አቋም የሚያሳይ ታላቅ ታሪካዊ ምዕራፍ ነው። ይህ ዘመናዊ መሠረተ ልማት የቤተ ክርስቲያኒቱን ዘመናት ተሻጋሪ መንፈሳዊ ልዕልና፥ ዲፕሎማሲያዊ ተጽዕኖና ማኅበራዊ አገልጋይነት ወደ ላቀ ከፍታ የሚያሸጋገር የኩራት ማእከል ነው። ከዕንሰ-ሐሳብ እስከ ፍጻሜው ባሉት አስደናቂ የጉዞ ማዕዘኖች ውስጥ፥ ፕሮጀክቱ ስኬታማ እንዲሆን የብዙዎች ድካም፥ ጥበብና እምነት ታክሎበታል። በተለይም ይህ ታላቅ ሕንጻ ዛሬ ለደረሰበት ግርማ ሞገስና ዓለም አቀፍ ደረጃ መብቃት የቤተ ክርስቲያኒቱ ቅዱሳን ፓትርያርኮች፥ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፥ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና መላው ሕዝበ ክርስቲያን ያበረከቱት አስተዋጽኦ እጅግ የላቀና በታሪክ የሚዘከር ነው። ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት ለፕሮጀክቱ መሳካት ያደረጉት አባታዊ ጸሎት፥ ቁርጠኝነትና የሰመረ መሪነት የኩነቱ ዋና ማዕቀፍ ነበረ። የቤተ ክርስቲያኒቱን ሁለንተናዊ ዕድገትና ክብር አስቀድመው በማሰብ ያደረጉትን የሞራልና የሥራ ድጋፍ መላው ሕዝበ ክርስቲያን በታላቅ አክብሮት የሚያስታውሰው ነው።

በዚህ አባታዊና ተቋማዊ መሪነት ሠንሰለት ውስጥ፥ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የፕሮጀክቱን እያንዳንዱን ሂደት ከጅማሬው እስከ ፍጻሜው በቀጥታ በመከታተል፥ በቅርበት በመመራትና ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በላቀ ጥንቃቄ በመምራት ያበረከቱት አስተዋጽኦ የፕሮጀክቱ የጀርባ አጥንት ሆኖ አልፏል። ብፁዕነታቸው ግንባታው ጥራቱን የጠበቀ፥ በታቀደለት የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚጠናቀቅና ለቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪካዊ ክብር የሚመጥን እንዲሆን በቀንና በሌሊት ያደረጉት ያላሰለሰ የቅርብ ክትትል ማእከሉ ዛሬ ለሚታየው ዘመናዊ ገጽታና ስኬት መብቃቱ ቁልፍ ምክንያት ነው። ይህ የቁርጠኝነትና የዕለት ተዕለት የቁጥጥር ሥራ የፕሮጀክቱን ባለቤትነት ስሜት በማዳበር ረገድ አርአያነት ያለው ታሪካዊ አሻራ ጥሏል።

ይህ ዓለም አቀፍ የመሰብሰቢያ ማእከል የትውልድ አደራን ተቀብሎ ለቀጣይ ዘመናት የሚሻገር፥ የቤተ ክርስቲያኒቱን ሉዓላዊነትና ተቋማዊ አቅም የሚያጸና፥ እንዲሁም የሰላም፥ የትምህርትና የመንፈሳዊ አንድነት መድረክ ሆኖ ለዘለዓለም ይኖራል። የተከናወነው ታላቅ ሥራ የትናንቱን ታሪክ ከነገው የዲጂታልና የዘመናዊ ዓለም አቀፍ ግንኙነት ጋር የሚያገናኝ ሕያው ድልድይ ሆኖ ይቀጥላል።

በጠቅላይ ቤተ ክህነት ተሠርተው የተጠናቀቁ እና ጅምር የልማት ሥራዎች

መጋቤ ሃይማኖት ጌታባለው አድማሱ
የቤቶችና ሕንጻዎች አስተዳደርና ልማት ድርጅት
የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዋና ክፍል ኀላፊ

መግቢያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ የሀገርና የሕዝብ አለኝታ በመሆን፣ በሃይማኖታዊ፣ በማኅበራዊ፣ በትምህርታዊና በባህላዊ መስኮች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስታበረክት የቆየች ታሪካዊ ተቋም ናት። በዘመናዊው ዓለም ቤተክርስቲያን የተጣለባትን ታላቅ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ኃላፊነት በጥራትና በፍጥነት መወጣት እንድትችል ተቋማዊ አሠራሯን ማዘመን፣ የመልካም አስተዳደር መርሖችን ማስፈን፣ የፋይናንስና የንብረት ቁጥጥር ሥርዓቱን ማጠናከር እንዲሁም የልማት ፕሮጀክቶችን በስኬት መምራት ወሳኝ ጉዳይ ሆኖ በመገኘቱ ዘመኑን የዋጀ የአመራር ስልት በመንደፍ ቤተክርስቲያንን የሚታደጉ የሥራ ኃላፊዎች እንደሚስፈልጉ ግልጽ ነው።

ይህንን የተረዳው የቅድስት ቤተክርስቲያን የበላይ መሪና የሐዋርያት አሠረ ፍኖት ተቀባይ የሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ በግንቦት 2017 ዓ.ም. በቅዱስ መንፈስ እየተመራ ለሁለት ሳምንታት ያህል ሲያካሂድ የቆየውን ጉባኤ ሲያጠናቅቅ ለቀጣዮቹ ሦስት ዓመታት ቅድስት ቤተክርስቲያንን በሁለት ቁልፍ የኃላፊነት ቦታዎች እንዲመሩ የመረጣቸውን ሁለት ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት ለሕዝበ ክርስቲያኑ ይፋ አደረገ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ እነዚህን ሁለት ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት ለቤተክርስቲያን የመሪነት ቦታዎች የመረጠበት ውሳኔ በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ልዩ የሚባል ምዕራፍ የታየበት እንደነበር በብዙዎች ይታመናል።

ምክንያቱም ከዚህ በፊት ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ የመንበረ ፓትሪያርክ ጠቅላይ ቤተክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው፣ በዚያው ተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ ደግሞ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ፀሐፊነት ኃላፊነትን ይዘው ለሦስት ዓመታት ባገለገሉበት ወቅት የኃላፊነት ዘመናቸውን በመናበብ፣ በመደማመጥና በስኬት ተወጥተዋል። ስለሆነም በሌላ ምርጫ ደግሞ በ2017 ዓመተ ምሕረት ከቀረቡት ዕጩዎች መካከል ከፍተኛውን ድምፅ በማግኘት ዳግም ቤተክርስቲያንን በኃላፊነት እንዲመሩ በቅዱስ ሲኖዶስ ተመርጠው በታላቅ መንፈሳዊ ቅናት፣ ትጋትና ስኬት እያገለገሉ ይገኛሉ። ይህም በዓይነቱ ልዩ ያደርገዋል።

የብፁዕ ወቅዱስ ሥራ አስኪያጅ በጎ የሥራ አፈጻጸም

ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የመንበረ ፓትሪያርክ ጠቅላይ ቤተክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም የደቡብ ምዕራብ ሸዋና ሸገር ከተማ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው በቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ከተመረጡ በኋላ ባለው የሐዋርያዊ አገልግሎት ጊዜያቸው የቤተክርስቲያኒቱን መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች በተመለከተ ከቀደመውና ነባሩ አሠራር ጠንካራውን በማስቀጠል፣ ለደከመውና እንቅፋት ለሆነው ደግሞ አዳዲስ መንገዶችን በመከተል፣ እንዲሁም ከቤተክርስቲያኗ ክብር፣ ታሪክና ተልዕኮ ጋር የማይሞኑ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን አስጠንተው ጥቅም ላይ በማዋል የኃላፊነት ቦታው የሚጠይቀውንና የሚጠበቀውን በብቃት እያከናወኑ ይገኛሉ።

የመንበረ ፓትሪያርክ ጠቅላይ ቤተክህነት ጽሕፈት ቤት በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወሰኑ ውሳኔዎችን በሥራ ላይ የማዋልና መላዋን ቤተክርስቲያን የማስተዳደር ትልቅ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ሰፊ ጥበብ ይጠይቃል። ከዚህ አንጻር የጽሕፈት ቤቱ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ኃላፊነት ከተረከቡ በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ ቀደም ብለው የተጀመሩ የልማት ሥራዎች አስፈላጊው ጥናት ተደርጎላቸው እንዲጠናከሩ አድርገዋል። በጅምር ተጓትተው የቀሩና የጥራት ጉድለት የነበረባቸውን ፕሮጀክቶች ደግሞ የዲዛይን ክለሳና የዋጋ ማሻሻያ በማድረግ አስቀጥለዋል።ብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ በዝምታና በጽናት እየገነቡት ያለው ይህ መሠረት የሣሬውን ችግር የሚቀርፍ ብቻ ሳይሆን፣ ነገ የሚመጣውን ትውልድ ከተደቀነበት የሞራል፣ የመንፈስና የማኅበራዊ ውድቀት የሚያድን

ታላቅ መሸጋገሪያ ነው። ዛሬ በዓለማችን ላይ የሚታየው የቴክኖሎጂ አሉታዊ ጎኖችና የመንፈሳዊ እሴቶች መሸርሸር አዲሱን ትውልድ ለታላቅ አደጋ ባጋለጠበት በዚህ ወቅት፣ ብፁዕነታቸው ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ትውልድ አስተማማኝ መጠጊያና የጽድቅ መኖሪያ እንድትሆን ቀድመው በመመልከት ታላቅ ራዕይ ሰንቀዋል። የብፁዕነታቸው ጥረትና የተቀረጹት ስትራቴጂዎች ቤተ ክርስቲያንን ከሰው እጅ ጥገኝነት በማዳን በራሷ መንፈሳዊ ልዑልነትና ነፃነት እንድትቆም የሚያደርጉ፣ አዲሱ ትውልድ ሃይማኖቱንና ታሪኩን አውቆ በተደላደለና በጸና መሠረት ላይ እንዲኖር የሚያስችሉ፣ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያናችን ለሀገርም ጭምር የሰላምና የዕርቅ ማዕከል ሆና እንድትቀጥል የሚያስችሉ ሲሆኑ በአጠቃላይ የ18 ወራት የብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ የአመራር ዘመን በዝምታ በተሠራ ታላቅ ታሪክና በታላቅ የለውጥ መንፈስ የሚታወቅ ሲሆን፣ እሳቸው በቃላት ብዛት የሚገለጡ መሪ ሳይሆኑ በሥራ ፍሬያቸው የሚመሰከረላቸው ታማኝ መሪ መሆናቸውን አባዛኛው ሰው ይስማማበታል።

በጠቅላይ ቤተክህነት ቅጽር ግቢ የተከናወኑ የልማትና የማስዋብ ሥራዎች

በየትኛውም የሥራ ሥፍራ የሥራ ክባቢው ምቹ ካልሆነ ሠራተኛው የመሥራት ፍላጎትና ተነሳሽነት አይኖረውም ተብሎ ይታመናል። ብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ይህንን መርሕ መሠረት በማድረግ የመጀመሪያ ተግባራቸው ያደረጉት የጽሕፈት ቤቱን ቅጥር ግቢ ማስዋብና ለሠራተኛው ምቹ ክባቢ መፍጠር ነበር። ቀደም ሲል የነበረው የጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ግቢ የተቋሙን ክብር የማይመጥን፣ በአሮጌ መኪናዎችና በቆሻሻ የተሞላ፣ ደረጃውን ያልጠበቀና የማይማርክ ገጽታ እንደነበረው የማይካድ ሐቅ ነው።ይህንን ሁኔታ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመለወጥ አሮጌ መኪናዎችን በሕጉ መሠረት በማስወገድ፣ ግቢው ለመኪና ማቆሚያም ሆነ ለእይታ ማራኪ እንዲሆን በማድረግ፣ የቤተክርስቲያኒቱን አጠቃላይ ሁኔታ ሊገልጽ የሚችል የግቢ ዲዛይን አደረጃጀት በባለሙያዎች አስጠንተው ሥራውን ተግባራዊ ሲያደርጉ በየቀኑ በመከታተልና ሠራተኞችን በዕዳት ዘመቻ በማሳተፍ የጠቅላይ ቤተክህነት ጽሕፈት ቤት ግቢ ውብና ማራኪ እንዲሆን ተደርጓል።

በተለይም ከጽሕፈት ቤቱ ጀርባ ያለውና ተነክቶ የማያውቀው በጫካ የተሞላው ቦታ ሙሉ በሙሉ ተስተካክሎ እንግዶችን ለመቀበል የሚያስችል ክብር ያለው ቦታ ሆኗል። በተጨማሪም የቅዱስ ፓትሪያርኩ መውጫና መግቢያ በር ከዚህ ቀደም የሁሉም ሰው ማለፊያ የነበረ ቢሆንም፣ አሁን ግን ለዲፕሎማቶችና ለከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት የተለየ መግቢያና መውጫ እንዲሆን ተደርጎ በዘመናዊ አጥር በመታጠሩ የተቋሙን ክብር ማስጠበቅ ተችሏል። እነዚህ በ18 ወራት ውስጥ የተከናወኑ ተግባራት ለሠራተኞች ምቹና የሚያስናፍቅ የሥራ አካባቢ መፍጠር ችለዋል።







የተጓተቱና በግንባታ ላዩ ያሉ ፕሮጀክቶች ከፈጸሙም

ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ባለፉት 18 ወራት በነበራቸው የአመራር ጊዜ የጽሕፈት ቤቱን የትኩረት አድማስ በማስፋት የቤተክርስቲያን ተልዕኮን ለማሳካት ወሳኝ በሆኑ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ላይ አተኩረዋል። በቅድሚያ ተጀምረው የተቋረጡና የአፈጻጸም ጉድለት የታየባቸው የልማት ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ተደርጓል። ከእነዚህም መካከል በአሮጌው ቁራ አካባቢ ሚገኙ ሁለቱ ሕንጻዎች ሕያው ምስክሮች ናቸው።

በአሮጌ ቁራ አካባቢ የሚገኙ ሕንጻዎች

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 (አሮጌ ቁራ) በ480 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈው ባለ 10 ወለል ሕንፃ ግንባታ የዋጋ ማሻሻያ ተጨማሪ ጥናት ተደርጎለት በ56 ቀናት ውስጥ ተጠናቆ እንዲቀርብ በሰጡት አባታዊ መመሪያ መሠረት ተጠናቆና ተመርቆ ለኪራይ ዝግጁ ሆኗል። በተመሳሳይ ሳይት በ1,000 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈው ሁለተኛው ሕንፃ በብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ በተሰጠው ቀጥታ አመራርና ክትትል መሠረት ግንባታው ተጠናቆ ለምርቃት በቅቷል። በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 (ባሻ ወልዴ) የሚገኘው ባለ 2 ቤዝመንትና 7 ፎቅ (2B+7) የመኖሪያ ሕንፃ የነበረበት የፍሳሽና የጥራት ችግር ተፈትቶ አገልግሎቱ እንዲቀጥል ተደርጎ በነዋሪዎቹ ዘንድም ምስጋናን አትርፏል።

ከዳዲስ ግዙፍ የልማት ፕሮጀክቶች

የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተክህነት ጽሕፈት ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስና የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ በፒያሳ፣ በአራት ኪሎና በአሮጌ ቁራ አካባቢዎች ታላላቅ ሕንጻዎችን ለመገንባት በጨረታ ያሸነፉ ኮንትራክተሮችን በመለየት ቦታዎቹን አስረክበዋል። እነዚህ ፕሮጀክቶች የቤተክርስቲያኗን ዘላቂ የመዋዕለ ነዋይ አቅም ለማጠናከር የተነደፉ ናቸው።

ፕሮጀክት 1፦ አበው ሕንጻ

ሕንጻ አበው በአራት ኪሎ አካባቢ ከጠቅላይ ቤተክህነት ጀርባ ባለው 6,000 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የሚገነባ ግዙፍ ሁለገብ ሕንጻ ነው። ይህ ሕንጻባለ 2 ቤዝመንት + 1 ንዑስ ቤዝመንት + ግራውንድ + 12 ወለል ፎቅ (B2 + Sub-Basement + G + 12) ሲሆን ያረፈበት የቦታ ስፋትም 6,000 ካሬ ሜትር ነው። ይህን ሕንጻ አተም ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ (Atem General Contractor)ኢኢኤስ አማካሪ አርክቴክቶች እና ኢንጅነርስ ኃ/የተ/የግል ማህበር (EES Consulting Architects & Engineers PLC) በኃላፊነት የሚመሩት ሲሆን ከጥር 05 ቀን 2018 ዓ.ም. ጀምሮ 5,343,125,562.68 ብር (አምስት ቢሊዮን ሦስት መቶ አርባ ሦስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሀያ አምስት ሺህ አምስት መቶ ስድስት አራት ከ 68/100 ETB) በላይ በሚገመት ጠቅላላ የውል ዋጋ በ900 ቀናት (30 ወራት) ይጠናቀቃል ተብሎ ይታመናል።

ሕንጻ አበው ከምድር እስከ 4ኛ ፎቅ ለተለያዩ የንግድ አገልግሎቶች እንዲሆን የታሰበ ሲሆን ከ5ኛ እስከ 12ኛ ፎቅ ለመኖሪያ ቤት አገልግሎት ይውላል ተብሎ ይጠበቃል። ይህ ሕንጻ ከያዛቸው ዘመናዊ የመኖሪያና የንግድ ቤቶች በተጨማሪ በአንድ ጊዜ 302 መኪኖችን ማቆም የሚያስችል ሰፊ ቤዝመንት አለው።



ፕሮጀክት 2፦ ዝክረ ቅዱሳን ሕንጻ

ዝክረ ቅዱሳን ሕንጻ በፒያሳ አካባቢ የሚገነባ ሁለገብ የንግድና የመኖሪያ ሕንጻ ሲሆን 2 ቤዝመንት + ግራውንድ + 7 ወለል ፎቅ (B2 + G + 7) እና 1,686 ካሬ ሜትር (በዲዛይን ደረጃ) መሆኑን የታወቀ ነው። ይህን ሕንጻ ምንሀር ኮንስትራክሽን (Minhar Construction)ና ኢኢኤስ አማካሪ አርክቴክቶች እና ኢንጅነርስ ኃ/የተ/የግል ማህበር (EES Consulting Architects & Engineers PLC) በጎለፊነት ሲሆን ውል ከታሰረበት ቀን ጀምሮ በ20 ወራት (600 ቀናት) ተጠናቆ ለአገልግሎት ክፍት እንደሚሆን ይጠበቃል።

ዝክረ ቅዱሳን ሕንጻ ከምድር እስከ 4ኛ ወለል ድረስ ለንግድ እና ለቢሮ አገልግሎት የሚውል ሲሆን ከ5ኛ እስከ 7ኛ ወለል ድረስ ለመኖሪያ ቤት አገልግሎት የሚውል ከመሆኑ ባሻገር በአንድ ጊዜ 62 መኪኖችን የማቆም አቅም አለው።



ፕሮጀክት 3፦ በአሮጌው ቁራ የሚገነባው ቅይጥ አገልግሎት ሕንጻ



የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በኮሪደርና በወንዝ ዳር ልማት ምክንያት በፈረሱ ቤቶች ምትክ ከመንግሥት በተረከበቻቸው ቦታዎች ላይ በምታካሂደው የልማት እንቅስቃሴ መሠረት በአሮጌው ቁራ አካባቢ የሚገነባው ሁለገብ አገልግሎት ሕንጻ አንዱ ሲሆን በ875 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ3 ቤዝመንት + ግራውንድ + 13 ወለል (B3 + G + 13) ቅይጥ አገልግሎት የሚውል ሕንጻ ነው።ይህንን ሕንጻ አዶር ኮንስትራክሽን (Ador Construction)ና ዱኃርቃ አማካሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር (Duharka Consultants PLC) በጎላፊነት ይመሩታል።ይህ ሕንጻ ከምድር ወለል 1ኛ ወለል እና 13ኛ ወለል ለተለያዩ የንግድ፣ የባንክ እና የጂም (Gym/Fitness) አገልግሎቶች የተመደበ ሲሆን ከ2ኛ እስከ

12ኛ ወለል ለመኖሪያ ቤት አገልግሎት የሚውልና በአጠቃላይ 55 የመኖሪያ ቤቶችን (አፓርትመንቶችን) በውስጡ ያካተተ ከመሆኑም ባሻር በአንድ ጊዜ 69 መኪኖችን ማቆም የሚያስችል ዘመናዊ የ3 ቤዝመንት ፓርኪንግ አቅም ያለው ነው።

ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በታሪኳ ሁሉ ታላላቅ ሥራዎችን የሠሩ፣ የመንፈስ ቅዱስ ሀብት የደረሳቸውና የመንጋውን ድኅነት ያረጋገጡ አበውን ስታስታውስ የምትኖረው በጨኸትና በእልልታ ሳይሆን በጽኑ ጸሎት፣ በበሰለ እቅድና በዝምታ በተሞላ ታላቅ ሥራቸው ነው። ጥበበኛው ሰሎሞን "ለሥራ ሁሉ ጊዜ አለው" እንዳለው፣ የዛሬዋ ቤተ ክርስቲያናችን ከቃላት ይልቅ በተግባር፣ ከወሬ ይልቅ በእውቀትና በሥራ የምትመራበት ልዩ ታሪካዊ ምዕራፍ ላይ ትገኛለች። በዚህም ረገድ የብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ አመራር በግልጽ የሚታየውን ያህል በዝምታና በውስጥ የሚከናወነው ተጋድሎአቸው እጅግ የላቀና የሚደነቅ ነው። የብፁዕነታቸው የአመራር ብቃት መሠረቱ መንፈሳዊ ትህትናን ከዘመናዊ አስተዳደራዊ ብስለት ጋር አዋሕዶ የያዘ በመሆኑ፣ በቤተ ክርስቲያናችን የጠቅላይ ቤተ ክህነት መንበር ላይ ተቀምጠው የአስተዳደር መዋቅሩን ማስተካከልና ማዘመን ችለዋል። የውስጥና የውጭ ፈተናዎች በሚበዙበት በዚህ ጊዜ ብፁዕነታቸው ያሳዩት አመራርና ጥበብ እጅግ የሚያስደንቅ ሲሆን፣ የሚሠሩት ሥራ ሁሉ ከግብዝነት የጸዳና "የግራ እጅህ የሚሠራውን ቀኝ እጅህ አይወቅ" የሚለውን የጌታችንን አስተምህሮ መመሪያ ያደረገ ነው።

አሁን ባለንበት ወቅት በጠቅላይ ቤተ ክህነት ደረጃ የሚከናወኑት ሁለንተናዊ የልማት፣ የአስተዳደር፣ የወንጌል አገልግሎትና ሕገ ቤተ ክርስቲያንን የማስጠበቅ ሥራዎች በሙሉ የብፁዕነታቸውን ራዕይና የዕለት ተዕለት የትጋት ውጤት የሚያንጸባርቁ ናቸው። በልማትና በኢኮኖሚ አቅም ግንባታ በኩል፣ ቤተ ክርስቲያኗ በመንፈሳዊ አገልግሎቷ ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚያዊ ራስን በመቻል አቅሟም እንድትጠናከር የቤተ ክርስቲያኗን ሀብትና ንብረት በአግባቡ የማስተዳደር፣ ባዶ ቦታዎችንና ይዞታዎችን ወደ ገቢ ማስገኛ ፕሮጀክቶች የመቀየር፣ እንዲሁም የካፒታል ልማቶችን በዘመናዊ መልኩ የመምራት ሥራዎችን እያከናወኑ ይገኛሉ።

ለዚህም ትልቁ ማሳያ ከ9 ዓመታት በፊት ተጨማሪ ገቢ ለማስገኘት ታስቦ የመሠረት ድንጋይ ከተጣለ በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች ሳይፈጸም የቆየውና ለተጨማሪ ወጪ ዳርጎ የነበረውን አሠራር ለመቀየር፣ ብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁና ብፁዕ የቅዱስ ሲኖዶስ ፀሐፊ የውል ማሻሻያ በማድረግ ሥራዎች በተያዘላቸው ቀነ ገደብ እንዲጠናቀቁ አስገዳጅ ውል መዋዋላቸው ቤተክርስቲያንን ከተጨማሪ ወጪ ከመታደጉም በላይ ተጨማሪ ገቢ የምታገኝበትንና ተጨማሪ ሕንጻዎችን ለመስራት የሚያስችላትን አቅም እንድታደርጅ ማገዙ ትልቅ ማሳያ ነው።የተጀመሩት ፕሮጀክቶች የቤተክርስቲያንን አገልግሎት ለማቀላጠፍ የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ አቅም የሚገነቡበት በመሆናቸው በተያዘላቸው ቀነ ገደብ ለፍፃሜ ማድረስ ትልቅ ትኩረት መሰጠቱም ሌላው አንቱታን የተረፈው የብፁዕነታቸው ሥራ ነው።በአስተዳደርና በመዋቅራዊ ማሻሻያ ረገድ ደግሞ የአሠራር ብልሹነቶችን በማስወገድ፣ የሰው ኃይል አስተዳደሩን በዕውቀትና በችሎታ ላይ የተመሠረተ በማድረግ፣ የዲጂታል አሠራር ሥርዓቶችን በመዘርጋትና የመልካም አስተዳደር መርሖችን በመተግበር በጠቅላይ ቤተ ክህነት ውስጥ አዲስ ሕይወት ዘርተዋል። በተመሳሳይ መልኩ፣ የወንጌል አገልግሎት በየአህጉረ ስብከቱና በየገጠሩ በሰፊው እንዲስፋፋ፣ ሰበካ ጉባኤያት እንዲጠናከሩና በየቋንቋው የሚሰጡ የአገልግሎት መድረኮች እንዲጎለብቱ በማድረግ የወንጌልን ተልዕኮ በብቃት እየተወጡ ይገኛሉ። ከሁሉም በላይ ደግሞ የቤተ ክርስቲያናችን ዋስትና የሆነውን ሕገ ቤተ ክርስቲያንና ቀኖናን በመጠበቅ፣ በተለያየ ጊዜ የሚነሱ የቀኖና ጥሰቶችንና ሕገ-ወጥ አሠራሮችን በትዕግሥት፣ በሕጋዊ መንገድና በቁርጠኝነት በመከላከል የቤተ ክርስቲያኗን ክብርና አንድነት በአስተማማኝ ሁኔታ አስጠብቀዋል።

በአጠቃላይ በቤተ ክህነት ደረጃ አሁን እየተከናወኑ ያሉ ሁለንተናዊ ሥራዎች በሙሉ ቤተ ክርስቲያናችንን ከነበረችበት ፈተና አሻግረው ወደ ተሻለ ታሪካዊ ከፍታ የሚያሸጋገሩ ናቸው። ይህ በዝምታ የሚከናወን ተጋድሎና አርቆ አስተዋይነት የተሞላበት አመራር፣ ነገ የቤተ ክርስቲያን ተረካቢ የሚሆነውን አዲሱን ትውልድ ከተደቀኑበት በርካታ አደጋዎች የሚያድን፣ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በጽኑና በተደላደለ መንፈሳዊና ቁሳዊ መሠረት ላይ የሚያስቀምጥ ተስፋ ሰጪ እርምጃ ነው። የብፁዕነታቸው አገልግሎትና ዕይታ ለቤተ ክርስቲያናችን ዘላቂ ህልውናና ለአዲሱ ትውልድ ብሩህ አየርን የፈጠረ በመሆኑ፣ ይህ ጥረትና የዝምታ ፍሬ በታሪክ ማህደር ውስጥ በወርቅ ቀለም ተጽፎ የሚኖር ታላቅ ገድል ነው። እግዚአብሔር አምላክ ለብፁዕነታቸው ረጅም ዕድሜን፣ መንፈሳዊ ጥበብንና ኃይልን አብዝቶ እንዲሰጣቸውና የጀመሩትን ታላቅ የትውልድ ማሸጋገር ሥራ ፍጻሜውን እንዲያሳምርልን የሁላችንም ምኞትና ጸሎት ነው።





መግቢያ

በኢትዮጵያ የፌዴራል ሕግ ውስጥ "በመገናኛ ብዙኃን ዐዋጅ" መሠረት መገናኛ ብዙኃን ማለት በየወቅቱ የታተመ ኅትመት፥ ሬዲዮ፥ ቴሌቪዥን፥ ቪዲዮ ፕሮግራም፥ የዜና ማሰራጫ ፕሮግራምና ሌላ ዓይነት ወቅታዊ መረጃዎችን የማሠራጨት ሌላ ዓይነት ማለት ነው። V.P. Pugachev ሚዲያን ይተረጉመዋል፦ "ለየት ያሉ ቴክኒካዊ መሣሪያዎችን በመጠቀም የተለያዩ መረጃዎችን ለሕዝብ ክፍት፥ በይፋ ለማስተላለፍ የተፈጠሩ ተቋማት" ናቸው።

በዛሬው ጊዜ የመገናኛ ብዙኃን ማለት ወቅታዊ፥ የመስመር ላይ ኅትመቶች፥ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች፥ የሬዲዮ ቻናሎች፥ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች፥ የሬዲዮ ፕሮግራሞች፥ የቪዲዮ ፕሮግራሞች፥ የዜና ማሰራጫ ፕሮግራሞችና ሌሎች ወቅታዊ መረጃዎችን በቋሚ ስም (ርእስ) ሥር ማሠራጨት ማለት ነው።

በዚህ ረጅም ዘመን የራሷ የሆነ የብሮድካስት ሚዲያን በአጭሩ ዕንስ ሐሳብ አቅርቧል። ቤተ ክርስቲያን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለመስበክ፥ ክርስቲያናዊ እሴቶችን ለማስተማርና ማኅበራዊ ኃላፊነቶችን ለመወጣት ሚዲያን ከሰባ አምስት ዓመታት በፊት መሥርታለች። ለማቋቋም ዋና ተዋናዮች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከፍተኛ ባለሥልጣናት ናቸው። በተጨማሪም የተቋቋመው ሚዲያ ለቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ አገልግሎት፥ ክርስቲያናዊ እሴቶችና ማኅበራዊ ኃላፊነቶች ያበረከቱት አስተዋፅኦ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሚዲያ ላለፉት ሰባ አምስት ዓመታት ያሳየው ጠንካራና ደካማ ጎኖች ይብራራል።

ከርእሱ ጋር የተያያዙ የተለያዩ ጽሑፎችን የመገምገምና የመተንተን ዘዴ ተካሂዷል። በዚህ መሠረት በፕሬስ ንድፈ ሐሳቦች ላይ በመመስረት ጥናቱ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷን ተደራሽ ለማድረግ የሄደችበትን ርቀት ያሳየናል። ይህ ጥናት ከኅትመት ሚዲያው በተጨማሪ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቴሌቪዥን እንዴት እንደተቋቋመና በየጊዜው እድገት እያሳየ ዛሬ ለደረሰበት ደረጃ ሊበቃ የቻለበትን በጥልቀት ዳስሷል።

በሃያ አንደኛ ክፍለ ዘመን መገናኛ ብዙኃን በብሮድካስትና በዲጂታል ዘመን ወደ አዲስ መድረክ መምጣት ሰዎች ዓለምን በሁለት አስፈላጊ ሚዲያዎች ማለትም በኅትመትና በቴሌቪዥን እንዴት እንደሚያዩ እይታን በማዳበር ረገድ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል። እነዚህ ሁለቱ ሚዲያዎች በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ዝንባሌ የሚመሩበት በሰዎች ላይ ተዕእኖ የሚያሳድሩና አዳዲስ የመገናኛ መንገዶችን የሚፈጥሩበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

የመገናኛ ብዙኃን በዓለም ላይ በኅብረተሰቡ አመለካከት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ይታወቃል። McQuail የብዙኃን መገናኛዎች የሕዝብን ትኩረት በመሳብና በመምራት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳላቸው ማኅበረሰብ ተዕእኖዎች ከፍተኛ አቅም እንዳላቸው ተናግረዋል። በአመለካከትና በእምነት ጉዳዮች ላይ ማሳመን፥ በባሕሪ ላይ ተዕእኖ ማሳደር፥ የእውነታውን ትርጓሜዎች ማዋቀር፥ ደረጃና ሕጋዊነት መስጠት፥ በፍጥነትና በስፋት ማሳወቅ ነው ይላል (McQuail፥1994፡324)። ነገር ግን በርካታ ምክንያቶች የመገናኛ ብዙኃን በኅብረተሰብ ውስጥ ያለውን ሚና በአወንታዊም ሆነ በአሉታዊ ተዕእኖ ይታያሉ።

የመገናኛ ብዙኃን በኢትዮጵያ ውስጥ ከተቋቋመ ጀምሮ አጭር ዕድሜ ያለው ነው። በምዕራባውያን ማኅበረሰቦች ውስጥ ያሉ የሚዲያ አውታሮች ረጅም ዕድሜን ያስቆጠሩ፥ ማንኛውንም የዜና መጣጥፍ

እንደፈለጉ የሚያቀርቡበት ሚዲያ ነው። ነፃነቱም ስላላቸው የፈለጉትን ያቀርባሉ። ነገር ግን ወደ ታዳጊ ሀገሮች ስንመጣ እንደ ኢትዮጵያ የፖለቲካና የሚዲያ አደረጃጀት ከምዕራቡ ዓለም በእጅጉ የሚለይበት በርካታ ነገሮች አሉ።

በሀገራችን ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ እየታዩ ያሉ አወንታዊ እድገቶች ቢኖሩም፤ በኢትዮጵያ ውስጥና በዓለምም የመንፈሳዊ መገናኛ ብዙኃን በነፃነት እየሠሩ ነው ለማለት አይቻልም። ይሁን እንጂ ከዚህ ዘመን ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያን ለማቋቋም በቅታለች። በንጉሡ ዘመንም የራሷ ሬዲዮ ሥርጭት ነበራት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሚዲያ በአብዛኛው ማስተማር ላይ የሚያተኩር ነው። የሕዝብን ጥቅም ከማገልገል አንጻር ሚዲያው ተደራሽ መሆን አልቻለም። ጎትመቶቹም 75 ዓመታት ቢያስቆጥሩም የሥርጭት አድማሳቸው የተወሰነ በመሆኑ አስፈላጊውን የስብከተ ወንጌል ለማኅበረሰቡ ሰጥተዋል ማለት አይቻልም።

በሀገራችን ሁለቱም ሚዲያዎች ለሰላም ግንባታና ለሀገር አንድነት ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው። ስለዚህ ሁለቱ ሚዲያዎች በተናበበ ሁኔታ በሀገራችን አከራካሪ ጉዳዮችን በማንሣት ችግሮች መፍትሔ እንዲያገኙ ያደረጉት ጥረት ሊመረመርና ሊጠና ይገባል። ከሚዲያ አንጻር ኢትዮጵያ ውስጥ የተካሄዱ ጥናቶች በአብዛኛው የሚያተኩሩት ዓለማዊ ሚዲያዎች ላይ ነው። ማለትም እንደ መንግሥታዊ/ፖለቲካዊ ተፅዕኖና ጫናዎች፥ ሳንሱርና ሌሎች አስተዳደራዊ እንቅፋቶች ላይ ነው። የቤተ ክርስቲያኗ ሚዲያ ላይ የተሠሩ ጥናቶች የሉም። እንደ ተመራማሪው ግንባቤ የቤተ ክርስቲያኗ ሚዲያ ላይ በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምሁራን የተደረጉ ጥናቶች አለመኖራቸው ተመራማሪው ትኩረት እንዲሰጥበት አድርጎታል።

ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ጥልቅ የሆነ የክርስትና ታሪክና ቅርስ ያላት ሀገር ናት። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም የሀገራችን መንፈሳዊ፥ ባህላዊና ታሪካዊ የታሪክ ድርሳን ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ያላት ተቋም ናት። ቤተ ክርስቲያኗ ለዘመናት ቅዱሳት መጻሕፍትንና ሌሎች የጽሑፍ ሥራዎችን በማዘጋጀት መንፈሳዊ አስተምህሮዋንና ትውፊቷን፥ የቅዳሴና የጸሎት ሥርዐቷን፥ የቅኔና የዝማሬ ትውፊትዋን፥ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንና የሀገር ታሪክን ከትውልድ ወደ ትውልድ በማስተላለፍ በዛሬዋ ኢትዮጵያ መልክ ደምቃ የምትታይ ሀገር የገነባች፥ ሕዝብን ያስተሳሰረች ተቋም ናት። ፊደል ቀርጻ፥ ብራና ፍቃ፥ ቀለም በጥብጣ፥ ሥርዓተ ጽሕፈትና ሰዋስው አደራጅታ በማስተማር ሀገር እንደ ምሰሶ እንዲቆም ያደረገችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፥ ዘመናዊ የጎትመት መሣሪያ መፈጠርን ተከትሎ፥ ኋላም በ20ኛው መ/ክ/ዘ የጎትመት መሣሪያ ወደ ሀገር ውስጥ መግባቱን ተከትሎ መንፈሳዊ መጻሕፍትንና በዘመናዊ መልክ የተዘጋጁ መጽሔቶችና ጋዜጦችን በማሠራጨት በሀገራችን የብዙኃን መገናኛ ታሪክ የራሷን አሻራ አሳርፋለች።

I. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብዙኃን መገናኛ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለልጆቿ ብዙኃን መገናኛ ያቋቋመችው ዶግማዋን፥ ትምህርቷን፥ ትውፊቷን፥ ታሪካን በሚዲያ ለማስተማር ነው።

ጋዜጣና መጽሔት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘመናዊ የሚዲያ ታሪክ የሚጀምረው በ1930ዎቹ ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የጎትመት ሚዲያ በመጠቀም በርካታ የጎትመት ውጤቶች ተዘጋጅተው ተሠራጭተዋል። በእነዚህ ዘመናት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ተቋማት የጎትመት ውጤቶች (ጋዜጣና መጽሔት) ታትመው ይሠራጩ ነበር። ከእነዚህም ውስጥ በ1938 ዓ.ም መታተም የጀመረው "ተክለ ሃይማኖት" ጋዜጣ በቀዳሚነት ይጠቀሳል። በ1940 ዓ.ም መታተም የጀመረው "ዜና ቤተ ክርስቲያን ዘኢትዮጵያ" ጋዜጣ ቤተ ክርስቲያናችን ዘመናዊ ሚዲያን በመጠቀም ያሠራጨችው ተጠቃሽ የጎትመት ውጤት ነው። ከተክለ ሃይማኖትና ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጦች ተጨማሪ በ1956 ዓ.ም መታተም የጀመረው "ድምፀ ተዋሕዶ" እና "ድምፀ ምእመናን" ጋዜጣ፥ የካህናት ጉዳዮችን ብቻ የሚስተናግደው "ግብረ ልዑካን"፥ እንዲሁም ‹‹ቃለ ዐዋዲ›› ጋዜጣ በታሪክ በቤተ ክርስቲያናችን ታትመው ከሚሠራጩ የጎትመት ውጤቶች መካከል ይጠቀሳሉ።

በመጽሔትም "ትንሣኤ" እና "ማዕዶት"›› መጽሔቶች በታሪክ የሚጠቀሱ የጎትመት ውጤቶች ናቸው። ከዚያም በኋላ በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ልዩ ልዩ ክፍሎችና እንደ ማኅበረ ቅዱሳንና ጽርሐ ጽዮን የሐዋርያት አንድነት የኑሮ ማኅበር ያሉ የቤተ ክርስቲያናችን ተቋማት ልዩ ልዩ የጎትመት ውጤቶችን ሲያሠራጩ ቆይተዋል። ይህም የሚያሳየው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጎትመት ሚዲያው ዘርፍ የተደራጀ አሠራር እንደነበራት ነው።

ሬዲዮ

ጥንታዊት፥ ሐዋርያዊትና ታሪካዊት የሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከ1966 ዓ.ም በፊት በሀገሪቱ ብሔራዊ ሬዲዮና ቴሌቪዥን፥ እንዲሁም በሉተራን ፌዴሬሽን የብሥራተ ወንጌል፥

የምሥራች ድምፅ ሬዲዮ የሰላም፥ የእምነትና የማኅበራዊ ተልእኮ ትምህርቶቿን፥ ዓመታዊ በዓላቷንና ሥርዐተ አምልኮዋን የማስተላለፍ ዕድል ነበራት። ከብሥራተ ወንጌል ጣቢያ በተገኘው የአየር ሰዓት በሐዋርያዊው ድርጅት በተሰባሰቡ ዕውቅ ምሁራን ትምህርተ ወንጌል ይሰጥ ነበር።

ዩሳተካይት ቴኤቪ ሽፕ

በቤተ ክርስቲያናችን ብዙኃን መገናኛ ቴክኖሎጂን ከጎትመት ወደ ብሮድካስት ቴክኖሎጂ ሲያድግ፥ ቤተ ክርስቲያናችን በነበረው የብዙኃን መገናኛ አዋጅ ለሃይማኖት ተቋማት በሀገር ውስጥ የብሮድካስት ሥርጭት ስለማይፈቅድ፥ በነበረው የሕግ ክፍተት ከሀገር ውጪ የሚሠራጭ የ24 ሰዓት የቴሌቪዥን ሥርጭት በመጀመር መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቷን ማሠራጨት ችላለች።

ቅዱስ ሲኖዶስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የመገናኛ ብዙኃን አገልግሎት ድርጅት እንዲቋቋም ጥናት እንዲካሄድ የወሰነው በጥቅምት ወር 2006 ዓ.ም ነው። በዚህም ውሳኔ መሠረት ተገቢው ጥናት ተከናውኖ፥ አስፈላጊው መሣሪያና የሰው ኃይል ተደራጅቶ፥ በጥቅምት ወር 2008 ዓ.ም ለሥራው የሚያስፈልገው በጀት በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ተወስኖ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የመገናኛ ብዙኃን አገልግሎት ድርጅት በሳተላይት ቴሌቪዥን በመላው ዓለም የቤተ ክርስቲያኗን መንፈሳዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ማስተላለፍ ችሏል።

በሂደትም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የመገናኛ ብዙኃን አገልግሎት ሥርጭት ድርጅት የቅድስት ቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነት ትውፊት፥ ቀኖናና መዋቅራዊ አሠራር መሠረት በማድረግ ብቃትና ጥራት ያላቸውን መርሐ ግብራት በብዙኃን መገናኛ ማሠራጫዎች በመደበኛነት ለማቅረብ በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ የተሰጠው እውቅና እንደተጠበቀ ሆኖ፥ በተሻሻለው የብዙኃን መገናኛ አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀጽ 6(1)፥(5) እና 40(3)(ለ) መሠረት፥ በኢፌዴሪ የመገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን እውቅና አግኝቷል።

ድርጅቱ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፥ ሥርዐተ አምልኮ፥ ታሪክና ቅርስ፥ መንፈሳዊ፥ ማኅበራዊና ልማታዊ አገልግሎትን፥ በጎ አድራጎትን ለቤተ ክርስቲያኗ እምነት ተከታዮችና ለሌሎችም በመላው ዓለም ለሚገኙ ምእመናን የቤተ ክርስቲያናችንን ሕግጋትና የሀገራችንን ሕገ መንግሥት፥ ሌሎች አዋጆችና ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በማቅረብ ላይ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአፋን ኦሮሞ ቴሌቪዥን ድርጅት (EOTC AFAAN OROMOO) እና የማኅበረ ቅዱሳን ቴሌቪዥን በብሮዳክስት ዘርፍ የቤተ ክርስቲያናችን የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ሆነው በመሥራት ላይ ይገኛሉ።

ማኅበራዊ ትስስር ሚድያ በኢትዮጵያ

(Social Media in Ethiopia)

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር እስከ ጥር 2021 የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር 116.4 ሚሊዮን ደርሷል የሚሉ መረጃዎች አሉ። ከጥር 2020 እስከ ጥር 2021 ባለው ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በ2.9 ሚሊዮን ወይም የ2.5% ጭማሪ አሳይቷል። 21.9% የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በከተማ ማእከላት የሚኖር ሲሆን፤ 78.1% የሚሆነው ደግሞ በገጠር ይኖራል። እስከ ጥር 2021 በኢትዮጵያ 23.96 ሚሊዮን ሕዝብ ኢንተርኔት ይጠቀማል፤ ከ2020 እስከ 2021 ባለው ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ የበይነ መረብ ተጠቃሚዎች ቁጥር በ2.8 ሚሊዮን ወይም የ13% እድገት አሳይቷል።

እስከ ጥር 2021 በኢትዮጵያ የኢንተርኔት አገልግሎት ተደራሽነት 20.6% ሲሆን፤ 6.70 ሚሊዮን የሚሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ የማኅበራዊ ትስስር ሚዲያ ተጠቃሚ ነው። በኢትዮጵያ የማኅበራዊ ትስስር ሚዲያ ተጠቃሚዎች ቁጥር ከ2020 እስከ 2021 ባለው ጊዜ ውስጥ የ500 ሺህ ወይም የ8.1% ለውጥ አሳይቷል። በኢትዮጵያ እስከ ጥር 2021 ከጠቅላላው ሕዝብ 5.8% የሚሆነው ማኅበራዊ ትስስር ሚድያ ተጠቃሚ ነው። እ.ኤ.አ. እስከ ጥር 2021 በኢትዮጵያ 44.86 ሚሊዮን የሞባይል ግንኙነቶች /Connection/ ሲኖሩ፥ የተንቀሳቃሽ ስልክ ግንኙነቶች /Connection/ ቁጥር ከጥር 2020 እስከ ጥር 2021 ባለው ጊዜ ውስጥ የ710 ሺህ ወይም የ1.6% ጭማሪ አሳይቷል። በጥር 2021 በኢትዮጵያ የሞባይል ግንኙነቶች ብዛት ከጠቅላላው ሕዝብ 38.5% ይሸፍናል (Digital 2021)።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዚሁ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ናት። በዚህ ዙሪያ የቤተ ክርስቲያኗ ልጆች ምን ያህል ተጠቃሚዎች ናቸው የሚል ዝርዝር ጥናት ባይኖርም፥ እንደ አጠቃላይ ግን ይህ መረጃ ቤተ ክርስቲያኗንም ያካትታል። በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሚዲያ በማኅበራዊ ትስስር ገጽ ያለውን ሂደት ጥናቶች ያሳያሉ።

2. ዲጂታል ሚዲያ

ዲጂታል ሚዲያ ማለት በዲጂታል ኮድ ቅርጸት የሚገኙና በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ወይም በኮምፒውተር ኔትወርኮች አማካኝነት ሊፈጠሩ፥ ሊስተካከሉ፥ ሊሠራጩና ሊጠበቁ የሚችሉ ይዘቶች

ስብስብ ነው።

- ድረ-ገጾች (Websites)
- ማኅበራዊ ሚዲያ (Social Media) – Facebook, TikTok, Instagram, X
- የኦንላይን ጋዜጦችና መጽሔቶች
- የቪዲዮ ሚዲያ – YouTube ወዘተ
- ፖድካስት (Podcast)
- ኢሜይል (Email)
- ኢ-መጽሐፍ (E-book)
- ዲጂታል ሬዲዮ
- የኦንላይን ቴሌቪዥን/Streaming
- ዲጂታል ምስሎችና ግራፊክስ
- የመልእክት መተግበሪያዎች – Telegram, WhatsApp, Messenger

በአጭሩ ጽሑፍ፥ ምስል፥ ድምፅና ቪዲዮ በዲጂታል መልክ የሚተላለፉበት ማንኛውም መድረክ ዲጂታል ሚዲያ ሊባል ይችላል። በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሚዲያ ዋንኛው የግንኙነት መሣሪያ ነው። ቴክኖሎጂው በየቀኑ በሚለዋወጥበት በዚህ የዲጂታል ዘመን ሚዲያ ለኢኮኖሚና ለርዕዮተ ዓለማዊ መሣሪያነት ከመዋል አልፎ በመንፈሳዊው ዘርፍም ከፍተኛ እመርታ እያሳየ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት በመላው ዓለም የሚገኙ ክርስቲያን የሚዲያ ተጠቃሚዎች ቁጥር (Users of radio/TV/Internet) እኤአ 2021 2 ቢሊዮን 340 ሚሊዮን ሲሆን፤ ይህ ቁጥር በ2025 2 ቢሊዮን 460 ሚሊዮን፥ በ2050 ደግሞ 2 ቢሊዮን 930 ሚሊዮን እንደሚደርስ የስታስቲክስ ጥናቶች ያሳያሉ (Status of Global Christianity, 2021, in the Context of 1900-2050)::

የዲጂታል ሚዲያ የማኅበራዊ ሚዲያ ፕላትፎርሞችን በመጠቀም በቴሌቪዥን ከሚሠራጩት መርሐ ግብራት በተጨማሪ በተለየ በራሱ የአሠራር መንገድ (Algorism) ቴክኒክና መገለጫዎች ማለትም በተለያዩ ኤሌክትሮኒክስ ቁሳቁስ፥ በአጋዥ ሶፍትዌሮች፥ በዋብሳይት በቪዲዮዎች በቀጥታ ሥርጭት ማኅበራዊ ግንኙነትን በሚያሳልጡ የማኅበራዊ ሚዲያ ፕላትፎርሞች የሚሠራጭ ዘመን አመጣሽ የሚዲያ ቅርጽ ሆኖ ለሚሊየኖች ተደራሽ መሆን ችሏል። ይህም ከይዘት ማስተላለፊያነት አልፎ የታላላቅ ተቋማት የሀብት ማግኛ መንገድ ከመሆኑ በላይ፥ ለብዙ ወጣቶች የዕለት እንጀራ በመሆን በግለሰብ፥ በማኅበረሰብ፥ በሀገርና በዓለም መድረክ ዋነኛ የመከወኛ መንገድ ሆኗል። በአሜሪካ ገበያ ብቻ 85.6 ቢሊዮን ዶላር የሚንቀሳቀስበት ሲሆን፤ በ2025 117.4 ቢሊዮን ዶላር ይደርሳል ተብሎ የተተነበየለት ግዙፍ ኢንዱስትሪ ነው።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያ በዲጂታል ሚዲያ መረጃና ትምህርት የሚያስተላለፉ ድረ ገጾች በርካታ ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ፦

1. የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽሕፈት ቤት / EOTC His Holiness Secretariat Office https://www.facebook.com/EotcpatriarchateOffice
2. የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መገናኛ ብዙኃን አገልግሎት ሥርጭት ድርጅት / EOTC Broadcasting Service Agency/ https://www.facebook.com/share/1DAeKLqeFT/
3. የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ሕዝብ ግንኙነት መምሪያ/ Department of Public Relation,EOTC https://www.facebook.com/profile.php?id=100068379977850
4. ማኅበረ ቅዱሳን ብሮድካስት አገልግሎት /Mahibere Kidusan Broadcast Service - https://www.facebook.com/eotcmkidusan
5. የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ https://www.facebook.com/profile.php?id=61580232751988
6. EOTC Afaan Oromoo https://www.facebook.com/profile.php?id=100092399080581
7. የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሚዲያ አገልግሎት/Addis Ababa Diocese Media Service https://www.facebook.com/addisababadiocese
8. ሐመረ ተዋሕዶ ሚዲያ /Hamere Tewahedo Media https://www.facebook.com/profile.php?id=100085509522860
9. አቡቀለምሲስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሚዲያ https://www.facebook.com/abukelemsisdigital
10. ሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ሚዲያ - North Wollo Diocese Media https://www.facebook.com/EOTCNWD
11. በምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት የሕዝብ ግንኙነት- East Shoa Diocese Public Relation https://www.facebook.com/profile.php?id=100075733759858
12. የድሬዳዋ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት የፌስቡክ

ገጽ https://www.facebook.com/profile.php?id=61563382452089

13. ዜና ጎርጎርዮስ ሚዲያ https://www.facebook.com/profile.php?id=61568379839705
14. የሲዳማ ሀገረ ስብከት ሕዝብ ግንኙነት https://www.facebook.com/profile.php?id=100079788595416
15. የደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት የሚዲያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት https://www.facebook.com/profile.php?id=61569477210755
16. የምዕራብ አርሲ ሀገረ ስብከት ሕዝብ ግንኙነት Qunnamtii Ummataa Kutaa Lallaba Arsii Lixaa https://www.facebook.com/eotcwestarsiPR
17. EOTC Germany Archdiocese ፡ የጀርመንና አካባቢው ሀገረ ስብከት https://www.facebook.com/eotc.germany.archdiocese
18. የጅማ ሀገረ ስብከት መገናኛ ብዙኃን አገልግሎት Miidiyaa Biyya lallaba Jimmaa https://www.facebook.com/profile.php?id=61576704284764
19. የዳውሮ ሀገረ ስብከት መገናኛ ብዙኃን ገጽ EOTC Dawro Diocese Broadcast Services https://www.facebook.com/eotcdawrohageresibket
20. የአርሲ ሀገረ ስብከት ሚድያ Miidiyaa Biyya Lallaba Arsii https://www.facebook.com/MiidiyaaBiyyaLallabaArsii
21. የሶማሌ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት/Somali Diocese Secretary/ https://www.facebook.com/profile.php?id=61564835578695
22. የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት-Kutaa Lallabaa Go/sh/ki/lixaa-South West Shoa Diocese https://www.facebook.com/profile.php?id=100063905612972
23. እጩጌ የወላይታ ሀገረ ስብከት ሚዲያ https://www.facebook.com/profile.php?id=61576040274494
24. ነቅዐ ጽድቅ የጋሞና አካባቢው ሀገረ ስብከት ሚዲያ https://www.facebook.com/share/1Dka8ybMZN/
25. ብሕንሳ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሀዲያና ስልጤ ሀገረ ስብከት ሚዲያ https://www.facebook.com/share/1BZ3eFnN7W/

ተጠቃሾች ናቸው።

የዲጂታል ዘመን መምጣት የጽሑፍ የመረጃ ማስተላለፊያ ሂደት አዲስ ገጽታ እንዲይዝ አድርጎታል። ዛሬ መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን የተቀረጸ ስብከት፥ የቪዲዮ ትምህርት፥ የቀጥታ ሥርጭት፥ ፖድካስት፥ ድረ-ገጽ፥ ፌስቡክ፥ ቴሌግራም፥ ዩቲዩብና ሌሎች የዲጂታል መድረኮች የመንፈሳዊ ትምህርት ማስተላለፊያ መሣሪያዎች ሆነዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በድረ ገጽ (በዌብ ሳይት) የቤተ ክርስቲያናችንን መረጃዎች በማሠራጨት በዲጂታል ሚዲያ ዘርፍ ስትሠራ ቆይታለች። ከእነዚህም ውስጥ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ድረ ገጽ፥ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ድረ ገጽ፥ የማኅበረ ቅዱሳን ድረ ገጽ እንዲሁም የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ድረ ገጽ ተጠቃሽ ናቸው።

የኢኦተቤ ቴቪ (EOTC TV) ዲጂታል ሚዲያ

ከዲጂታል ሚዲያዎች መካከል ማኅበራዊ ሚዲያ በአነስተኛ በጀትና የሰው ኃይል በቀላል ቴክኖሎጂ የኢንተርኔት መረብን በመጠቀም እየተሠራጨ በማኅበረሰብ ውስጥ መረጃን፥ እውቀትን፥ እሴቶችንና አመለካከቶችን ከአንድ ሰው ወይም ተቋም ወደ ብዙ ሰዎች ለማስተላለፍ ወሳኝ ሚና አለው። በተለይ በዲጂታል ዘመን ይህ ሚና ከሬዲዮና ቴሌቪዥን ባህላዊ ሥርጭት በመውጣት ወደ ድረ-ገጽ፥ ዩቲዩብ፥ ፌስቡክ፥ ቴሌግራም፥ ቲክቶክ፥ ኢንስታግራምና ሌሎች የዲጂታል ሚዲያ ማስተላለፊያ መድረኮች ተስፋፍተዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብዙኃን መገናኛ ድርጅት የኢኦተቤ ቴቪ (EOTC TV) በመዋቅሩ የዲጂታል ሚዲያ በዋና ክፍል በማዋቀርና ባለሙያዎችን በመመደብ በዘርፉ የቤተ ክርስቲያንን ተልዕኮ በመደገፍ በመሥራት ላይ ይገኛል። ይህ የዲጂታል ሚዲያ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልዩ ትርጉም አለው። ቤተ ክርስቲያኗ ለዘመናት የቅዱሳት መጻሕፍት፥ የአበው ትምህርት፥ የቅዳሴ፥ የዝማሬ፥ የቅኔና የመንፈሳዊ ትውፊት ጠባቂ ሆና ቆይታለች። በዲጂታል ዘመን ግን ይህንን ሀብት በዘመናዊ መሣሪያዎች ማስተላለፍ አዲስ የሚዲያ ስትራቴጂ ይጠይቃል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብዙኃን መገናኛ ድርጅት የዲጂታል ሚዲያ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ብዙኃን መገናኛ ድርጅት (EOTC TV) በመዋቅሩ የዲጂታል ሚዲያ በዋና ክፍል በማዋቀር ባለሙያዎችን በመመደብ በዘርፉ

የቤተ ክርስቲያንን ተልዕኮ በመደገፍ በመሥራት ላይ ይገኛል። የዲጂታል ሚዲያ የመጪው ዘመን ተቀዳሚ የሚዲያ መሣሪያ መሆኑን በመረዳት ለዘርፉ ትኩረት በመስጠት የሚያከናውነው ሥራ በቤተ ክርስቲያኗ የሚዲያ እንቅስቃሴ አዲስ መልክ ነው።

በባህላዊ የቴሌቪዥን ተመልካች የተወሰነ ሰዓት ላይ በሚሠራጭ ፕሮግራም ላይ ይመሠረታል። በዲጂታል ሚዲያ ማለትም በዩቲዩብ ወይም በሌሎች ፕላትፎርሞች የሚተላለፈው ግን ተመልካች ይዘቱን በፈለገው ጊዜ ማግኘት፥ ማጋራትና እንደገና ማየት ስለሚያስችለው የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለሆነው የቤተ ክርስቲያኗ ተከታይ ተቀዳሚ ምርጫ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብዙኃን መገናኛ ድርጅት ትምህርታዊ፥ ማኅበራዊና መረጃ ሰጪ መርሐ ግብራትን ከዩቲዩብ በተጨማሪም ፌስቡክ፥ ቴሌግራም፥ ቲክቶክ፥ ኢንስታግራምና ሌሎች የዲጂታል ሚዲያ ገጾች እንደየ ቴክኖሎጂ ባሕሪው በማስተላለፍ ላይ ነው። ይህም ለጣቢያው ሁለት ዓይነት ጥቅም ይፈጥራል፤ አንደኛ፥ በቴሌቪዥን የተላለፈውን ይዘት በድጋሚ ለማግኘት ያስችላል፤ ሁለተኛ፥ ከቴሌቪዥን ሥርጭት በላይ የሆነ አዲስ የይዘት ማምረቻና ማሠራጫ መድረክ ሆኖ በማገልገል ላይ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብዙኃን መገናኛ ድርጅት (EOTC TV) ዋና ተልእኮ በሚዲያ መሣሪያነት የቤተ ክርስቲያኗን ድምፅ ማሰማትና መንፈሳዊ ትምህርቷን ማስተላለፍ ነው። እኤአ በ2024 “Media and Religion in Ethiopia” ሪፖርት EOTC TV በመንፈሳዊ ጉዳዮች ብቻ ያልተገደበ ይዘት እንደሚያቀርብ ይገልጻል። ሪፖርቱ የሕፃናትና የወጣቶች ፕሮግራሞች፥ ማኅበራዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች፥ እንዲሁም ዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች በEOTC TV ይዘት ውስጥ እንደሚገኙ ጠቁማል። ማኅበራዊ ሚዲያው የኢኦተቤ ቴቪ (EOTC TV) እንደ ወንጌል ማሠራጫ ብቻ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያኗን ከማኅበረሰቡ ጋር የሚያገናኝ የሚዲያ አውታር ሆኖ እየሠራበት ነው።

የኢኦተቤ ቴቪ (EOTC TV) ዲጂታል ሚዲያ ተደራሽነት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የመገናኛ ብዙኃን አገልግሎት ሥርጭት ድርጅት በአሁኑ ወቅት በመላው ዓለም በሳተላይት ቴሌቪዥን፥ በዲኤስ ቲቪ፥ በምሥራቅ አፍሪካ በኢትዮ ሳት፥ በተጨማሪም በመላው ዓለም በሁሉም የዲጂታል ሚዲያ ፕላትፎርሞች መርሐ ግብራቱን በማሠራጨት ላይ ይገኛል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብዙኃን መገናኛ ድርጅት (EOTC TV) Internews የተሰኘ ዓለም አቀፍ ድርጅት ባስጠናው “Ethiopian Digital Media Information Ecosystem Assessment” በተሰኘ ጥናት፥ በሀገራችን ከሚገኙ ተጽዕኖ ፈጣሪ 10 የዲጂታል ፕላትፎርሞች አንዱ መሆኑን መስክሯል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብዙኃን መገናኛ ድርጅት (EOTC TV) በዲጂታል ሚዲያ በየፕላትፎርሙ በሚደረግ የሊንክ ግንኙነት በየወሩ እስከ 10 ሚሊየን ድግግሞሽ እያታ ያገኛል። የተቋሙ የፌስቡክ ገጽ በ2018 ዓ.ም (ከሐምሌ 1 ቀን 2017 - ሰኔ 30 ቀን 2018 ዓ.ም) 112,948,256 ሚሊዮን ጊዜ ገጹ ተጎብኝቷል።

ዋናው የEOTC TV YOU TUBE ገጽ የዕይታ መጠን በ2018 ዓ.ም 3.9 ሚሊዮን (ሦስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺህ አጠቃላይ የዕይታ ጊዜ በሰዓት 613.6 K (ስድስት መቶ አሥራ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ) ሰዓት ታይቷል። የዩቲዩብ ገጹ ከአምስት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺህ በላይ ሰብስክራይበሮች (557K Subscribers) የሚከታተሉት ሲሆን፤ በውስጡ 7600 (7.6K) የምስል ወድምዕ ክምችቶችን ይዟል። በዓመቱ አዳዲስ ደንበኞች (ሰብስክራይበሮች) የሚቀላቀሉት ሲሆን፤ በ2018 ዓ.ም ሰብስክራይብ ያደረጉ ተከታታዮች ቁጥር 29,900 ይደርሳል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብዙኃን መገናኛ ድርጅት (EOTC TV) በዲጂታል ሚዲያ ከአማርኛ በተጨማሪ የኦሮምኛና ትግርኛ እንዲሁም እንግሊዝኛ ቋንቋዎችን በመጠቀም የቤተ ክርስቲያኗን ይዘት ለተለያዩ ማኅበረሰቦች በማድረስ ላይ ነው። ይህ የቋንቋ ብዝኃነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብዙኃን መገናኛ ድርጅት (EOTC TV) ሁለት ዓይነት ጠቀሜታ አለው። አንደኛ፥ በኢትዮጵያ ያሉ የተለያዩ ማኅበረሰቦችን ለመድረስ ያግዛል። ሁለተኛ፥ በውጭ ሀገር የሚኖሩ የተዋሕዶ ምእመናንን ከቤተ ክርስቲያኗ ትምህርትና መረጃ ጋር ያገናኛል።

የዲጂታል ሚዲያ ዕድሎች ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

ቴሌቪዥን በተወሰነ የሥርጭት ክልል የሚገደብ ሲሆን፤ ዲጂታል ሚዲያ ግን በኢንተርኔት በኩል ዓለም አቀፍ ተደራሽነት ይፈጥራል። ቴክኖሎጂው ለአጠቃቀም ቀላልና በአነስተኛ የሰው ኃይል መሥራት መቻሉ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከመንበረ ፓትርያርክ እስከ አህጉረ ስብከት ብሎም አድባራትና ገዳማት ትምህርተ ወንጌልንና መረጃዎችን በመላው ዓለም በማድረስ የቤተ ክርስቲያናችንን ዋና ዋና ኩነቶች ዲጂታል ሚዲያን በመጠቀም ማስተላለፍ

ተችሏል።

የቀጥታ ሥርጭትን ጨምሮ ሌሎች መርሐ ግብራት በዲጂታል ሚዲያ ሲተላለፉ በቀጥታ የተመልካቾችን አስተያየት ለማግኘትና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ግብረ መልስ ለመስጠት አስቻይ ሁኔታ ፈጥሯል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብዙኃን መገናኛ ድርጅት (EOTC TV) ጨምሮ ሌሎች መንፈሳዊ ሚዲያዎች የቅዳሴ፥ የበዓላት፥ የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔዎች፥ የሃይማኖታዊ ጉባኤዎችና ሌሎች ዋና ዋና መርሐ ግብሮችን በቀጥታ ማሠራጨት በሩቅ የሚገኙ ምእመናንን ተሳትፎ አሳድገዋል። በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ደረጃ ምእመናንን በማስተባበር ለአብያተ ክርስቲያናት፥ ገዳማትና የአብነት ትምህርት ቤቶች ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች የገቢ ማሰባሰቢያ መንገድ በመሆን ከፍተኛ አዎንታዊ ውጤት ታይቶበታል።

3. ሰው ሠራሽ አስተውሎት (AI) እና ዲጂታል ሚዲያ

የዲጂታል ሚዲያ ቴክኖሎጂና ሰው ሠራሽ አስተውሎት (AI) በዘመናችን ጥብቅ ቁርኝት አላቸው። ዘርፉ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያለው ጥቅምና ጉዳት በጥልቅት በባለሙያዎች ሊፈተሽና በፖሊሲ ሊታቀፍ ይገባዋል። ሰው ሠራሽ አስተውሎት (AI) በዘመናችን የዲጂታል ቴክኖሎጂ ፈጣን ዕድገት የሰው ልጅ የሚሠራበትን፥ የሚማርበትን፥ የሚገናኝበትንና መረጃ የሚያገኝበትን መንገድ በእጅጉ ቀይሮታል። በተለይም ሰው ሠራሽ አስተውሎት (Artificial Intelligence–AI) በጽሑፍ፥ በምስል፥ በድምፅ፥ በቪዲዮ፥ በትርጉምና በመረጃ ትንተና ዘርፎች የሚዲያ ሥራን እየቀየረ ይገኛል።

ይህ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ትልቅ ዕድልና በተመሳሳይ ጊዜ ትልቅ ፈተና ይዞ መጥቷል። የቤተ ክርስቲያን የወንጌል ትምህርት፥ ስብከት፥ መዝሙር፥ የቅዱሳት መጻሕፍት ይዘትና የመንፈሳዊ መልእክት ለሰፊ ሕዝብ በፍጥነት እንዲደርስ AI ሊያግዝ ይችላል። ነገር ግን የሐሰት መረጃ፥ የዲጂታል ማጭበርበር (deepfake)፥ የግላዊነት ጥሰትና የቤተ ክርስቲያንን ትክክለኛ አስተምህሮ የሚያዛባ ይዘት መፈጠር የሚችልበት አደጋም አለ።

4. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንዲጂታል ሚዲያዎች የተጋፈጉ ፈተናዎች

በየኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዲጂታል ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ያለመዘመን፥ ማእከላዊ የዲጂታል ማኅደር መሠረተ ልማት አለመሟላት አገልግሎቱ በተፈለገው መጠንና ጥራት እንዳይሰፋፋ አድርጎታል። ደካማ የሳይበር ደኅንነት፥ የባለሙያዎች የሙያና የእውቀት ክፍተት የኢኦተቤ ቴቪ (EOTC TV) ጨምሮ በቤተ ክርስቲያናችን የዲጂታል ሚዲያ አውታሮች ፈተናዎች ናቸው።

በሀገራችን የዲጂታል ሚዲያ ችግር ውስጥ ጎልቶ የሚታየው የሐሰተኛ መረጃ ሥርጭት ነው። ይህም እንደ ሀገር ኢትዮጵያን፥ እንደ ተቋም ቤተ ክርስቲያንን እየፈተነ ይገኛል። ይልቁን ይኸው ችግር በሰው ሠራሽ አስተውሎት (Artificial Intelligence–AI) ተደግፎና በልጽጎ ዲፕፌክ (Deepfake) እና የሐሰት ቪዲዮ AI የሰውን ፊት፥ ድምፅና ንግግር በመጠቀም ሰውየው ያልተናገረውን እንደተናገረ ወይም ያላደረገውን እንዳደረገ ማሳየት፥ በሐሰት ትርክት በቤተ ክርስቲያኗ እምነትና ሥርዓት፥ በቤተ ክርስቲያኗ አባቶች በዲጂታል ሚዲያ የሚተላለፉ የሐሰት መረጃዎችን ተአማኒ በማድረግ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ይገኛል።

ከዚህም በተጨማሪ የሐሰተኛ መረጃና የክሕደት ትምህርቶች ሥርጭት በማኅበራዊ ሚዲያ የቁጥጥር ማነስ ምክንያት የቤተ ክርስቲያኗን ሥርዓትና ዶግማ የማይከተሉ ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያኗ ስም በስፋት መሠራጨት ሌላው ችግር ነው።

የጽንፈኝነትና የቤተ ክርስቲያኗን የዲጂታል ሚዲያ አውታሮች ለፖለቲካዊ ትግል ለማዋል የሚደረጉ ሙከራዎች የሃይማኖት፥ የብሔርና የፖለቲካ ውጥረቶችን የሚያባብሱ መረጃዎች በቤተ ክርስቲያኗ የዲጂታል ሚዲያዎች አስተያየት መስጫ ሳጥኖች በኩልና በቤተ ክርስቲያናችን ስም በሚከፈቱ ሐሰተኛ ገጾች አማካኝነት መሠራጨታቸው በዘርፉ ያጋጠመ ሌላው ተግዳሮት ነው። የምእመናን ትኩረት መበታተን፥ የአእምሯዊ ንብረት (Copyright) መጣስ፥ የቤተ ክርስቲያን መዝሙራት፥ ስብከቶችና መጻሕፍት ያለፈቃድ ለንግድ ዓላማ መዋላቸው ሌላው የዲጂታል ሚዲያው ፈተና ነው።

5. ስልታዊ የመፍትሔ አቅጣጫዎች

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብዙኃን መገናኛ ድርጅት (EOTC TV) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መምሪያ በማቋቋም ቀደምት የጽሑፍ ሀብቶችን ወደ ዲጂታል የማሸጋገር ሥራ በይፋ ጀምራለች። ይህ የሚያበረታታ ተግባር ቀደም ሲል በነበሩ ቅዱሳን ፓትርያርኮችና የቤተ ክርስቲያኗ ወሳኝ ኩነቶች የተቀረጹ የአናሎግ ቪዲዮችንም ዲጂታል ማድረግን ሊያካትት ይገባል። ቤተ ክርስቲያኗ በዓመታት ውስጥ የተጠቀመችባቸውን የቪዲዮና የድምፅ ሥራዎች በሥርዐት ማእከላዊ የዲጂታል ማኅደር ማደራጀት ለሚቀጥለው ትውልድ የሃይማኖት፥ የታሪክና የሚዲያ

ምርምር ትልቅ ምንጭ ይሆናል።

ይህንን ትልቅ ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብዙኃን መገናኛ ድርጅት (EOTC TV) ጨምሮ ለሌሎችም በዘርፉ ለሚገኙ ባለድርሻዎች በቤተ ክርቲያናችን በኩል የሚዲያና የኮሙኒኬሽን ፖሊሲ ማውጣት ያስፈልጋል። ይህም የቤተ ክርስቲያኗ የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀምን፥ የዲጂታል ሚዲያ ባለሙያዎችንና የይዘት ፈጣሪዎችን ብሎም ተጠቃሚዎችን የሚያስተዳድር ግልጽ መመሪያና ፖሊሲ ማዘጋጀት አለባት።

በዘርፉ ውጤታማ ለመሆን ስለ ዲጂታል ሚዲያ አጠቃቀምና ስለ ዘመናዊ የኮሙኒኬሽን ስልቶች የሙያ ብቃት ማሻሻያ የሥልጠና ፕሮግራሞች ለሚዲያ ባለሙያችና አገልጋዮችና ለአበው ካህናት ሥልጠና መስጠት ያስፈልጋል። ከዚህም በተጨማሪ ኦፊሴላዊ የዲጂታል መድረኮችን ማጠናከር፥ ምእመናን ትክክለኛውንና የተረጋገጠውን ትምህርት የሚያገኙባቸውን የቤተ ክርስቲያኗን ኦፊሴላዊ ድረ-ገጾችና የማኅበራዊ ሚዲያ ገጾች ማደራጀት፥ የዲጂታል መጻሕፍትና ቤተ-መጻሕፍት ልማት፥ ጥንታዊ የብራና መጻሕፍትን ዲጂታላይዝ በማድረግና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለጥናትና ምርምር ክፍት ማድረግ ከቤተ ክርስቲያናችን የሚጠበቁ ተግባራት ናቸው።

ማጠቃለያ

ዲጂታል ቴክኖሎጂና ሚዲያ በራሳቸው ጥሩ ወይም መጥፎ አይደሉም፤ ውጤታቸው የሚወሰነው በምንጠቀምበት መንገድ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዲጂታል ዘመንን እድሎች በአግባቡ በመጠቀምና ፈተናዎቹን በስትራቴጂካዊ መንገድ በመከላከል፥ ለስብከተ ወንጌል ሥርጭት፥ ለታሪክ ጥበቃና ለምእመናን አንድነት ልትጠቀምበት ይገባል። ዲጂታል ቴክኖሎጂ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ዕድል የሚፈጥር የዘመኑ የመገናኛ መሣሪያ ነው። ቤተ ክርስቲያን ይህንን ቴክኖሎጂ በትክክል ካደራጀችው የቤተ ክርስቲያኗን የስብከተ ወንጌል ሥራ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም ዙሪያ ማስፋፋት ያስችላል። የዲጂታል ሚዲያ ስኬት በቴክኖሎጂ መሣሪያ ብቻ አይመዘንም። የይዘት ጥራት፥ የትምህርተ ሃይማኖት ትክክለኛነት፥ የጋዜጠኝነት ሥነ-ምግባር፥ የሰው ኃይል ብቃት፥ የተመልካች ግብረ መልስና የዲጂታል ስትራቴጂ ወሳኝ ናቸው።

ስለዚህ በቀጣይ "የቤተ ክርስቲያኗ የተቀናጀ ዲጂታል ሚዲያ ማእከል" አቅዶ ማዋቀር ይገባል። ይህም የቤተ ክርስቲያኗን ትምህርት በታማኝነት እያስጠበቀ ከአዲሱ ትውልድ የመገናኛ ልማድ ጋር የሚስማማ የሚዲያ ሥርዓት ለመገንባት ያስችላል። ከዚሁ ጎን ለጎን በየዕለቱ ለሚከሰቱ ችግሮች ምክንያት የሆነውን የሐሰት መረጃ መከላከያ ሥርዐት በተለይ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ማቋቋምና ወደ ሥራ ማስገባት ይገባል። በመጨረሻ፥ ቴክኖሎጂ ለመንፈሳዊ ተልእኮ እንጂ ተልእኮው ለቴክኖሎጂ እንዳይሆን የዲጂታል ሚዲያ ፖሊሲ ተሰናድቶ በዚህ መርህ ሊመራ ይገባል።

ዋቢ ምንጮች

- (Safko, Lon. The Social Media Bible: Tactics, Tools, and Strategies for Business Success. John Wiley & Sons, 2010)
- Fantahun Muche Assefa (2024). SURVEY OF ETHIOPIAN ORTHODOX TEWAHEDO CHURCH (EOTC) BROADCAST SERVICES: HISTORICAL BACKGROUND, DEVELOPMENT AND FUTURE PERSPECTIVES
- Moges, M. A., & Skjerdal, T. (2024). Media and Religion in Ethiopia: A Research Report. Fojo Media Institute, Linnaeus University.
- Tekle, K. C. (2026). The effect of digital transformation on church performance: A mediation moderation analysis.
- Gessese, N., Gebru, A., & Nigatu, B. (2021). Mediatization of development in sub-Saharan Africa: Insights from Ethiopian Orthodox Tewahedo Church (EOTC), Mahibere Kidusan magazine, Ethiopia.
- Safko, Lon. The Social Media Bible: Tactics, Tools, and Strategies for Business Success. John Wiley & Sons, 2010
- https://internews.org/resource/ethiopian-digital-media-informat
- EOTC TV YouTube፥ Facebook፥ Telegram፥ TikTok እና Instagram ዲጂታል ሚዲያ ገጾች
- ዐዋጅ ነጋሪ መጽሔት፥ ፱ኛ ዓመት፥ ቁጥር ፲፪፤ ጥቅምት ፳፻፱ ዓ.ም፥ ገጽ 77-78)።

በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ በ2018 ዓ.ም. የተከናወኑ ተግባራት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ

ወዮንክምዋሙ እርኣያ ለእለ እምኑ ሎሔሙ እለ በመቄደንያ ወአካይያ በመቄደንያና በአካይያ ላሉ ምእመናን ምሳሌ ሆናችኋል።"

(1ተሰ. 1፡7)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከላይ በርእሳችን በተጠቀሰው መልእክቱ የተሰሎንቄ ምእመናንን ስለ እምነታቸው ጽናት ስለ መዋደዳቸውና በእግዚአብሔር ላይ ስላላቸው ጽኑዕ ተስፋ እያደነቀ በእናንተ ምክንያት እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን፤ ምክንያቱም እንደ ተመረጣችሁ ዐውቀናልና ይልና፤ «እስመ ኢኮነ ትምህርትነ ኀቤክሙ በነገር ባሕቲቱ ዓዲ በኃይልኒ ወበመንፈስ ቅዱስ -- ወንጌላችን በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም እንጂ በቃል ብቻ ወደ እናንተ አልመጣምና» በማለት ብዙ ድካም የነበረው ቢሆንም የመንፈስ ቅዱስ እገዛ ያልተለየው የተሰሎንቄ የወንጌል አገልግሎት ጠንካራ እምነት ያላቸው፥ መገለጫቸውም ፍቅር የሆነ በተስፋ የጸኑ ምእመናንን እንዳስገኘ በዚህ መልእክቱ ተናግሯል። አያይዞም የተሰሎንቄ ምእመናን ፍቅርና የእምነት ጥንካሬ በመቄዶንያና በአካይያ ላሉ ምእመናን ምሳሌ መሆኑን ሲናገር፦ «ወኮንክምዎሙ አርኣያ ለእለ በመቄዶንያ ወአካይያ፤ በመቄዶንያና በአካይያ ላሉ ምእመናን ምሳሌ ሆናችኋል" በማለት ተናገረ።

የወንጌል አገልግሎት በብዙ ድካም የሚፈጸም ፈተናና መከራ የማይለየው የመስቀል ጉዞ ቢሆንም፥ የመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ ሁል ጊዜ ስለማይለየው ፍጻሜው ያማረ ይሆናል። በተሰሎንቄ የነበረው የወንጌል አገልግሎት ብዙ ድካም እንደነበረው ነገር ግን በአገልግሎቱ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ስለነበረ ለሌሎች አማኞችም ሳይቀር ምሳሌ የሚሆኑ ምእመናንን እንዳስገኘ በማድነቅ ተናግሯል።

መንፈስ ቅዱስ ያልተለየው አገልግሎት ድካም ቢኖረው እንኳን ፍሬያማነቱ አጠያያቂ አይደለም፤ መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት በወረደበት በዓለ ሃምሳ ብዙ ምእመናንን ያፈራው የቅዱስ ጴጥሮስ የወንጌል አገልግሎት ነቀፋና ትችት ያልነበረበት የአገልግሎት መንገዱም አልጋ በአልጋ አልነበረም። የመንፈስ ቅዱስን አሠራር ያልተረዱ ሰዎች 'ጉሽ ጠላ ጠጥቶው ሰክረዋል' ብለው ቢነቅፏቸውም፥ ቅዱስ ጴጥሮስ በጽናት በመስክ የሰማእያኑን ልብ መንፈስ ቅዱስ እየለወጠ በጥቂት አገልግሎት ብዙ ነፍሳትን መማረክ ችሏል።

ይህ ሦስት ሺህ ነፍሳት በማዳን የተጀመረው ሐዋርያዊ አገልገሎት በብዙ ፈተናዎች እየታጀበ በዓለም ሁሉ ወንጌልን በሰከንዶች ሽረፍራፊ ማዳረስ ከሚቻልበት ከዚህ ዘመን ደርሰናል። ዛሬ ላይ እኛ መጠቀም ከቻልን እንደ ሐዋርያት ምእመናን ወደሉበት መሄድ እንኳን ባንችል ካለንበት ወንጌልን ወደ ምእመናን ቤት ማድረስ የምንችልባቸው የመገናኛ ብዙኃን አማራጮች ዘመኑ ሰጥቶናል። ይህንን እድል በአግባቡ ተጠቅሞ ዘመኑን በዋጀ መልኩ የስብከተ ወንገል አገልገሎት ላመኑትም ሆነ ላላመኑት በአግባቡ ማድረስ ያስፈልጋል።

በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ በተ ክህነት የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ የተሰጠውን ያላመኑትን አስተምሮ የማምጣት፥ ያመኑትን በእምነት የማጽናት (የመጠበቅ)፥ የጸኑትን ደግሞ ለምግባር ለትሩፋት፥ ከፍም ላለ መንፈሳዊ ተጋድሎ የማዘጋጀት ተልእኮ በአግባቡ ለመፈጸም ይችል ዘንድ በምእመናን አሥራት ከሚኖሩ ካህናት ምእመናንን ለመጠበቅ የሚሰበሰብ የዓሥራት ዓሥራት (1%) በአግባቡ

በመሰብሰብ የመምሪያውን ተልእኮ መሠረት ያደረጉ ሐዋርያዊ ሥራዎች ተከናውነዋል። እነዚህም፡-

1. የቢሮ አደረጃጀትና ዕድሳትን በተመለከተ፥

ቀደም ሲል መምሪያው የነበረበት ቢሮ ለሥራ ተነሳሽነት የማይጋብዝ ከመሆኑም ባሻገር በመምሪው ሥር ያሉትን የየዘርፍ ኃላፊዎች ለማስተናገድ የማይመች ስለነበር፤ ስፓንሰርሽፕ በማፈላለግና በተገኘው ድጋፍ በፓርትሽን በመከፋፈል እንዲሁም ያለሥራ የተቀመጡ ቢሮዎችን በማስፈቀድ ቢሮውን ለሥራ ምቹ ከማድረግም ባሻገር ቀድሞ ከነበሩት በቁጥር 5 ቢሮዎች ወደ 8 በማሳደግ የተሻለ የሚሮ ከባቢን መፍጠር ተችሏል። በዚህም ሥራ በመምሪያው የነበረውን የቢሮ ችግር በጥቂቱም ቢሆን ተፈትቷል።

2. ለመምሪያው የሚያስፈልጉ የሥራ መሣሪያዎች ማሟላትን በተመለከተ፥

ቀደም ሲል መምሪያው የጽሕፈት ቤት ሥራዎችን በተፈለገው አግባብ ለማሟላት ይቸገር እንደ ነበር ይታወቃል። ነገር ግን ለስብከተ ወንጌል ማስፋፊያና ማጠናከሪያ የሚሰበሰበው 1% መምሪያው እንዲያስተዳድር በቅዱስ ሲኖዶስ ከተወሰነ በኋላ ከሚሰበሰበው የአንድ ፐርሰንት እና ካገኘው ስፖንሰር ገቢ ላይ ወጪ በማድረግ 4 ዴስክቶፕ ኮምፒውተር እና ሦስት ፕሪንተር እንዲሁም ልዩ ልዩ የጽሕፈት መሣሪያዎችን ሕጉን በጠበቀ የግዥ ሥርዓት ተገዝቶ በመሟላቱ ሥራዎች በተቀላጠፈ መልኩ እየተሠሩ ይገኛሉ።

3. በአሠራር ዙሪያ የተደረጉ ተደጋጋሚ ውይይቶችን በተመለከተ፥

ለሦስት ዓመታት ያህል የስብከተ ወንጌል የስምሪት ተቋርጦ በመቆየቱ የመምሪያው ሰባክያንና ልዩ ልዩ ሠራተኞች የአገልግሎት ተነሳሽነታቸው ቀንሶ ስለነበር በመምሪያው ሊቀጳጳስ መመሪያ ሰጪነት ተነሳሽነትን ለመፍጠርና በትብብር መሥራትን ለማዳበር ተደጋጋሚ ውይይቶች ተደርገው በተፈጠረው ተነሳሽነት በበጀት ዓመቱ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል። በቀጣይም ይኸው ተናቦ የመሥራት የሥራ ባሕል በማዳበር የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ በትኩረት ይሠራል።

4. ለመምሪያው አስፈላጊውን የሰው ኃይል በማስመደብ ለማጠናከር የተደረገውን ጥረት በተመለከተ፥

የአንድ ፐርሰንት ወርኃዊ አስተዋጽዖ መምሪያው እየሰበሰበ በራሱ እንዲያስተዳድር ቅዱስ ሲኖዶስ ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት የጽ/ቤት፤ የፋይናንስ እና የንብረት አስተዳደሩን በተገቢው መንገድ ለመምራት፤ ለማንቀሳቀስ እና የተሰጠውን አደራ በአግባቡ ለመወጣት ይቻል ዘንድ የሚዲያ ባለሙያዎች፤ ሒሳብ ሹም፤ ቁጥጥር፤ ገንዘብ ያዥ፤ መዝገብ ቤት፤ ጠቅላላ አገልግሎት እና ግዥ ክፍል በማስመደብ ጽ/ቤቱን በአዲስ መልኩ ተገቢና አስፈላጊ በሆነ የሰው ኃይል ማደራጀት ተችሏል።

5. መጠነኛ ቤተ መጻሕፍት ማደራጃትን በተመለከተ፥

የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ሰፊ ዝግጅት እና በየጊዜው ራስን ማሻሻልን የሚጠይቅ የአግልግሎት ዘርፍ በመሆኑና መምሪያው በሥሩ ከ25 በላይ ተዘዋዋሪ ሰባክያነ ወንጌል ያሉት መምሪያ ስለሆነ ለአገልግሎት ዝግጅት የሚጠቅሙና የአመለካከት ክፍታን የሚጨምሩ መንፈሳዊ፤ ሥነልቦናዊ፤ ማህበራዊና ፍልስፍናዊ ይዘት ያላቸውን መጻሕፍት ከመምሪያው ሠራተኞች፤ ከበጎ አድራጊ ግለሰቦች በማሰባሰብ መጠነኛ ቤተ መጻሕፍት በመምሪያው ቢሮ ማደራጀት ተችሏል፤ አገልግሎት እየሰጠም ይገኛል።

6. የመቶ ሃያው ቤተሰብ ፕሮጀክት የ1% ወርኃዊ የስብከተ ወንጌል መዋጮ አሰባሰብን በተመለከተ፥

ቀደም ሲል የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ የስብከተ ወንጌል አገልግሎቱን ከከተማ እስከ ገጠሪቱ ቤተ ክርስቲያን ለማዳረስ ታሳቢ በማድረግና በበጀት እጥረት ችግር እንዳይገጥመው የ120 ቤተሰብን ከመመሥረትና ወርኃዊ መዋጮ እንዲደረግ ከማዘዝ ጀምሮ በየትኛውም የቤተ ክርስቲያን መዋቅር የሚያገለግል አገልጋይ ወይም ሠራተኛ ከሚከፈለው ወርኃዊ ደመወዝ ላይ 1% ለስብከተ ወንጌል አገልግሎት እንዲያበረክት በተወሰነው መሠረት የ1% ወርኃዊ አስተዋጽዖ ከመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተክህነት ጀምሮ እስከ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ድረስ መምሪያው በከፍተኛ ሁኔታ በመንቀሳቀስ እና ከአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ጋር ቅንጅት በመፍጠር ውሳኔውን ከዋናው መሥሪያ ቤት እስከ አዲስ አበባ ገዳማትና አድባራት ድረስ በማውረድ ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል። በተገኘው ገቢም የስብከተ ወንጌል ተደራሽነት በእጅጉ እየሰፋ ነው፤

7. የመምሪያውን ማኅበራዊ ሚዲያ

ማጠናከርን በተመለከተ፥

መምሪያው ዘመኑ ያፈራውን ቴክኖሎጂ፤ ማኅበራዊ ሚዲያና ልዩ ልዩ መተግበሪያዎች ተጠቅሞ የቅዱስ ወንጌልን አገልግሎት ለዓለም ሁሉ ማዳረስ ዋና ተግባሩ በመሆኑ ለዚህ አገልግሎት የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን ከማሟላት ጀምሮ ሁለት ጊዜያዊ የሚዲያ ባለሙያዎችን በጊያዊነት በመቅጠርና በመምሪያው ስም ልዩ ልዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች /ፌስቡክ፤ ቴሌግራም እና ቲክቶክ/ በመክፈት ስብከተ ወንጌል ነክ ዜናዎችንና ልዩ ልዩ ትምህርቶችን እያስተላለፈ ይገኛል፤በዚህም በርካታ ምእመናን ማኅበራዊ ሚዲያን በመጠቀም ትምህርትና አጠቃላይ የመምሪያውን እንቅስቃሴ መከታተል የሚችሉበት እድል ተፈጥሯል፡፡ለዚህም ሥራ አንድ የሥነ ጽሑፍና አንድ የግራፊክስ ባለሙያ በኮንትራት ተቀጥረው ሥራውን በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

8. በመምሪያው ስም እየተዘጋጀ በኢቢኤስ ቴሌቭዥን ጣቢያ የሚተላለፈውን መርሐግብር በተመለከተ፥

ዓለም ዐቀፍ ተመልካች ካለው የኢቢኤስ ቴሌቭዥን ጣቢያ በተገኘው ሳምንታዊ ነጻ የአየር ሰዓት ለብዙሖች ተደራሽ ሊሆን የሚችል ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት መስጠት ይቻል ዘንድ ሚዲያ ክፍሉን የሚመራ ባለሙያ በማስመደብና ለጊዜው የሚያስፈልገውን የሚዲያ መሣሪያ በማሟላት በተሻለ ይዘትና የአቀራረብ መንገድ ትምህርትና ስብከቶችን እያዘጋጀ ረቡዕ ከቀኑ 9፡00-10፡00 ሰዓት እና እሑድ ከጧቱ 4፡00-5፡00 ሰዓት ቅዱስ ወንጌልን በተሻለ ሁኔታ ተደራሽ እያደረገ ይገኛል፡፡

9. የመጽሔት ሕትመትን በተመለከተ፥

በሕትመት ሚዲያው ረገድም ቀደም ሲል በመምሪያው እየታተሙ ሲሰራጩ የቆዩትን የልሣነ ተዋሕዶ መጽሔት እና የዜና ቤተክርስቲያን ጋዜጣ ሕትመት በተሻለ ይዘትና አቀራረብ በድጋሚ ለመጀመርና በዲጅታል መልኩም በድረ-ገጽ ለማዳረስ እንዲቻል ከዘጋጆችን በማነጋገር በተሻለ ጥራትና አቀራረብ ዝግጅቶቹ እንዲቀጥሉ በመምሪያው ሊቀ ጳጳስ ጠንከር ያለ መመሪያና አቅጣጫ ተሰጥቶ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ የሦስተኛ ዓመት የስብከተ ወንጌል ቀንን እና በዓለ ጥምቀትን አስመልክቶ በርካታ መምህራንን ያሳተፈ ልዩ ዕትም መጽሔት ሁለት ጊዜ በማዘጋጀትና በማሳተም በነፃ ለምእመናንና ለበዓሉ ታዳሚያን እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

10. ምክክርና ውይይት በተመለከተ፥

መምሪያው ከሁሉም አህጉረ ስብከት ጋር ያለውን መዋቅራዊ ግንኙነትና የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ተደራሽነት ዙሪያ መሪነትና ተልእኳችን በሚል መሪቃል ምክክርና ውይይት ለማድረግ መስከረም 6 ቀን 2018 ዓ.ም ባዘጋጀው ጉባኤ ከየአህጉረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጆች ጋር በቀረቡት ሁለት ጥናታዊ ጽሑፎች መነሻነት ለአንድ ቀን ምክክርና ውይይት ተደርጎ በቀጣይ እንዴት እንሥራ በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ በውይይቱም የተገኙ ብአቶች መምሪያውም በሥራ ላይ እያዋለው ይገኛል፡፡

11.በመምሪያው ስም ድሕረ ገጽ /ዌብሳይት/ ማበልጸግን በተመለከተ፥

በሀገረ ኖርዌ ከሚገኘው የተክሌ ቴክኖሎጂ አስተዳደር አገልግሎት አማካሪ /አጥቢያ ዶትኮም/ የተባለ የቴክኖሎጂ ድርጅት ጋር መምሪያው በኢንተርኔቱ ዓለም ሰርበር ላይ የራሱ አድራሻ /ዶሜን ኔም/ እንዲኖረው በመነጋገር፤ የድረ ገጽ ይዘቱን በመለየትና የጽሑፍ ሥራዎችን በማሰባሰብ በመምሪያው ስም ድረ ገጽ የማበልጸጉ ሥራ ከ5 ወራት በኋላ ተጠናቅቆ ሚያዝያ 19 ቀን 2018 ዓ.ም የመምሪያው ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ማርቆስ እና ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በተገኙበት በይፋ አስፈላጊውን ክፍያ በመፈጸም ሥራው እንዲጀምር ተደርጓል፡፡

12. ሀገር ዐቀፍ ልዩ ስምሪትን በተመለከተ የስብከተ ወንጌል፥

ስምሪት ወይም ተልእኮ የቅድስት ቤተክርስቲያን ዋና ተልዕኮ ማስፈጸሚያ መንገድ በመሆኑ ላለፉት ሦስት ዓመታት ተቋርጦ የቆየውን ስምሪት በድጋሚ በማስጀመር ዓመታዊ ክብረ በዓላት ተጠብቆ ከሚደረገው ስምሪት በተለየ መልኩ የስብከተ ወንጌል ተደራሽነትና የምዕመናን ቁጥር አነስተኛ የሆነባቸው ጠረፋማና አንጻራዊ ሰላም ባለባቸው አህጉረ ስብከት የመነሻ ጥናት ተከናውኖ የመምሪያውን ሰባክያን የተሻለ የትምህርት ዝግጅት ካላቸውና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት ይችላሉ ተብለው ከተመለመሉ ድጋፍ ሰጭ ሰባክያነ ወንጌል ጋር አቀናጅቶ ልዩ ስምሪት በማድረግ በተመረጡ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ለአገልጋይ ካህናት ሥልጠና ተሰጥቷል፤የስብከተ ወንጌል ጉባኤያትም ተከናውኗል፡፡

13. ሚያዝያ 18 ቀን 2018 ዓ.ም በተመረጡ 12 አብያተክርስቲያናት የተደረገውን ሕዝባዊ የስብከተ ወንጌል ጉባኤ በተመለከተ፥

ሦስተኛውን ሀገረ አቀፍ የስብከተ ወንጌል ቀን ከሚያዝያ 18-19 ቀን 2018 ዓ.ም ለሁለት ተከታታይ ቀናት የተከበረ ሲሆን ቀኑን በማሰብ ሚያዝያ 18 ቀን በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በተመረጡ 9 ገዳማትና አድባራት እንዲሁም በሸገር ከተማ ሀገረ ስብከት በተመረጡ 3 አብያተ ክርስቲያናት በድምሩ በ12 ቦታዎች በመምሪያው አስተባባሪነትና አስፈላጊውን ወጪ ሁሉ በመሸፈን ወጥ የሆነ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት በተመሳሳይ ስዓት ተከናውኗል።

14. ሦስተኛውን ሀገር ዐቀፍ የስብከተ ወንጌል ቀን ማክበርን በተመለከተ፥

ቀደም ሲል ቅዱስ ሲኖዶስ ባሳለፈው ወሳኔ መነሻነት የስብከተ ወንጌል አገልግሎትንና የተጓዘበትን የዘመናት ጉዞ ለመዘከር በሀገር ዐቀፍ ደረጃ የስብከተ ወንጌል ቀን ከ2016 ዓ.ም ጀምሮ ለሦስተ ተከታታይ ዓመታት ሲከበር መቆየቱ የሚታወስ ሲሆን እየተጠናቀቀ ባለው በ2018 ዓ.ም በጀት ዓመትም ለሦስተኛ ጊዜ በቅድስት ሥላሴ ዩንቨርስቲ በልዩ ሁኔታ ሲከበር አሁናዊ የስብከተ ወንጌል አገልግሎትና ተግዳሮቶቹ በሚል ርእስ የዳሰሳ ጥናት ቀርቦ ውይይት ተደርጓል። በአገልግሎት ለደከሙ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና አጋር ተቋማት ዕውቅና ተሰጥቷል።

15. ሳምንታዊ የረቡዕ የዮሐንስ ወንጌል ጥናት በተመለከተ፥

በመምሪያው አስተባባሪነት እና በመ/ብሉይ አእመረ አሸብር ሥልጠና ሰጪነት በየሳምንቱ ረቡዕ የሚሰጠው ተከታታይ የዮሐንስ ወንጌል ጥናት በርካታ ሠልጣኞች የሚሳተፉበትና መልካም ውጤት የተመዘገበበት ነው። በመምሪው ሊቀ ጳጳስ መመሪያ ሰጪነት በቀጣይም በተጠናከረ መልኩ ለማስቀጠል እንዲቻል የሚያስፈልገውን የሥልጠና ማቴሪያል እንዲሟላ በመምሪያው አስተዳደር ጉባኤ ውሳኔ አግኝቷል። ሥልጠናው በጽርሐ ተዋሕዶ መፍረስ ምክንያት ተቋርጦ የነበረ ቢሆንም ብፁዕ አቡነ ማርቆስ ከቅድስት ሥላሴ ዩንቨርስቲ የሥልጠና ቦታ በጊዜያዊነት በማስፈቀድ ሥልጠናው እንዲቀጠል ተደርጓል።

16. የአንድ ከመቶ (1%) አሰባሰብ ዕውቅና መስጠትን በተመለከተ፥

ከላይ በርእሳችን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የተሳሎንቄ ምእመናንንን በመቁደንያ እና በአካይያ ላሉት ምሳሌ ሆናችሁላቸው እንዳለው የቅዱስ ሲኖዶስን ውሳኔ አክብረው የመምሪያው ተልእኮ የቤተ ክርስቲያን ዋነኛ ተልእኮ ነው በማለት የሚጠበቅባቸውን የአንድ ከመቶ (1%) አስተዋፅኦ በአግባቡ ያሰባሰቡ መምሪያዎች፥ ድርጅቶች፥ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብት፥ ስምንቱ ክፍላተ ከተማ አብያት ክህነት፥ መንፈሳውያን ማኅበራት እና የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ያደረጉ አካላት ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ፥ የራያ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፥ ብፁዕ አቡነ ሕዝቅኤል የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ የበላይ እና የከፋ ሸካ ምእራብ ሸኮ ቤንች ማጂ ሀአህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፥ ብፁዕ አቡነ ማርቆስ የስብከተ ወንጌልና ሀዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ሊቀ ጳጳስ፥ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት ጳጉሜን 2 ቀን 2018 ዓ.ም በካፒታል ሄቴልና ስፓ የመሰብሰቢያ አዳራሽ የምስጋናና የዕውቅና መርሐ ግብር በማከናወን ከላይ ለተጠቀሱት ተቀቋማትና ግለሰቦች የሠርተፍኬትና የካባ ሽልማት ተበርክቷል።

ከላይ የተዘረዘሩት ሥራዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ የብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ የደቡብ ምዕራብ ሸዋና የሸገር አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የምስክየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም የበላይ ኃላፊ፥ እንዲሹም የብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ፥ የራያ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፥ አባታዊ መልካም አመራርና ድጋፍ፥ የመምሪያው ሊቀ ጳጳስ የብፁዕ አቡነ ማርቆስ የዕለት ተዕለት ክልትትና አቅጣጫ ሰጪነት ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዝ በመኾኑ መምሪያው ለብፁዓን አባቶቻችን ከፍተኛ ምስጋና ያቀርባል።

ውስብሐት ለእግዚአብሔር!!!

የአዳራሽ ትዝታ

በመ/ር ዳንኤል ሰዩፈ ሚካኤል

ለሁሉም ነገር የራሱ መነሻ አለው። ተቋማትን ጨምሮ ሁሉም ነገሮች በሂደት ይሻሻላሉ። ዛሬ በከፍተኛ ክብርና በውድ ቁሳቁስ በከበሩ ድንጋዮችና በማራኪ ሥነ ጥበብ ተሠርተው አምልኮ የምንፈጽምባቸው ታላላቅ ካቴድራሎች ከመሠራታቸው በፊት ሥርዓተ አምልኮም ሆነ የምሥጢራት አገልግሎት የሚፈጸምባቸው መካናት የስደት ዋሻዎች፣ ግበበ ምድር፣ በአለቶች መካከልና በሰዋራ ቦታዎች ነበር። ከሣር የተሠሩ ጎጆዎች፣ በድንጋይ የተገጣጣሙ ዕድሞዎችም አገልግሎት ላይ ውለዋል። ዛሬ ደቀመዛሙርትና መምህራን በምቹ ወንበር፣ በሰፋፊ ክፍሎች፣ በአሣንሥር ወጥተው ፎቅ ላይ ተንደላቀው የሚያስተምሩባቸው ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ከመሠራታቸው በፊት በድንጋይ መቀመጫ፣ ጭናቸውን እንደ ጠረጴዛ አድርገው የሚማሩ ተማሪዎች፣ ዛፍ ደገፍ ብለው ተሐዋስያንን በጭራ እየተከላከሉ የሚያስተምሩ ሊቃውንት ነበሩ፡ ፡ ዛሬም ያልተለወጠበት ቦታ ይኖራል።

በተቋማዊ እድገትም እንዲሁ ነው። የዛሬው ታላቅ አዳራሽ ከመሠራቱ በፊት ለዛሬው አዳራሽ መሠረት የነበው የቀድሞው አዳራሽ በየዘመኑ በርካታ የሆኑ ትዝታዎችን አሳልፏል። በዚያ አዳራሽ ከቁርባን ቅዳሴ በቀር ይልተፈጸመ መንፈሳዊ አገልግሎት አልነበረም፣ ስብከት፣ ጸሎት፣ ወረብ፣ ምክክር፣ ሰበካ ጉባኤ፣ ፍትሐት፣ ዝክር፣ ግብዣ፣ ምርጫ፣ ሹመት፣ የወጣቶች ክብረ በዓል፣ በዓለ ሢመት፣ ሙዚየም (ዐወደ ርእይ)፣ ጽሕፈት ቤት፣ እና በርካታ ሁነቶች ተከናውነውበታል። ከቀድሞው የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ እስከ ቅዱስ ሲኖዶስ፣ ከዚያም የጉባኤ ሊቃውንት፣ የሰበካ ጉባኤና የሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎት ተከናውነውበታል።

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ዘመነ ፕትርክና የነበረውን የግቢውን ሁኔታ የሚያስታውሱት አባ ናሁሰናይ በኢትዮጵያ ዕሥራ ምዕት አከባበር ወቅት ሲናገሩ፤ አዳራሹ በቆርቆሮ የተሠራ፣ ከውስጡ በሚያምሩ ግጥምጥም እንጨቶች የተሸፈነ፣ ከመሬቱ ጋር የተያያዙ አግዳሚ ወንበሮች የነበሩበት፣ መድረኩ ላይ በትልቁ የጌታችን ሥነ ስቅለትና የኢትዮጵያ ፊደላት የተጻፉበት የሚከፈትና የሚዘጋ መጋረጃ ነበረው ይላሉ። በዚህ አዳራሽ በየሳምንቱ ሰኻ ጠዋት ሁሉም የቤተ ክህነት ሠራተኛ በአንድነት ይሰበሰብበት ነበር ቀሳውስት ማዕጠንት ዲያቆናት መስቀል ይዘው በአንድ ላይ ጸሎተ ወንጌልና ኪዳን አድርሰው፣ ትምህርተ ወንጌል ሰምተው ወደ ሥራ ይገቡ ነበር። በየሳምንቱ ዓርብ ሐዋርያዊ ድርጅት በሚያስባባረው መሠረት እንዲሁ ጸሎተ ምሕላ ይደርስ ነበር። ቅዳሜ ዋና ዋናዎቹ ማኅበራትና ተቋማት ከተምሮ ማስተማር፣ ከዐምደ ሃይማኖት፣ ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ፣ ከሰዋስወ ብርሃን ተራ እየገቡ ለሕዝቡ ትምህርት ይሰጥ ነበር። አንዳንዱ ትምህርት እየተቀረጸ በራዲዩ ይተላለፍ ነበር።

በብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ዘመን አዳራሹ በደንብ ተስፋፋ፣ በግራና በቀኝ ቢሮዎች ተሠሩለት፣ የራሱ አጥርም በአትክልት ታጥሮለት ነበር። የቤተ ክህነቱም ስብሰባ በዚሁ ይደረግ ነበር፤ ፓትርያርኩ አንግዶችን፣ ከአህጉረ ስብከትና ከሀገር ክፍሎች ጠቅላይ ግዛት የሚመጡ ሊቃውንት ተሰብስበው ምክክር ያደርጉበት ነበር። ግብዣም ሆነ ማናቸውም ነገር ይፈጸምበትና በኋላ ደግሞ ጸድቶ ትምህርት ይሰጥበት ነበር። ወለሉም በጥሩ ሁኔታ የተሠራው በሳቸው ጊዜ ነው።

የቀድሞው አዳራሹ በደንብ ተስፋፋቶ የተሠራው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ሦስተኛው ፓትርያርክ ዘመነ ፕትርክና ነው፡ ፡ ቅዱስነታቸው የመጀመሪያውን ዓመታዊ የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ያስጀመሩት በዚሁ አዳራሽ ነበር፡ ፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያለማቋረጥ አጠቃላይ ሀገር አቀፍ ጉባኤው ተከናውኖበታል። የመጀመሪያዎቹ የቃለ ዐዋዲ ረቂቆችና የልዩ ልዩ ደንቦች፣ የሥራ መመሪያዎች ዝግጅትም በዚሁ አዳራሽ ይከናወን ነበር። በዓቢይ ጾም የመዲናና ዘለሰኛ ቀረጻ ለማድረግ መሰንቆ የሚመቱና በገና የሚደረድሩ ዘማሪዎች በዚሁ አዳራሽ ሲለማመዱ ይቆዩና ከአዳራሹ በታች በተሠራው መቅረጫ ክፍል ገብተው ይቀረጹ ነበር።

በግራ በኩል የጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ፣ በቀኝ በኩል ደግሞ በጣውላ በተሠሩ ባለ አንድ ፎቅ ቤት በርካታ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት መምሪያዎችና ልዩ ልዩ ጽሕፈት ቤቶችን ሁሉ አካቶ የያዘ ነበር። በሥሩ ሰፊ የሆነ የዕቃ ግምጃ ቤት፣ ንብረት ክፍል ነበሩት፤ ብዙ ጊዜ ዝናብ ሲጥል በርካታ ወረቀት ነክ እቃዎች እየተበላሹ ስለነበር መዝገብ ቤቱና ቤተ መጻሕፍቱ ወደ ውጭ እና ከላይኛው ደርብ እንዲሆኑ ተደረገ። በዚያን ጊዜ አዳራሹ ከሥር አንድ ወደ ታች ፎቅ፣ በአንድ አቅጣጫ ደግሞ ባለ አንድ ፎቅ ቢሮዎች ነበሩት። ይኸ ተመሳሳይ አገልግሎት ብዙም ለውጥ ሳይደረግበት የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን ዘመን ተሻግሯል፡ ፡ በቅዱስነታቸው ዘመን መጠነኛ እድሳት ተደርጎለት፣ ተመሳሳይ አገልግሎትን ሲሰጥ ቆይቷል።

የቀድሞው የስብከተ ወንጌል አዳራሽ ከመፍረሱ በፊት ሰፊ ጥገናና ማሳፋፋት የተደረገለት በአምስተኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ዘመነ ፕትርክና ነበር። ቅዱስነታቸው በአጠቃላይ

የመንበረ ፓትርያርኩን ግቢ በልዩ ሁኔታ ሲገነቡት ቀድሞውን የፓትርያርኮች መኖሪያ ወደ ሙዚየምነት ቀይረው ታላቅ የቅርስ ማሳያ አደረጉት፣ ራሱን የቻለ የብፁዓን አባቶች መኖሪያ ሕንፃ፣ የሙዚየም ቢሮና የቅዱስ ሲኖዶስ ጽሕፈት ቤት፣ ራሱን የቻለ ጽርሐ መንበር የቅዱሳን ፓትርያርኮች ፓላስ፣ ደረጃውን የጠበቀና የአኅት አብያተ ክርስቲያናት ፓትርያርኮች ከነረዳቶቻቸው ማስተናገድ የሚችል የዓለም አቀፍ ግንኙነትና የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጽሕፈት ቤት ሕንፃ፣ እንዲሁም ሁሉን ማካተት የቻለ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና መሥሪያ ቤት ሲሠሩ ከአዳራሹ ጋር የነበሩት ጽሕፈት ቤቶች በሙሉ ፈረሰው ወደ ስብከተ ወንጌል አዳራሹ ተጠቃለሉ። ትልቁ አዳራሽም ብቻውን ራሱን ችሎ ለአገልግሎት ተዘጋጀ። ሰው የመያዝ አቅሙ ከነበረው በጣም ሰፊ አዳራሽ ሆነ፣ ውስጡ በደንብ ተደራጅቶ ወለሉና ጣሪያው ሳይቀር ተጠናክሮ ተሠራ፣ በአንድ በኩል ወደ ጎን ሰፋ ብሎና የእንጨት መስኮቶቹ ተነሥተው መስታወት ተገጠመለት። የራሱ የሆነ ከፍ ያለ መድረክና ጽሕፈት ቤት ኖሮት ኃላፊም ተመደበለት።

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ (ዶ/ር) ዘመነ ፕትርክና አዳራሹ በየሳምንቱና በየወሩ ታላላቅ መንፈሳዊ አገልግሎቶችን ይሰጥ ነበር፡ ፡ በተለይም ሀገራችን ዕሥራ ምእትን ስታከበር ተጨማሪ እድሳት ተደርጎለት የቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፍ ዐውደ ርእይ ተዘጋጀበት፡ ፡ ይኸ በዓይነቱ ልዩ የሆነ ዐውደ ርእይ መላውን የ2000 ዓ/ም ዐሥራ ሁለት ወራት ከፍት ሁኖ በሚሊየን የሚቆጠር ሕዝብ ያለማቋጥ ጎበኘው። የሀገራችን ታሪክ፣ ቅርስ፣ ሥርዓተ አምልኮ፣ ሥነ ጥበብ፣ ኪነ ጥበብ፣ ልማት፣ ቋንቋ፣ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች ለመለው ዓለም ታዩበት። በወቅቱ በሀገራችን ከነበሩ ሚዲያዎች ዐውደ ርእዩን ያልዘገበው አልነበረም።

ቅዱስነታቸው ከዚህ በኋላ ዕሥራ ምእቱን ዐውደ ርእይ ሲዘጉ ይኸ ሁሉ ትምህርት ባይቋጥ መልካም ነበር። ግን ቦታ የለንም ስለዚህ ወደፊት በቋሚነት ሁሉን የሚያስተናግድ ትልቅ አዳራሽ መሥራት ይኖርብናል በማለት ትልቅ እቅድ አቅደውም ነበር። ዓለም አቀፍ ደረጃውን ጠበቀ የስብሰባ አዳራሽ ለመገንባትም የመሠረት ድንጋይ አስቀምጠው ነበር። ለዚህም ራሱን የቻለ ጽሕፈት ቤትና የሥራ ኃላፊም ተመድቦ ነበር። የቅዱስነታቸው ሐሳብ በወቅቱ ሳይፈጸም ሐዋርያዊ የቅድስና አገልግሎት ዘመናቸውን ፈጽመው ወደ ፈጣሪያቸው በክብር ተጠሩ።

ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር እንደሚባለው ለሁሉም ጊዜ የራሱ ዘመን አለውና የቀድሞው አዳራሽ በእድሜ ብዛት እሱም አገልግሎቱን ፈጸመ። ዐዲስ አዳራሽ ይሠራ ዘንድ ግድ ሆነ። የዚህ አዳራሽ ሥራም በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ጸድቆ፣ በጀት ተመድቦለት፣ ዲዛይንና የሥራ ተቋራጩ ተመድቦለት ላለፉት ጥቂት ዓመታት ግንባታው ሲከናወን ቆይቶ እነሆ ዛሬ እንዲህ ያለ አስገራሚ ዓለም አቀፍና ሁለገብ የስብሰባ አዳራሽ ተሠርቶ ለምረቃ መብቃት ቻለ።

የአሁኑ አዲሱ አዳራሽ ዋና የስብሰባ አዳራሽ፣ የተወካዮች መቀመጫ፣ ዘመናዊና በዲጂታል ቴክኖሎጅ የታገዘ የንግግር መድረክ፣ የከፍተኛ ባለማዕረግ አባቶችና የሥራ ኃላፊዎች የክብር መቀመጫ በተሟላ መልኩ የተደራጀለት፣ የራሱ የድምፅ መስጫ/የድምፅ መቆጣጠሪያ፣ የውይይትና የምክክር መለስተኛ አዳራሾች፣ የኮንፈረንስ ክፍሎች ወይም አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የኮሚቴዎች ክፍሎች፣ የሁለትዮሽ እና ባለብዙ ወገን ስብሰባ ክፍሎች፣ የቅዱስ ሲኖዶስ መስብሰቢያ፣ የግል የክብር እና ባለማዕረግ ክፍሎች፣ የትርጉምና የመገናኛ ተግባር መፈጸሚያ፣ የቀጥታ ትርጉም ክፍሎች፣ የኦዲዮና ቪዲዮ መሣሪያዎች የብሮድካስት ክፍል፣ የቴክኒክ ቁጥጥር ክፍል፣ ራሱን የቻለ የእንግዳ የመቀበያና የማኅበራዊ አገልግሎት ተግባር ማከናወኛ፤ ዋና መግቢያና መረጃ ፈላጊዎችን ማስተናገጃ፣ የከፍተኛ ባለሥልጣኖችና ባለማዕረጎች፣ የዲፕሎማቶች ሳሎን፣ የሚዲያና ሕዝብ ግንኙነት ተግባር መፈጸሚያ የፕሬስ ማዕከል፣ የጋዜጣዊ መግለጫ ክፍል፣ የጋዜጠኞች የሥራ ቦታ፣ የቃለ-መጠይቅ ክፍሎች፣ የራሱን አስተዳደር ተግባር መፈጸሚያ የቢሮ ቦታዎች፣ የሴክሬታሪያት ክፍል፣ የምዝገባና የአክሬዲቴሽን ቦታ፣ የሠራተኞች ክፍሎች፣ የደህንነት ተግባር ማከናወኛ፣ የልዩ ልዩ ባለማዕጎች መግቢያና መውጫ፣ ለአካል ጉዳተኞች ታሳቢ የሆነ መስተንግዶ ያለው፣ የአደጋ ጊዜ መውጫዎች፣ የባህልና የኤግዚቢሽን ተግባር፣ ዐውደ ርእይና የመንፈሳዊ ክንውኖች ማስፈጸሚያ ቦታ፣ የምግብ ዝግጅትና ካተሪንግ፣ መጋዘን፣ በየማዕረጉና በየጾታው ደረጃቸውን የጠበቁ መፀዳጃ ቤቶች፣ የጥገና ቦታ፣ የመወጣጫ አሳንሥሮች፣ ተገጥመውለት ስናይ በቀድሞው ትዝታ ውስጥ የነበረውን አገልግሎት በጉጉት እየናፈቅን እናየዋለን።

የዚህ አዳራሽ መሠራት ቤተ ክርስቲያናችን በሀገር ውስጥ ለምትፈጽማቸው ማናቸውም ደረጃቸውን የጠበቁ ስብሰባዎች፣ ምክክሮች፣ ውይይቶችና መንፈሳዊ መርሐ ግብሮች ብቻ ሳይሆን ከፍ ያሉ ዓለም አቀፍ ክንውኖችንም ለማስፈጸም የሚረዳ ትልቅ ውጤታማ ስኬት ነው። ዛሬ በየትኛውም ዓለም መሪዎች ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው ከሚሠሯቸው መንፈሳዊና ማኅበራዊ ማእከላት ውስጥ አንዱና ዋናው የሰዎች መሰብሰቢያ አዳራሽ ነው። መሰብሰቢያ አዳራሾች ሰውን ከሰው ያገናኛሉ፣ ሐሳብ ለሐሳብ እንዲለዋወጥ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ።

ሐሳብ ከአእምሮ አዳራሽ ይፈልቃል፣ ከዚያም ከሌሎች ሰዎች ሐሳብ ጋር ለማዛመድ ሰዎች እርስ በርሳቸው የሚወያዩበት ቦታ ይፈልጋሉ። እንኳንስ ጥቂት ሰዎች ይቅርና ዛሬ የዓለም መንግሥታት በአንድነት ተሰባስበው ለመወያየት ደረጃውን የጠበቀ መሰሰቢያ ይፈልጋሉ፡ ፡ ለዚህም አገር አቋርጠው ከየሀገሩ ተሰባስበው በኒው ዮርክና በጀኔቫ፣ በቶኪዮና በአምስተርዳም አዳራሾች ተሰባስበው በርካታ ዓለም ታሪክ የቀየሩ ውይይቶችን አድርገዋል። ዛሬም በየዓመቱ ወደ ኒው ዮርክ በመጓዝ በመሪዎች መነጋገሪያ ድምጻቸው ያሰማሉ፡ ፡ የአፍሪካ መሪዎችም በየዓመቱ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው አዳራሽ እየተሰባሰቡ የህገሮቻቸውንና የመንግሥቶቻቸውን አቋም ያንጸባርቃሉ። ታላላቅ አዳራሾች በሰው ልጅ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊና ሁለንተናዊ ሕይወት ውስጥ ትልቅ ሚና አላቸው።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ ተመሳሳይ ታሪክ ባለቤት ናት፤ ዛሬው አዳራሽ ከመሠራቱ በፊት በጠባብ ቤትም ቢሆን ከመቶ የማያንሱ ሊቃውንት የዛሬ መቶ ዓመት መንፈሳዊ ጉባኤ መሥርተው ተቋም አቅንተዋል። ተውልድ ተሻጋሪ ሥራን ሠርተዋል፡ ፡ በመስሰቢያ አዳራሽ አገልግሎት ከቀድሞው ትዝታ እስከ አሁኑ ስኬት ቤተ ክርስቲያን ብዙ ጉዞዎችን ተጉዛ ለዚህ በመድረሷ ደስታው እጥፍ ድርብ ነው። ሁላችንንም እንኳን ደስ ያለን።

TSIRHA TEWAHEDO

ጽርሐ ተዋሕዶ















Octobe 10, 2026 AD

EOTC Department of Public Relations

Tsirha Tewahedo



Modern and International Multipurpose Conference Center

This special edition magazine, titled 'Tsirha Tewahedo', was prepared by the Public Relations Department to mark the inauguration of the modern international multipurpose conference center built by the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church Patriarchate Head Office.

Table of Content

The message of the magazine 75

Message from the Grand Committee 78

Message of H.H. The Patriarch 81

Message of H.G. The General Manager 83

Message of Secretary General of the Holy Synod 86

Message of Deputy Manager of the Patriarchate for Spiritual Affairs 90

Message of Deputy Manager of the Economic and Social Sector 92

General Patriarchate Office In the past sixteen months 94

An International Conference Center that Befits the History and Dignity of Our Church From Concept to Completion 116

Editor in Chief
Liqe Siyuman Eskindir Gebre Kristos

Edition
L.S. Nebiyu Eliyas

Graphic Design
Temesgen Tomas

Translation
Miss Yordanos Addise
Mhr. Akalewold Tessema (Ph.D.)
Assistant Professor Rev. Girma Batu
Mhr. Daniel Seifemichaiel

Photography
M.S. Abba Kiros Woldeab

Publisher
Tisaie Zegubaie Printing press

The message of  the magazine

Generational Succession for the Growth of the Church

The ancient, historical, national and international Ethiopian Orthodox Tewahedo Church's successful efforts to modernize its administrative structure, accelerate its development and increase its revenue capacity have been successful because of its ability to carry out its tasks through collaboration and cooperation. The ancient churches that have been built since ancient times and have been passed down through generations, and the buildings and houses that serve as a source of income for the church today are permanent witnesses.

When our ancestors conceived, planned, and initiated long-lasting projects but passed away before their completion, other fathers who were present at the inception or joined on the eve of their launch accepted the trust of their predecessors. By carrying out these duties faithfully and bringing them to completion, they honored the memory of their fathers while enabling the new generation to benefit from these developmental works and serve the Church. In turn, as each generation envisioned, planned, and constructed developments for the next, their children picked up the layer whenever their parents' time drew to a close ultimately bringing us to where we stand today.

This state-of-the-art international multi-purpose conference center being inaugurated today is likewise a testament to the farsighted vision of our Church's fathers within this pro-

cess of generational succession a project that stands as a source of pride for both the Church and the nation.

Believing that a modern building reflecting the Church's dignity and status had to be constructed to enable the preaching of the Gospel with breadth and fullness, the plan was originally envisioned by His Holiness Abune Paulos I, Patriarch of Ethiopia. Speaking repeatedly from the site of the former hall where this modern facility now stands, His Holiness voiced the necessity of constructing a modern Gospel preaching center, secured the approval of the Holy Synod, and laid the foundation stone.

However, although His Holiness's had passed, during the tenure of His Holiness Abune Mathias I, Patriarch of Ethiopia, under the executive leadership of His Grace Abune Dioskoros as General Manager of the Patriarchate Head Office and His Grace Abune Sawiros as General Secretary of the Holy Synod building permits were secured, soil tests were conducted, and design works were finalized. Yet, as the service terms of the two Archbishops concluded, physical excavation and construction could not immediately commence.

Subsequently, His Grace Abune Yared assumed leadership and leveraged the previously acquired construction permits to transition the project into full-scale building works; right after the global COVID-19 pandemic had subsided. Giving special priority to this massive modern structure, His Grace provided wise leadership by rapidly demolishing the old hall and constructing a temporary facility so that the Church's annual General Parish Spiritual Council meetings would proceed without interruption. By initiating and advancing the construction of this new monumental facility with remarkable success, he completed his term of service.

Following His Grace's term of office, His Grace Abune Abraham presumed leadership and took over the construction of this monumental building, which was already at a promising stage of execution. Advancing the construction, he introduced specific design modifications, incorporating a Holy Synod hall spanning 500 square meters capable of accommodating over one hundred venerable bishops, thereby leaving his own indelible mark before the conclusion of his term.

Succeeding His Grace Abune Abraham as General Manager, His Grace Abune Sawiros, working alongside His Grace Abune Dioskoros, General Secretary of the Holy Synod built upon the groundwork laid by the venerable fathers before them. By conferring with the building contractors, consultancy firm, and Church engineers, and placing exceptional focus on accelerating the remaining work, this modern and monumental international building has now been successfully completed and brought to its grand inauguration.

While it is true, as briefly noted above, that this modern and monumental building reached its grand inauguration today with exceptional speed, quality, and beauty because the Graceful General Manager continuously monitored the construction and provided clear direction through discussions with the contractor and

consultancy firm, it is an undeniable fact that the sluggishness and delays previously observed in the construction were uniquely resolved, and work began progressing at an astonishing pace primarily through His Grace's extraordinary efforts and unflagging supervision.

His Grace Abune Sawiros, who ensured that this internationally benchmarked, beautiful structure was thoroughly and perfectly completed for today's inauguration, achieved outstanding results during his tenure. He ensured adequate parking space around the building, had the compound enclosed with a perimeter wall adorned with art reflecting our Church, and rendered the grounds attractive and visually captivating thereby elevating the Patriarchate Head Office to match the dignity and stature of the Church. Through these accomplishments, he has executed a monumental body of work that will ensure his legacy is commemorated throughout history.

This monumental building comprises a main hall with a seating capacity of over 2,800 attendees, nine smaller conference and training halls, a Holy Synod hall accommodating over one hundred venerable archbishops, a museum and digital library, offices, a modern restaurant, and numerous restroom facilities.

This great international conference center is a project that serves as a primary example of generational succession within the Church conceived by the visionary mind of His Holiness Abune Paulos, initiated and completed during the patriarchate of His Holiness Abune Mathias, issued its construction permit during the tenure of His Grace Abune Dioskoros as General Manager and His Grace Abune Sawiros as General Secretary of the Holy Synod, and brought to its grand inauguration during the tenure of His Grace Abune Sawiros as General Manager and His Grace Abune Dioskoros as General Secretary of the Holy Synod.

We congratulate His Holiness Abune Mathias, Patriarch, on the inauguration of this modern hall, which began during his reign. To the respected General Managers of the Patriarchate Head Office who left your leadership imprint from its inception to its final execution to bring this project to fruition, we likewise extend our congratulations.

While admiring and expressing our gratitude for the synchronized and effective work of His Grace Abune Sawiros, General Manager of the Patriarchate Head Office and Archbishop of the Sheger and West Shewa Dioceses, as well as His Grace Abune Dioskoros, General Secretary of the Holy Synod and Archbishop of the Raya Diocese, we invite you to read and gain insights from the commemorative magazine we have prepared for this building's inauguration program. We do so with full confidence that new projects initiated by His Grace Abune Sawiros will achieve similar success through generational succession, just as previous development endeavors have prospered before them.

Liqe Siyuman Eskindir Gebre Kristos

Head of the Public Relations Department of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church and General Manager of the Houses and Buildings Administration and Development Enterprise

Message from the Grand Committee

The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church has always been a leading role model for modernity and development in addition to being a pillar of the country and religion throughout its long history. Accordingly, in 2019, the "Tsirha Tewahedo" International Evangelization and Conference Center is one of the major and strategic development projects that will be inscribed in golden letters in the history books and inaugurated with great spiritual ceremony. This great center is an institutional asset that fully reflects the global status and potential of our church, integrating modern technology and architectural art with service. The Grand Inauguration Committee has fully taken on its historic responsibility to oversee the launch of this modern, international gospel and conference center. The committee is actively working to guarantee that the inauguration ceremony reflects the Church's global standing through a colorful, memorable, and reverent celebration.

